ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

እሁድ 83ኛ ዓመት ቁጥር 125 ጥር 5 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




## "የወንጪ-ደንዲ ኢኮቱሪዝም ሥራን በአጭር ጊዜ በጥራት ማከናወን እንደምንችል ማሳያ ነው"

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር)

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የወንጪ-ደንዲ ኢኮቱሪዝም ፕሮጀክት ሥራን ጀምረን በአጭር ጊዜ ውስጥ በጥራት ማከናወን እንደምንችል ማሳያ ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች አካል የሆነውን የወንጪ-ደንዲ ኢኮቱሪዝም ፕሮጀክትን ትናንት በይፋ መርቀዋል።


የወንጪ ደንዲ ኢኮ ‹..ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም መንደር የኢትዮጵያን ቱሪዝም የሚያሳድግ ነው

ታደሠ ብናልፈው



አዲስ አበባ፡- የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም መንደር የኢትዮጵያን ኢኮ ቱሪዝም ከማሳደግ ባለፍ የአፍሪካ ኢኮ ቱሪዝም እንዲያድግ በር የሚከፍት ነው ሲሉ የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን ሊቀመንበር ሙሳ ፋቂ ገለጹ፡፡

የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን ሊቀመንበር ሙሳ ፋቂ የወንጪ ደንዲያ ኢኮ ቱሪዝም መንደርን ጎብኝተዋል፡፡

በጉብኝቱም እንደተናገሩት፤ የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም መንደር የሀገሪቱን ኢኮ ቱሪዝም የሚያሳድግና የአፍሪካ ኢኮ ቱሪዝም ዘርፍ የሚያነቃቃ ነው ፡፡

የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም መንደር የአካባቢው ማህብረሰብ እንዲለማ፤ እንዲያድግ በማድረግ ትልቅ ሚና ይጫወታል ያሉት


የወንጪ ደንዲ ኢኮ ‹..ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## "በፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ሆነን ባደረግናቸው የዲፕሎማሲ ሥራዎች በጎ ውጤቶች ተመዝግበዋል"

-አምባሳደር ተሾመ ቶጋ


ገጽ 4


## "ከብልህ ደጃፍ ደረሰኝ ይቆረጣል"

ተስፋ ፈሩ



ሐተታ

ግዢ ስንፈጽምና አገልግሎት ስናገኝ ደረሰኝ የመቀበል ልምድ ያለን ምን ያህሎቻችን ነን ? በሀገራችን ደረሰኝ ባለመቁረጥ፣ ሐሰተኛ ግብይት በመፈጸምና ከዋጋ በታች ተምኖ ደረሰኝ በመቁረጥ መንግሥት ከታክስ ማግኘት


"ከብልህ ደጃፍ ደረሰኝ ...ወደ ገጽ 4 ዞሯል

















# “የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ታሪክ ከወገንተኝነትን ይልቅ ፍትሐዊነት ላይ ያተኮረ ነው”

- የታሪክ ምሁሩ ኤመሬተስ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- ለረጅም ዘመናት ያስቆጠረው የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ታሪክ ከወገንተኝነት ይልቅ ፍትሃዊነት ላይ ያተኮረ ነው ሲሉ የታሪክ ምሁሩ ኤመሬተስ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ ተናገሩ።

“ዲፕሎማሲያችን ለብሔራዊ ጥቅማችን” በሚል መሪ ሃሳብ የተዘጋጀው ኤግዚቢሽን በተጓዳኝ በተዘጋጀው የፓናል ውይይት ላይ ኤመሬተስ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ ጥንታዊውን የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ታሪክ የተመለከተ ጥናታዊ ጽሁፍ አቅርበዋል።

በጽሁፋቸው ጥንታዊ የኢትዮጵያ ነገስታት ክርስቲያን በመሆናቸው ብቻ በዓለም የተለያዩ አካባቢዎች የሃይማኖት መሰረት ያላቸው ጦርነቶች ሲከሰቱ አዱን ወገን እንዲደግፉ ዲፕሎማሲያዊ ጫና እንደደረሳቸው አስረድተዋል።

ይሁንና ነገስታቱም ሆኑ መሪዎች በማንኛውም ጊዜ ወገንተኝነት ያለው ድጋፍ ሳይሆን ሁሉንም አካላት በሚያግባባ መልኩ ነገሮችን በማጤን ግጭቶችን ከማባባስ እንደተቆጠቡ ጠቁመዋል።

በዘመናት መካከል የነበረው የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲም ከወገንተኝነት ይልቅ ብሔራዊ ጥቅምን በማስከበር ላይ ያተኮረ መሆኑም በርካታ ማስረጃዎች መኖራቸውን አመልክተዋል።

በመስቀል ጦርነት ወቅትም ሆነ በእስራኤልና ፍልስጤም እንዲሁም አረቦች ጦርነት ወቅት ኢትዮጵያ አንድን ወገን ደግፋ እንድትቆም ብትጠየቅም ማንንም ወገን ሳትደግፍ በብልሃት ያለፈችባቸው ጊዜያት መኖራቸውን አንስተዋል።

በተለያየ ዘመናት የነበሩ የኢትዮጵያ መሪዎች በዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲ ከፍተኛ ሚና መጫወታቸውንና የኢትዮጵያ ተወካዮች በአፍሪካ ህብረትና በዓለም አቀፍ በነበራቸው የዲፕሎማሲ ተሳትፎ አከራካሪ ጉዳዮችን በማጤን በድምጸ ተአቅቦ ያልፉ እንደነበርም ጠቁመዋል።

የዲፕሎማሲ ታሪካችን መሃል ሆኖ የሚመለከትና በወቅቱ ከነበረው የሃይማኖት፣ የንግድና መሰል ጉዳዮች ጋር ተያይዞ ያለውን ቅርበት ተመርኩዞ ከመደገፍ ይልቅ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም አንጻር ዲፕሎማሲው የሚታይበት አግባብ ነበር ሲሉ ተናግረዋል።

በየክፍለ ዘመኑ የነበሩ የኢትዮጵያ መሪዎች የተለያየ የዲፕሎማሲ ሥራ ቢኖራቸውም በአፍሪካና በዓለም አቀፍ ተቋማት ላይ ያከናወኑት ስራ የኢትዮጵያን ዲፕሎማሲ ያጎላ ነበር ብለዋል።

በ15ኛውና በ16ኛው ክፍለ ዘመንና በየጊዜው የነበሩ መሪዎች በተለያዩ ጊዜያት በነበሩ ጦርነቶችና መድረኮች ላይ ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ሚና በመጫወት የሀገራቸውን ሚና አጉልተዋል ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት የደረሱባትን የዲፕሎማሲ ጫናዎች የተወጣችበት ታሪክ አስተማሪም አንዳንድ ጊዜም ክፍተት ያለበት እንደነበርም ጠቁመዋል።

ትውልዱ የቀደምትና የአሁን ዲፕሎማሲ ታሪክና ሂደቶች በማጥናት ለቀጣዩ ሁኔታ ሁሉ በቂ ስንቅ መያዝ እንዳለበት አመልክተዋል።

# የባለብዙ ወገንና የሁለትዮሽ ስኬታማ የዲፕሎማሲ ሥራዎች ተከናውነዋል

## -ዓመታዊ የሚሲዮን መሪዎች ስብሰባ ተጀመረ

**ሞገስ ጸጋዬ**



አዲስ አበባ፡- የ2016 ሩብ ዓመት ስኬታማ የባለብዙ ወገንና የሁለትዮሽ የዲፕሎማሲ ተግባራት መከናወናቸውን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

ዓመታዊ የሚሲዮን መሪዎች ስብሰባ መከፈቱን አስመልክቶ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቷል። በስብሰባው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተጠሪ ተቋማት ኃላፊዎችም ተገኝተዋል።

ለጋዜጠኞች መግለጫ የሰጡት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ አለም (ዶክተር) እንደገለጹት፣ መድረኩን በንግግር የከፈቱት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ሲሆኑ በ2016 ሩብ ዓመት የነበሩ አጠቃላይ ሂደቶችን በተመለከተ ገለጻ አድርገዋል። በቀጣይ ሪፖርቶች ቀርበው ውይይት እንደሚደረግባቸውም ገልጸዋል።

ዘርፎች የሩብ ዓመቱን አጠቃላይ ሪፖርት ያቀርባሉ ተብሎ ይጠበቃል ያሉት አምባሳደሩ፤ ያለፈው የ2016 ሩብ ዓመት ስኬታማ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ የተደረገበት ነው ብለዋል።

ከባለብዙ ወገን አንጻር ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግሥታት መድረኮች ላይ አቋሞቿን በሚገባ በማንጸባረቅ ድል ያገኘችበት እንደሆነ ገልጸው፤ከብርቱ የዲፕሎማሲ ሥራና እንቅስቃሴ በኋላ ኢትዮጵያ የብሪክስ አባል የሆነችበት ሌላኛው ውጤት ነው ብለዋል።

ሌላው ከናይል ተፋሰስ አንጻር ብሩንዲ የትብብር ማዕቀፍ ስምምነትን የፈረመችበትና ያጸደቀችበት ወቅት ነው ያሉት አምባሳደር መለስ፤ ከተለያዩ ሀገሮች ጋር የሁለትዮሽና የጋራ ኮሚሽን ስብሰባዎች መካሄዳቸውንም አውስተዋል።

ከየሀገሮች ጋር ለበለጠ ግንኙነት መጠናከር ሥራ የተሰራበት መሆኑን ገልጸው፤ የበርካታ ሀገራት መሪዎች በሀገራችን ጉብኝት አድርገው ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸውን ግንኙነት የበለጠ የጎለበተ እንዲሆን ለማድረግ ከመግባባት ተደርሷል ነው ያሉት።

ኢትዮጵያም በመሪዎቿ በኩል በተለያዩ ሀገሮች ጉብኝቶች ተካሂደዋል ያሉት ቃል አቀባዩ፤ይህም ኢትዮጵያ ከሀገሮች ጋር ያላት ግንኙነት የበለጠ እንዲጠናከር አስተዋጽኦ ያደርጉ እንደነበር አብራርተዋል።

በተለያዩ አለም አቀፍ መድረኮች ላይ ኢትዮጵያ በጎ ገጽታዋን የሚያሳዩ እንቅስቃሴዎች መደረጋቸውን ገልጸው፤ በተለይ የኮፕ 28ና የዓለም የፋይናንስ መድረኮች ላይ ኢትዮጵያ ከራሷ አልፋ የሌሎች አፍሪካውያን ወንድሞች ድምጽ ለመሆን መቻሏን አስገንዝበዋል።

የዲፕሎማሲ ሳምንት ከጥር 2 ቀን ጀምሮ እየተከናወነ እንደሚገኘ አስታውሰው፤ በዲፕሎማሲ ሳምንቱ የፓናል ውይይት መደረጉን፤6 የጥናት ጹሁፎች ቀርበው ውጤታማ ምክክር መካሄዳቸውን ጠቅሰዋል። ሌላኛው የዲፕሎማሲ ሳምንት አካል የሚሲዮን መሪዎች ዓመታዊ ስብሰባ መካሄድ መጀመሩን አምባሳደር መለስ አለም ገልጸዋል።

እንደ አምባሳደር መለስ ገለጻ፤ ትናንት የተጀመረው የሚሲዮን መሪዎች ስብሰባ በቀጣይ ቀናት በዲፕሎማሲ ጉዳዮችና በሌሎች ዙሪያ ውጤታማ ውይይት ያደርጋል። ስብሰባው እስከ ጥር 18 የሚቆይ ይሆናል። አጠቃላይ የሥራ ሂደቶችን በተመለከተ ውይይት ይካሄዳል። የመስክ ጉብኝት እንደሚኖርም ጠቁመዋል።

# ‹‹ዘላቂ እድገትን ለማረጋገጥ በጥናት የተደገፈ የፖሊሲ ግብዓት ያስፈልጋል››

- ነመራ ገበየሁ (ዶ/ር)
የፕላንና ልማት ሚኒስትር ዴኤታ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በጥናት ላይ የመሰረተ ሁሉን አካታችና ዘላቂ እድገት ማረጋገጥ የሚያስችል የፖሊሲ ግብዓት ማዘጋጀት ያስፈልጋል ሲሉ የፕላንና ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ነመራ ገበየሁ (ዶ/ር) ገለጹ።

"የአየር ንብረት ለውጥን በመቋቋም ዘላቂ እድገት የምታረጋግጥ ኢትዮጵያ" በሚል መሪ ሃሳብ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ከዓለም አቀፍ የእድገት ማዕከል (IGC)፣ከለንደን እስኩል ኦፍ ኢኮኖሚክስና ከኦክስ ፎርድ ዩኒቨርሲቲ ከተወጣጡ ተመራማሪዎች ጋር በአየር ንብረት ለውጥ ዙሪያ ውይይት ተካሂዷል።

የፕላን እና ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ነመራ ገበየሁ (ዶ/ር) በጥናት ላይ የመሰረተ ሁሉን አካታች የሆነና ዘላቂ እድገት ማረጋገጥ የሚያስችል የፖሊሲ ግብዓት ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

የውይይት መድረኩ የተዘጋጀው የአየር ንብረት ለውጥ አብዛኛውን የኢትዮጵያን ሕዝብ እየጎዳ በመኾኑ መንግሥት እንዴት ይህን ችግር መቅረፍ ይችላል በሚለው ጉዳይ እንዲሁም ሀገሪቱ የጀመረችውን ጉዞ የሚያጠናክር ጥናት በመኾኑ ውይይት ለማድረግ የተዘጋጀ መድረክ ነው ብለዋል።

ዶክተር ነመራ አክለውም፤ ኢትዮጵያ በታዳሽ ኃይልና በኢንዱስትሪ ዘርፍ ያላትን እምቅ አቅም ለመጠቀም እንዲሁም የአየር ንብረት ለውጥን ተቋቁማ ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ በጥናት የተደገፉ የፖሊሲ ግብዓቶች ያስፈልጓታል ብለዋል።



እንደ ዶክተር ነመራ ገለጻ፤ የአየር ንብረት ለውጥን ከመጠበቅ ጎን ለጎን ዘላቂ እድገት መረጋገጥ ለነገ የማይባል ጉዳይ ነው።

መንግሥት በቀጣይነት የግል ሴክተሩን ማሳተፍ የሚችልበት መንገድ በሚጠናው ጥናት የሚካተት መሆኑንም ዶክተር ነመራ ጠቁመዋል።

ከማዕከሉ ጋር በትብብር እየሰራን ነው ያሉት ዶክተር ነመራ፤ መንግሥት በቀጣይ ሊሰራቸው የሚገቡ ጉዳዮች ላይ ምክረ ሃሳብ እያቀረበ ይገኛል ብለዋል።

አዲስ የሚጠኑ ጥናቶች ሀገሪቱ ያላትን ሀብት በምን መልኩ መጠቀም እንዳለባት የሚያመላክቱ ናቸው።

ስማርት ሲቲን ከመፍጠርና የሶላር ኢንቨስትመንት ከማሳደግ ረገድ ኢትዮጵያ ሰፊ እድሎች አሏት ያሉት ዶክተር ነመራ፤ጥናቱ አዳዲስ የፖሊሲ ለውጦች ይዞ የሚመጣ መሆኑን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ የኢነርጂ ተጠቃሚነቷን ለማስፋት የተለያዩ አማራጮችን እየተከተለችና እየተጠቀመች እንደምትገኝ ጠቁመዋል።

እንደ ዶክተር ነመራ ገለጻ፤መንግሥት የያዛቸውን የለውጥ ስራዎች በተጨማሪ በጥናት የተደገፉ የፖሊሲ ግብዓት ማዘጋጀት ወሳኝ ነው።

በኢትዮጵያ የዓለም አቀፉ የእድገት ማዕከል ከፍተኛ የኢኮኖሚ ባለሙያ ቴዎድሮስ መኮንን (ዶ/ር) በበኩላቸው ተቋማቸው ከመንግሥት ጋር እየሰራ ነው ያሉ ሲሆን፤ማዕከሉ መንግሥት ያሉበትን የፖሊሲ ጥያቄ በመውሰድ ለፖሊሲ ግብዓት የሚሆኑ ጥናቶች ያጠናል ብለዋል።

እንደ ዶክተር ቴዎድሮስ ገለጻ፤ ከዚህ በፊትም ከመቶ ሃምሳ በላይ የጥናት ፕሮጀክቶች ተሰርተው ለተለያዩ መንግስት መስሪያ ቤቶች ቀርበዋል።

ማዕከሉ የሚወጡ ፖሊሲዎች በጥናት የተደገፉ እንዲሆኑ አስተዋፅኦ እያበረከተ ነው ያሉት ዶክተር ቴዎድሮስ፤የአየር ንብረት ለውጥ በዘላቂ ልማት ላይ የሚያሳድረውን ጫና ለመቀነስ እንዴት መስራት እንዳለበት አዲስ የጥናት አውድ ተከፍቶ እየተሰራ እንደሆነ ጠቁመዋል።

# “የወንጪ-ደንዲ ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በወቅቱ ባስተላለፉት መልዕክት የወንጪ-ደንዲ ኢኮቱሪዝም ፕሮጀክት በአጭር ጊዜ ውስጥ ትልቅ ሥራ መስራት እንደሚቻል የተረጋገጠበትና መደመር በተግባር የታየበት መሆኑን ተናግረዋል።

ፕሮጀክቱ ከተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በተሰባሰበ ሀብት፣ ከተለያዩ አካባቢዎች በመጡ ባለሙያዎች እና የፕሮጀክት አስተባባሪዎች የተገነባ በመሆኑ መደመር በተግባር የታየበት ነው ብለዋል።

ከወንጪ አካባቢ የወጡ በርካታ ጀግኖች የኢትዮጵያን አንድነት ለማስጠበቅና ሉዓላዊነት ለማስከበር ትልቅ ውለታ መዋላቸውን አስታውሰዋል።

መደመር በጋራ ተያይዞ ማደግ መሆኑን ጠቁመው፤ የኢትዮጵያን ብልጽግና ለማረጋገጥ መደመር ወሳኝ ነው ብለዋል።

ፕሮጀክቱ ወንጪንና አካባቢውን በልማት ማስተሳሰር የሚያስችል መሆኑንም ገልጸዋል።

የወንጪ-ደንዲ ኢኮቱሪዝም ፕሮጀክት የተለያዩ መሰረተ ልማቶችን ያቀፈ በመሆኑ ባለሀብቶች በቀጣይ ለሚሰሩት ሥራ የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠሩን ጠቁመዋል።

ፕሮጀክቱ ጅምር ሥራ መሆኑን ጠቅሰው፤ በቀጣይ ትልቅ ሥራ ይጠበቅብናል በማለት ተናግረዋል።

በቀጣይ አምቦን፣ ወንጪ-ደንዲ ሀይቅን፣ ወሊሶን አንድ ላይ የሚያስተሳስር ትልቅ ሥራ መሥራት እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

ባለሀብቶች የወንጪ-ደንዲ አካባቢ በስፋት በኢንቨስትመንት እንዲሳተፉ የክልሉ መንግሥት በትኩረት ሊሠራ እንደሚገባ ገልጸው፤ የወንጪ አካባቢ ማህበረሰብ የአካባቢውን ተፈጥሮ ጠብቆ እንዳቆየ አሁንም ይህንኑ ተግባር አጠናክሮ እንዲቀጥል መልዕክት አስተላልፈዋል።

በባህሉ እንግዳ ተቀባይ የሆነው ህዝብ ወንጪ-ደንዲን ለመጎብኘት የሚመጡ እንግዶችን በመልካም ሁኔታ በመቀበል ስሙን ጠብቆ መቀጠል እንዳለበት ገልጸዋል።

ጎብኚዎችን ተንከባክቦ አስተናግዶ በደስታ እንዲመለሱ በማድረግ የጎብኚዎችን ቀልብ መሳብና የተሻለ ገቢ የሚያገኝበትን መንገድ ማመቻቸት ይኖርበታል ሲሉ ተናግረዋል።

በተፈጥሮ በተቸረን ሀብት ላይ ጠንክረን በመስራት ብልጽግናችንን ማረጋገጥ ይገባናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የተጀመረውን የብልጽግና ጉዞ ከማረጋገጥ የሚያስቆመን ነገር የለም ብለዋል።

በቀጣይም በአገሪቱ የተለያዩ የልማት ሥራዎችን በአጭር ጊዜ ለማጠናቀቅ እንተጋለን ሲሉ ገልጸዋል።

የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ በበኩላቸው የወንጪ - ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም መንደር የቱሪዝም ማዕከል ብቻ ሳይሆን የብዙ እድሎች መግቢያ በር ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ፕሮጀክቱ ገቢ በማመንጨት፣ የሥራ እድል በመፍጠር እንዲሁም ስራ ፈጠራን በማበረታታት ለኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያደርግ ጠቅሰዋል።

ከጠቅላይ ሚኒስትሩ በተጨማሪም የአፍሪካ ኅብረት ኮሚሽን ሊቀመንበር ሙሳ ፋኪ ማኅማት፣ የኢጋድ ሊቀመንበር ወርቅነህ ገበየሁ (ዶ/ር) እና ሌሎች የዲፕሎማቲክ ልዑካን ቡድን አባላት እንዲሁም የፌዴራልና የክልል ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች በምረቃ ሥነ ሥርዓቱ ተገኝተዋል።

የወንጪ-ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም መንደር በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) 'ገበታ ለሀገር' መርሐ ግብር ከተገነቡት መዳረሻዎች ሶስተኛው መሆኑን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት መረጃ ያመላክታል።የወንጪ ዳንዲ ኢኮ ቱሪዝም መንደርን በማልማት ሂደት በግንባታው ምዕራፍ ከ8ሺህ እስከ 12 ሺህ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል የፈጠረ ሲሆን በዚህም ግዙፍ የመሰረተ ልማት ሥራ ተሰርቷል። ከእነዚህም 43 ኪሎ ሜትር መንገዶች፤ 35ኪሎ ሜትር የመንገድ መብራት እና የኃይል አቅርቦት፤ 72 ሜትር ድልድይ እና ትምህርት ቤት ተጠቃሽ ናቸው። የአካባቢው ወጣቶች ታላላቅ የልማት ራዎች ይዘው የሚመጡትን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ማጣጣም ጀምረዋል። ሰፊው የአካባቢው ማኅበረሰብም አሁን የላቀ የተጠቃሚነት ዕድል ማግኘቱን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ማስፈራቸው ይታወሳል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የጋራ ዕጣ ፈንታችንን በጋራ!

የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ከመልክዓ-ምድራዊ ጉርብትና ባለፈ ከፍ ያለ ማኅበራዊ ትስስር ያላቸው ሕዝቦች ናቸው። የቅኝ ግዛት መስመሮች እንደ ሀገር ይከፋፍላቸው እንጂ፤ አሰፋፈራቸው ከመስመሩ ያለፈ ስለመሆኑ አካባቢውን ለማየት ዕድል ላገኘ በቀላሉ ሊያስተውለው የሚችለው ተጨባጭ እውነታ ነው ።

በአንዱ ሀገር ያለ ሕዝብ በሁለንተናዊ ማንነቱ/ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ማንነቱ/ድንበር ተሻግሮ በሌላ ሀገር፣ በሌላ ዜግነት ሰፍሮ ማየት የተለመደ ነው። የሕዝቦቹ እንቅስቃሴም ቢሆን በድንበር መስመሮች የሚገታ አይደለም፤ ከዚያ አልፎ የሄደ ነውና።

በአብዛኛው የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች በባሕልና በሃይማኖት የተሳሰሩ፣ ማኅበራዊ እሴቶቻቸው በመካከላቸው ጠንካራ ትስስርና ጉርብትና መፍጠር የሚችሉና የፈጠሩም ናቸው የዕለት ተዕለት ማኅበራዊ መስተጋብራቸውም ነገዎቻቸውን በጋራ እንዲሠሩ የሚያስገድዳቸው ነው።

ይህም የጋራ ሠላማቸውን በጋራ ማጽናት የሚያስችል፣ ከዚያም አልፈው ያላቸውን አቅም አቀናጅተው ነገዎቻቸውን ብሩህ ማድረግ የሚያስችል መልካም ዕድሎችን ብሎም ስለ ነገዎቻችው መክረው ለጋራ ተጠቃሚነት ሊንቀሳቀሱ የሚችሉበትን የተሻለ አማራጭ ፈጥሮላቸዋል።

እስካሁን ባለው እውነታ ግን ይህ ሲሆን አልታየም። ከሁሉም በላይ አካባቢው ካለው የጂኦ-ፖለቲካል ስትራቴጂ አኳያ የብዙዎች ዓይን ማረፊያ፣ የብዙ ፍላጎቶች መሻኮቻ በመሆኑ የአካባቢው ሀገራት በተለያዩ ወቅቶች በሚከሰቱ ግጭቶች ሠላማቸውን በማጣት ብዙ ያልተገባ ዋጋ ለመክፈል ተገደዋል፤ ዛሬም እንደተገደዱ ናቸው ።

ያለ ፍላጎታቸው በሚገቡበት ግጭት ለከፋ ድህነትና ኋላቀርነት፤ ግጭት ለሚያስከትለው ሞትና ስደት፣ የኢኮኖሚ ውድመት ተዳርገዋል፣ ሁሉ እያላቸው ቀናትን ለማሸነፍ ሁሌም እጃቸውን ለምፅዋት ማንሳት ዕጣ ፈንታቸው ሆኗል። በዚህ ሁሉ ግን የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች ፍላጎታቸው ሠላም እና ልማት ነው።

የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች እንደ ሀገር ካላቸው ሊለማ የሚችል የተፈጥሮ ሀብትና አምራች የሰው ኃይል አኳያ ከልማት ጋር የተያያዘው ፍላጎታቸው ሊያጋጥመው የሚችለው ተግዳሮት ሠላማቸውን መመለስ እስከቻሉ ድረስ ብዙም እንደማይሆን ይታመናል።

በተለይም የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች ያላቸውን አቅም አቀናጅተው በጋራ መንቀሳቀስ የሚችሉበት ዕድል ከተፈጠረ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ አዲስ የኢኮኖሚ አቅም ሆነው ሊወጡ እንደሚችሉ ብዙም አጠያያቂ አይደለም። ለዚህ በኢትዮጵያ ያለው ተጨባጭ ተሞክሮ ማየት በቂ ነው ።

የሀገራቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ አዲስ የኢኮኖሚ አቅም ሆኖ የመውጣት አቅም፣ የሚያሳስባቸው፤ ለብሔራዊ ጥቅማችን ስጋት ነው ብለው የሚያምኑ ሀገራትና ቡድኖች አካባቢው የግጭት ማዕከል እንዲሆን እንቅልፍ አጥተው እየሠሩ ነው። በቀጣናው ላለፉት ስድስት አስርተ ዓመታት የሆነውም ይሄው ነው።

ለዚህ ደግሞ በቀጥታ በሀገራቱ የውስጥ ጉዳይ ከመግባት ጀምሮ፤ በሀገራቱ መካከል ልዩነቶችን ለሚያቀነቅኑ ቡድኖች እና ሥልጣን ላይ ለሚገኙ መሪዎች ድጋፍ እያደረጉ የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች ዕጣ ፈንታቸውን በጋራ እንዳይሠሩ ግድግዳ ሆነውባቸዋል።

የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች ቅኝ ገዥዎች ባሰመሯቸው የልዩነት መስመሮች ታግተው፣ ከገዛ ወንድሞቻቸው ጋር የጋራ ዕጣ ፋንታቸውን የሚወስኑበትን ነፃ ፈቃድ ተነጥቀው፣ በጥርጣሬ እንዲተያዩ ሆነዋል። ይህም ችግሮቻቸውን ከማወሳሰብ ባለፈ ያመጣላቸው አንድም የተሻለ ነገር የለም፤ ሊኖርም አይችልም ።

አሁን ግን ዘመኑን በሚዋጅ መንገድ፤ እንደ አንድ የቤተሰብ አባል የጋራ ዕጣ ፈንታቸውን በጋራ መወሰን የሚችሉበትን ተፈጥሯዊ መብታቸውን መጠቀም የሚችሉበት ዕድል ተፈጥሯል። በአንድነት ተነስተው ለጋራ ብሩህ ነገዎቻቸው የሚነሱበትና በቁርጠኝነት የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታም ተፈጥሯል ።

ይህ መብታቸው በየትኛውም የውጪ ኃይል የጥቅም መሻትም ሆነ፣ በመንግሥታት ፍላጎት እንዳይደናቀፍ፣ በየትኛውም ፈተና ተሰናክሎ እንዳይወድቅ ዘብ ሊቆሙ ይገባል፤ ትናንት በመከፋፈላቸው አቅም አጥተው የከፈሉትንና አሁንም እየከፈሉ ያለውን ያልተገባ ዋጋ በማጤን ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያውያን የቀረበውን አብሮ የመልማት ጥሪ ሊቀበሉ ይገባል።

እንደ አንድ ቤተሰብ የጋራ ዕጣ ፈንታችንን በጋራ ለመሥራት፤ በዚህም ለራሳችን ሆነ ለመጪዎቹ ትውልዶች የተሻለች የአፍሪካ ቀንድ አካባቢን ለመፍጠር፤ በተባበረ አዕምሮና ክንድ አዲስ የኢኮኖሚ አቅም ሆኖ ለመውጣት ጥሪውን በበጎ ሕሊና መቀበል ተገቢ ነው!

አዲስ ዘመን
ኢፕድ
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

ዋና አዘጋጅ
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## እንቁው ዲፕሎማት አምባሳደር ከተማ ይፍሩ

በቁምላቸው አበበ ይማም(ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

እንደ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ያሉ ተቋማት ሀገርን አኅጉርን ሲሸከሙ፤ እንደ አምባሳደር ከተማ ይፍሩ ያሉ የሀገር ባለውለታዎች ደግሞ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርንና የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አይነትን ተቋም ተሸከመው የዛን ጊዜውን የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የዛሬውን አፍሪካ ኅብረት አዋልደዋል።

በኢትዮጵያ የዘመናዊ ዲፕሎማሲ ታሪክ ላይ የሚያጠነጥነው የዲፕሎማሲ ዓውደ ርዕይ ባለፈው ዓርብ ጥር 3 ቀን 2016 ዓ.ም በሳይንስ ሙዚየም ሲከፈት ከሩቅ ጎልተው ከሚታዩት ዲፕሎማቶች ግንባር ቀደሙ ክቡር አቶ ከተማ ይፍሩ ናቸው። እኔም በዚህ የዲፕሎማሲ ሰሞናት ጉምቱውን ዲፕሎማትና ሀቀኛ ፓን አፍሪካኒስት እንዲህ ልዘክራቸው፣ ላስተዋውቃቸው፣ ላከብራቸውና ላወድሳቸው፤ መኅልዬ መኅልዬ ዘ ከተማ ይፍሩ" አልሁ።

በፊውዳሉ ሥርዓት ሹመት ከብቃት ይልቅ በዘር በሚሰጥበት ወቅት ስሟ ብዙ ከማትታወቀው የሐረርጌ ግዛቷ ጋራ ሙለታ ከደሃ ገበሬዎች ቤተሰብ የተገኙትና በ30ዎቹ ዕድሜ የነበሩት ወጣት ከተማ ይፍሩ የሀገሪቷ የውጭ ጉዳይ ግንኙነት አድራጊ፣ ፈጣሪ እንዲሁም የአፄ ኃይለሥላሴ ዋና ልዩ አማካሪ (ቺፍ ኦፍ ስታፍ) ይሆናሉ ብሎ ያለመ አልነበረም።

ነገር ግን የማይታሰበው እውን ሆኖ ከተማ ከዚህም አልፎ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ምሥረታ ላይ አሻራቸውን ማሳረፍ ችለዋል። የታሪክ መዛግብትም ሆነ በቅርብ የሚያውቋቸው ተራማጅ ብለው የሚጠሯቸው ከተማ ኢትዮጵያ ቅኝ ባለመገዛቷ ከአህጉሩ የተለየችና ኢትዮጵያውያንም ልዩ ነን የሚል እሳቤ በአብዛኛው ዘንድ ቢንሸራሸርም ለሳቸው ግን የኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታ ከሌሎች አፍሪካውያን የተለየ አይደለም። መተባበር ካለባትም ከአፍሪካውያን ጋር ነው የሚል ቁርጠኛ አቋም ነበራቸው።

ገና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያሉ ሊግ ኦፍ ኔሽን ኢትዮጵያን አንቅሮ የተፋበት ሁኔታ ቁጭት እንደፈጠረባቸው በአሁኑ ሰዓት የሕይወት ታሪካቸውን "ከተማ ይፍሩ፤ የሰላም የዕድገት እና የፓን አፍሪካኒዝም አቀንቃኝ" በሚል ርዕስ ጽፎ ለሕትመት ያበቃው ልጃቸው መኮንን ከተማ ይናገራል። የጥቁር ሕዝቦች ነፃነት ተምሳሌት የሆነችው ኢትዮጵያ በጣሊያን ስትወረር አባል የሆነችበት የሊግ ኦፍ ኔሽን ይተባበረኛል የሚል እምነት ነበራት። ነገር ግን ያልተጠበቀው ሆኖ አፄ ኃይለሥላሴ ንግግር በሚያደርጉበት ወቅት በመዘባበት፣ በጩኸትና በፉጨት ንግግራቸው ተቋረጠ።

ይህ ሁኔታ ታዳጊው ከተማን ከማስከፋት አልፎ ለተጨቆኑ ሕዝቦች እንዲቆም፤ ለፍትሕና ለእኩልነት እንዲታገል መሠረት እንደሆነው የቅርብ ጓደኞቻቸው ምስክር ናቸው። በአንድ ወቅት የቀድሞው የጣሊያንና ጂቡቲ አምባሳደር ዶ/ር ፍትጉ ታደሰ ስለ ከተማ ተጠይቀው ሲመልሱ በቅኝ ግዛት ስር የነበሩ የአፍሪካውያን ሁኔታ ስለሚያሳስባቸውም "እኛ ነፃነት አግኝተን፤ እነርሱ በባርነት ቀንበር እንዴት ይሰቃያሉ" የሚል አስተሳሰብ ነበራቸው ብለዋል።

ለዚያም ነበር ኢትዮጵያ ከጣሊያን ጋር በነበራት ትግል የረዳቻት እንግሊዝን እንኳ ለመተቸት ቅንጣት ወደ ኋላ ያላሉት። እንግሊዝ በአፓርታይድ ጭቆና ስር ለነበረችው ደቡብ አፍሪካ የጦር መሣሪያ መሸጧንም በከፍተኛ ሁኔታ ተችተዋል። ከመተቸት ባለፈም ነፃ ያልወጡ የአፍሪካ ሀገራት ነፃ እንዲወጡ ከፍተኛ ርብርብና ለነፃ አውጭዎቿም ድጋፍ አድርገዋል።

ከዚህም ውስጥ የሚጠቀሰው ለማንዴላ በኢትዮጵያ ፓስፖርት እንዲዘዋወሩ ማድረጋቸው ነው። ማንዴላ በአፓርታይድ መንግሥት በቁጥጥር ስር ሲውሉ የከተማ ፎቶ በኪሳቸው ውስጥ እንደተገኘ የከተማ ልጅ መኮንን ይናገራል። ፎቶው ላይ ለነፃነት ታጋዩ የሚል ጽሑፍ የነበረበት ሲሆን ፎቶው በማንዴላ እስር ወቅት እንደ ማስረጃ ሰነድ ቀርቦ እንደነበር በደቡብ አፍሪካ ጆሀንስበርግ ቪትዝ ዩኒቨርሲቲ ሙዚየም በማስረጃነት ተቀምጧል።

1950ዎቹ ለአፍሪካውያን የተለየ ተስፋ ይዘው የመጡ ዓመታት ነበሩ። ወቅቱ የቅኝ ግዛት፣ የጭቆና እና የባርነት ቀንበር በመሰባበር የነፃነት ጎሕ መቅደድ የጀመረበት ነበር ሲል ቢቢሲ ያስታውሳል። በዛን ጊዜም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከዚህ ቀደም ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ ወጣቱ ፓን አፍሪካኒስት ከተማ የአፍሪካ አህጉራዊ ድርጅት መፈጠር አለበት የሚል ንግግር አደረጉ።

ነፃ በወጡት አፍሪካ ሀገራት መካከል አህጉራዊ ትብብርና ኅብረት የመፍጠር ፍላጎት ቢኖርም፤ ነፃ የወጡ ሀገራት ተዋሕደው አፍሪካ አንድ ልትሆን ይገባል የሚል እሳቤዎችም የጎሉበት ጊዜ ነበር። በአንድ ወገን ዋናና ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ሀገራቱ በፍጥነት ተዋሕደው አፍሪካ አንድ ልትሆን ይገባል የሚለው የካዛብላንካ ቡድን፤ እንዲሁም አንድ ከመሆን በፊት ሌሎች ትብብሮች ሊቀድሙ ይገባል የሚለው የሞኖሮቪያ ቡድኖች ነበሩ።

ኢትዮጵያም በወቅቱ የሞኖሮቪያን ቡድን ተቀላቅላ ነበር። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከተማ ኢትዮጵያ ሁለቱን አንጃዎች የማስማማት ሥራ መሥራት እንዳለባት ለንጉሡ አጥብቀው ተናገሩ። ምንም እንኳን በወቅቱ ወግ አጥባቂ የነበሩት ሹማምንቱና መኳንንቱ "እንምከርበት" የሚል ሀሳብ ቢያነሱም አፄ ኃይለሥላሴ ግን "ታምንበታለህ" የሚል ጥያቄ ብቻ እንዳቀረቡላቸውና ሂደቱን ብቻ እንዲያሳውቃቸው እንደነገሩት መኮንን ይናገራል።

ሁለቱም ቡድኖች ስብሰባቸው ላይ እንዲገኙ ጥሪ ሲያቀርቡ ለኢትዮጵያ መልካም አጋጣሚ እንደሆነ በማሰብ አጀንዳቸውን ይዘው ሄዱ። የሚኒስትሩ ዋነኛ አጀንዳ የነበረው ከ20 በላይ አባላት የነበሩትን የሞኖሮቪያን ቡድንና ስድስት ብቻ አባላት የነበሩትን የካዛብላንካን አንጃ አሳምኖ አዲስ አበባ ጉባኤ ማካሄድ ነበር።

ኢትዮጵያ ሁለቱን ቡድኖች አንድ ላይ ለማምጣት የመሪነት ቦታውን በመያዝ የሞኖሮቪያን ቡድን ስብሰባ ለመሳተፍ አቶ ከተማ ወደ ሌጎስ አመሩ። አመራሮቹን አዲስ አበባ በሚካሄደው ጉባኤ እንዲመጡ፤ በኋላም ንጉሡንም አሳምነው ለመሪዎቹ ምስጋና እንዲያቀርቡ ያደረጉ ሲሆን ንጉሡም " እኛ ከሞኖሮቪያም ሆነ ከካዛብላንካ አይደለንም። ከአፍሪካ ጋር ነን የሚል" ታሪካዊ ንግግራቸውን አደረጉ።

በተለይም በወቅቱ የሀሳቡ አመንጪና ከረር ያለ አቋም የነበራቸውን የጋናውን መሪ የነንክሩማህን ቡድን ማምጣት ቀላል እንዳልነበር ከተማ ይናገሩ እንደነበር ልጃቸው መኮንን ይገልፃል። በተለይም ጉዳዩን አወዛጋቢ ያደረገው በወቅቱ የሞኖሮቪያ አባል የነበሩት የቶጎው መሪ መገደል ያኛውን ቡድን መወንጀልና ሁኔታዎችም መካረር ጀመሩ። ነገሮችንም ለማለሳለስ ብዙ ጥረት ተደረገ።

ከዚህም ውስጥ ሌላኛውን የካዛብላንካ ቡድን አባል የነበሩትንም የጊኒውን መሪ ፕሬዚዳንት ሴኩቱሬንም ወደ አስመራ በመጋበዝ ከንጉሡ ጋር እንዲነጋገሩ ተደረገ። ኢትዮጵያና ጊኒ በመከፋፈል

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

ዜና

# "በፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ሆነን ባደረግናቸው የዲፕሎማሲ ሥራዎች በጎ ውጤቶች ተመዝግበዋል"

-አምባሳደር ተሾመ ቶጋ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በፈታኙ ሁኔታ ውስጥ ሆነን ባደረግናቸው የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴዎች ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው በጎ ውጤቶች ተመዝግበዋል ሲሉ አምባሳደር ተሾመ ቶጋ ገለጹ።

አምባሳደር ተሾመ ከሀገራዊ ለውጡ ወዲህ የተመዘገቡ አንኳር ዲፕሎማሲያዊ ድሎችና ስኬቶችን አስመልክተው በዲፕሎማሲ ሳምንት የፓናል ውይይት ላይ ባቀረቡት ጽሁፍ እንዳመላከቱት፤ ሀገራዊ ለውጡ ባለፉት አምስት ዓመታት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎችን እንዳመጣ ገልጸዋል። በተለይም በለውጡ የተከናወኑ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ፈጻሚ ተቋም ውስጥ የተሰሩ ሪፎርምና አቅም ግንባታ ሥራዎች ለዲፕሎማሲው ሥራ ምቹ ሁኔታዎች መፍጠራቸውን አስታውቀዋል።

በፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ሆነን ባደረግናቸው የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴዎች ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው በጎ ውጤቶች ተመዝግበዋል ነው ያሉት።

ከለውጡ ወዲህ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ማሻሻያ መደረጉን የገለጹት አምባሳደር ተሾመ፤ የውጭ አገልግሎት አዋጅና ይህንን መነሻ ያደረጉ መመሪያዎችና ተቋማዊ የአሰራር ደረጃዎች (ስታንዳርድ) መውጣታቸውን ጠቅሰዋል። በዚህም ለ20 ዓመታት ያለ ሰላምና ያለ ጦርነት የቆየው ከኤርትራ ጋር የነበረው ፍጥጫ እልባት ማግኘቱ ለሀገሪቱ መልካም ገጽታና ለዲፕሎማሲ ሥራው ትልቅ አቅምና ጉልበት እንደነበር ተናግረዋል።

በ2010 ዓ.ም የመጣው ሀገራዊ ለውጥ ለዲፕሎማሲ ሥራው ምቹ ሁኔታ መፍጠሩን በመግለጽ፤ በዚህ የዲፕሎማሲ ድል በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የኖቤል ሰላም ሽልማት አሸናፊ መሆናቸው ትልቅ ሀገራዊና አህጉራዊ ኩራት መሆኑን አምባሳደሩ አስረድተዋል።

ከለውጡ ቱሩፋቶች ባሻገር በሀገሪቱ በተለያዩ ጊዜያትና አካባቢዎች የተከሰቱ ግጭቶች፣ የኮቪድ ወረርሽኝ፣ የድርቅና አምበጣ መንጋ፣ የውስጥ መፈናቀል፣ የስደትና ፍልሰት ሁኔታ በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ ላይ ጥላ ያጠሉና ለዲፕሎማሲ ሥራው ተግዳሮት ሆነው እንደነበርም አንስተዋል።

በሌላ በኩል የዓለም ሁኔታዎች፤ በተለይም የዩክሬንና የሩሲያ ጦርነት ሁኔታውን የበለጠ አባብሰውት እንደቆዩም ጠቅሰዋል። ሆኖም ኢትዮጵያ በፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ሆና ባደረገችው የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው በጎ ውጤቶችን ማስመዝገብ ችላለች ነው ያሉት።

እንደ አምባሳደሩ ገለጻ፤ ለውጡና የፖለቲካ ርምጃዎች የፈጠሩት መልካም ገጽታ ብዙዎች ወደ ኢትዮጵያ ፊታቸውን ማዞር ችለዋል። ከኤርትራ ጋር ያለው ግንኙነት ለቀጣናው እፎይታን አምጥቷል። የሱዳንን ችግር በመፍታት ከአፍሪካ ህብረት ጋር በመሆን ኢትዮጵያ የተጫወተችው ሚና፣ የደቡብ ሱዳን መሪዎችን በማቀራረብ የሽግግር ጊዜ ፍኖተ ካርታ እንዲተገበር የተደረገው እንቅስቃሴና የተጫወተችው ሚና በዲፕሎማሲ ታሪክ ስኬት ሆኖ የተመዘገበ ነው።

በአፍሪካ ቀንድ የቀጣናውን ሀገራት ማቀራረብና በኢኮኖሚና መሠረተ ልማት ማስተሳሰር የሕዝብ ለሕዝብ ትስስርን ለማጠናከር ትኩረት ተሰጥቶ መሠራቱም አንዱ በዲፕሎማሲው ረገድ የተገኘ ውጤት እንደሆነ ገልጸዋል።

አፍሪካዊ ችግሮችን በአፍሪካዊ መፍትሄ የሚለው የኢትዮጵያ መርህ በብዙዎች ተቀባይነትን ያገኘ መሆኑን ጠቅሰው፣ በቀጣይም የዓለምን ተለዋዋጭ ሁኔታ ያገናዘበና ብሄራዊ ጥቅምን ያስከበር ሚናዋን አጠናክራ መቀጠል እንዳለባት ተናግረዋል።

# የወንጪ ደንዲ ኢኮ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ሙሳ ፋቂ፣ የሀገሪቱንም ኢኮ ቱሪዝም ከማሳደግ ባለፈ ለሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ተምሳሌት በመሆን ኢኮ ቱሪዝም ላይ እንዲሰሩ ያደርጋል ብለዋል፡፡

ፕሮጀክቱ ተፈጥሮ ጠብቆ ለማቆየት ትልቅ ሚና ይጫወታል፤ ለአካባቢው ማህበረሰብም የስራ ዕድል ይፈጥራል፤ አካባቢውም እንዲድግና እንዲለማ ያደርጋል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም መንደር አካባቢውን የሚያስተዋቅና የተለያዩ እድሎችን የሚከፍት ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ፕሮጀክቱ ለማህበረሰቡ ኢኮ ቱሪዝም ላይ እንዲሰራ ትልቅ መነሳሳትን የሚፈጥር ሲሆን ለአፍሪካ ኢኮ ቱሪዝም እንዲያድግ ትልቅ አስተዋጾኦ አለው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም መንደር የሀገሪቱ ትልቅ ሀብት በመሆኑ የአካባቢው ባለስልጣንና ማህበረሰቡ ሊጠብቀውና ሊንከባከበው ይገባል፤ ጎብኚዎችም ሊጎበኙት የሚገባ አስገራሚ ቦታ ነው ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

የኢጋድ ዋና ፀሀፊ ዶክተር ወርቅነህ ገበየሁ በበኩላቸው፤ የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም መንደር የሀገሪቱን ቱሪዝም ይበልጥ እንዲያድግ ያደርጋል፤ ለአካባቢው ማህበረሰብ የስራ እድል በመፍጠር የገቢ ምንጭ ሆኖ ይገለግላል፤ የበርካታዎችን ህይወት ይቀይራል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ወንጪ ውብ ተፈጥሮ ከታደላቸው የሀገሪቱ ቦታዎች አንዱ ነው፤ ተፈጥሮን የሰው እጅ ሲነካው የበለጠ ማራኪ ይሆናል፤ ይህንንም በዚህ ፕሮጀክት አይተናል ብለዋል፡፡

ሀገሪቱ የተፈጥሮና ታሪካዊ የቱሪዝም ሀብቶች የታደለች ቢሆንም፤ የተፈጥሮ ቱሪዝሙ እየታየ አይደለም፤ ወንጪ ይህንን ችግር በመፍታት ትልቅ ሚና እንደሚጫወት ገልጸዋል፡፡

ሀገሪቱን ቱሪዝም መዳረሻ በማልማት ኢኮኖሚውን ለመደገፍ የሚሰሩት ስራዎች የሚያስደንቁ ናቸው የገለጹ ዋና ፀሀፊው፤ ወንጪ ሀገሪቱ ያላትን የቱሪዝም እንቅስቃሴ የበለጠ እንዲያደርግ ያደርጋል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የተፈጥሮ ቱሪዝም ለማልማት ትልቅ ኢንቨስትመንት የሚጠይቅ ቢሆንም መንግሥት በራሱ ተነሳሽነት ትኩረት ሰጥቶ እየሰራበት ነው ፤ የግሉም ዘርፍ ሊሰራበት ይገባል ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

አፍሪካ በተፈጥሮና በታሪክ ቱሪዝም የታደለች እንደሆነች ገልጸው፤ የኢኮ ቱሪዝሙን ለማሳደግና ይበልጥ ተጠቃሚ ለመሆን አሁንም በትኩረት መስራት ይጠበቅባታል ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ በታሪክ ቱሪዝም የታወቀች ናት፤ የተፈጥሮ የቱሪዝም ማስፋፋት ተገቢ ነው፤ ሲሉ አመልክተዋል፡፡

የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም መንደር የወንጪ የሥራ እድል ይፈጥራል፤ መሰረተ ልማትን እንዲስፋፋና ቱሪዝሙ እንዲያድግና እንዲጎለበት ያደርጋል ሲሉ በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር ኧርቭን ሆሴ ማሲንጋ ተናግረዋል፡፡

የሀገሪቱ የግሉ ዘርፍ እንዲበረታታ ያደርጋል፤ ቱሪዝም እንዲስፋፋ ትልቅ እድል ይፈጥራል፡፡ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ኢኮ ቱሪዝም ላይ ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰራ ያደርጋል ብለዋል፡፡

ቦታው አስገራሚና አስደናቂ ስለሆነ የዓለም ቱሪስቶች መጥተው ሊጎበኙት ይገባል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ከአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# በዩኒቨርሲቲው ትኩረት የተሰጠው የኒውክለር ሳይንስና ምህንድስና ትምህርት

**መክሊት ወንድወሰን**

የኒውክሌር ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ የኒውክሌር ኃይልን ጥናትና አጠቃቀምን የሚመለከቱ የትምህርት እና የጥናት መስኮች ናቸው። የኒውክሌር ኢነርጂ የሚገኘው የአቶሚክ ኒውክሊየስ በመከፋፈል ወይም ውህደት ሲሆን አነስተኛ መጠን ያለው የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀትን በመጠቀም ከፍተኛ መጠን ያለው ይል የማቅረብ አቅም አለው።

የኒውክለር ሳይንስ ጥናት የኒውክሌር ፊዚክስን፣ የጨረር ባዮሎጂን፣ የኑክሌር ኬሚስትሪን እና የቁሳቁስ ሳይንስን ጨምሮ የተለያዩ ዘርፎችን ያጠቃልላል። በእነዚህ መስኮች ያሉ ተመራማሪዎች የኒውክሌር ኃይልን መሰረታዊ መርሆችን ለመረዳት እና ለትግበራው አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለማዳበር ይሠራሉ፡፡

የኒውክሌር ሳይንስ ለኤሌክትሪክ ምርት በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ የኑክሌር ኃይል ማመንጫዎች ሙቀትን በማመንጨት እና እንፋሎት በማምረት የኤሌክትሪክ ተርባይኖችን ለማሽከርከር ያገለግላሉ፡፡ በኒውክሌር ሃይል ማመንጫዎች የሚመነጨው ኤሌክትሪክ አስተማማኝ እና አነስተኛ የካርቦን መጠን ያለው በመሆኑ በነዳጅ ላይ ያላቸውን ጥገኝነት ለመቀነስ ለሚፈልጉ ሀገራት ተመራጭ ያደርገዋል።

ይሁን እንጂ የኒውክሌር ኃይል ማመንጫዎች ሥራ ከፍተኛ የደህንነት ፈተናዎችን ይኖሩታል፡፡ እንደ እ.ኤ.አ. በ 1986 በዩክሬን የተከሰተውን የቼርኖቤል አደጋ እና በ 2011ዓ.ም በጃፓን ፉኩሺማ አደጋን ተከትሎ ለኒውክሌር ኃይል ማመንጫዎች ሥራ ላይ ጥብቅ ደንቦች እና የደህንነት ፕሮቶኮሎች ተዘጋጅጅተዋል።

ከኒውክሌር ሃይል ጋር የተያያዘ ሌላው ፈተና የኒውክሌር ቆሻሻን ማስወገድ ነው። የኑክሌር ብክነት በጣም ራዲዮአክቲቭ ነው ፤ እናም ለብዙ ሺህ አመታት አደገኛ ሆኖ ሊቆይ ይችላል። የኒውክሌር ቆሻሻን ለማከማቸት እና ለማስወገድ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ውጤታማ ዘዴዎችን ማዘጋጀት ለኒውክሌር ኢንዱስትሪ እና ተቆጣጣሪ ኤጀንሲዎች ለይደር የማይተውት ጉዳይ ነው።



ዶክተር ጌታቸው አዳም

እነዚህ ፈተናዎች ቢኖሩም፣ የኒውክሌር ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ በሂደት ጥቅም ላይ እንዲውል እየተደረገ ነው፡፡ በአለም አቀፍ ደረጃ የኒውክሌር ኃይልን የበለጠ ተመጣጣኝ እና ዘላቂ ለማድረግ እንደ ትናንሽ ሞዱላር ሪአክተሮች (SMRs) እና የላቀ የኒውክሌር ነዳጅ የመሳሰሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እየተዘጋጁ ነው። የአለም ሀገራት የካርበን አሻራቸውን በመቀነስ ወደ ንፁህ የሃይል ምንጮች ለመሸጋገር በሚፈልጉበት ወቅት፣ የኒውክሌር ሃይል የአለምን የሃይል ፍላጎት በማሟላት ረገድ ትልቅ ሚና መጫወቱን በመገንዘብ እየሰሩበት ይገኛሉ።

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ሃገራችን በኒውክለር ሳይንስና ምህንድስና የላቀ ደረጃ ለማድረስ የተለያዩ የትምህርት መርሃ ግብሮችን በማዘጋጀት ብቁ ዜጋዎችን በማፍራትቀ ላይ ይገኛል፡፡ ለዚህም ይረዳው ዘንድ በያዝነው አመት በኒውክለር ሳይንስና ምህንድስና በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ ማስተማር ጀመሯል።

ኢትዮጵያ የኒውክለር ቴክኖሎጂን ለሰላማዊ ግልጋሎቶች በታሰበ መንገድ ለተለያዩ የልማት ስራዎች ለመጠቀም የሚያስችላትን የፕሮቶኮል ስምምነት ከዓለም አቀፉ አቶሚክ ኢነርጂ ኤጀንሲ ጋር ተፈራርማ እየሰራች መሆኑ ይታወቃል።

ከዚህ በተጨማሪም የኢትዮጵያና የሩስያ መንግስት በኢትዮጵያ የኒውክለር ሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማትን በጋራ ለማሳለጥ በሚያስችል የማእቀፍ ስምምነታቸው ለጤና፣ ለግብርና ፣እና ለተለያዩ ቴክኖሎጂዎች የሚውሉ ግብአቶችን ለማምረትና እንዲሁም ለሰው ሀይል ስልጠና ለመጠቀም የሚያስችልና በኒውክለር የሀይል ማመንጫ ዘርፍም በትብብር አብሮ ለመስራት የሚያስችል የሁለትዮሽ ስምምነት መፈራረማቸው ይታወሳል።

ዩንቨርሲቲው ቀደም ሲል በመስኩ ባቀደው የሰው ሃብት ልማት በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በኩል ባደረገው ግንኙነት በአለም አቀፍ ደረጃ ግንባር ቀደም ከሆነው ከሩሲያ ሮሳቶም ኒውክሌር ኃይል ባገኘው ድጋፍ ከአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ አራት ተማሪዎች ወደ ሩሲያ ሃገር ሞስኮ ኢንጅነሪንግ ፊዚክስ ኢንስቲቲዩት ሄደው በመስኩ የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርታቸውን ከመስከረም 19 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ እየተከታተሉ ይገኛሉ። እንዲሁም ሌላ አንድ ተማሪ ከኮርያ ሲኦል ናሽናል ዩኒቨርሲቲ ባገኘነው ድጋፍ የ2ኛ ዲግሪ ትምህርቱን በዚያው ዩኒቨርሲቲ በመካታተል ይገኛል።

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ልህቀት ማዕከላት ዳይሬክተር ዶክተር ጌታቸው አዳም እንደገለጹት፤ዩኒቨርሲቲው አገሪቱ በኒውክለር ኃይል ልማት የያዘችውን እቅድ ለማሳካት የሚያግዝ በዘርፉ ምርምሮችን ለማካሄድ እና የሰለጠነ የሰው ኃይል በማብቃት ላይ ትኩረት ያደረገ አላማ ይዞ በመስራት ላይ ይገኛል።

በዩኒቨርሲቲው ከተከፈቱት ስምንት የልህቀት ማዕከላት ውስጥ የኒውክለር ሪአክተር ቴክኖሎጂ የልህቀት ማዕከል አንዱ መሆኑን አንስተው ማእከሉንም በዘርፍ ከፍተኛ ልምድ ያላቸውን ኮርያዊ ፕሮፌሰር ዶንግሶንግ ሶንን በመቅጠር በርካታ ስራዎችን እየከወነ ይገኛል። በዩኒቨርሲቲው የኒውክለር ሪአክተር ቴክኖሎጂ ልህቀት ማዕከል የህንጻ ግንባታው ተጠናቆ አስፈላጊ የምርምር እና የማስተማሪያ መሳሪያዎችን ለማሟላት እየተሰራ መሆኑንም ተናግረዋል።

የኒውክለር ሳይንስና ኢንጂነሪንግን የማስተርስ መርሃ ግብርን ለማስጀመር በዘርፍ ልምድ ካላቸው የኮሪያ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ አድቫንስድ ኢንስቲቲውት (KAIST)፣ የኮሪያ አቶሚክ ኢነርጂ ሪሰርች ኢንስቲቲውት (KAERI) እና ኮርያ ኒውክሊየር ኢንተርናሽናል ኮኦፕሬሽን ፋውንዴሽን (KONICOF) ጋር በትብብር እየሰራ መሆኑን ገልፀው፤ ዩኒቨርሲቲው በመጀመሪያው መርሃ-ግብሩ አምስት ተማሪዎች መቀበሉን አስረድተዋል።

የልህቀት ማእከሉም የሚቀበለውን የተማሪ ቁጥር እና የፕሮግራም ብዝሃነት ለማሳደግና በሶስተኛ ዲግሪ ትምህርቱን በመስጠት አገሪቱ በዘርፉ የሚያስፈልጋትን የሰው ኃይል ለማሟላት አቅዶ እየተሰራ ነው ብለዋል። በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲው በዘርፉ ጥራት ያለው ትምህርትን እና ምርምርን ለማካሄድ ከሩሲያ እና ኮሪያ ካሉ የትምህርት እና ምርምር ተቋማት ጋር በትብብር እየሰራ መሆኑን አስረድተዋል። በመጨረሻም ዩኒቨርሲቲው ለልህቀት ማእከሉ የሚመጥኑ የምርምር ግብአቶችን ለማሟላት የቅድመ አዋጭነት ጥናት እያካሄደ መሆኑንም ጠቅሰዋል።

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# እንቁው ዲፕሎማት...

ከገጽ 3 የዞረ

አያምኑም የሚል መግለጫም በጋራ አወጡ። መሪዎቹን አስማምቶ ማምጣት በጣም የከበደ ሥራ እንደነበር የሚናገረው መኮንን በብዙ አጋጣሚዎችም አባቱ ከተማ የዲፕሎማሲ ክህሎታቸውን በመጠቀም ነገሮችን እንዳሳኩ ያስታውሳል።

ከተማ በየሀገራቱ ሲዞሩ “ወደ ሀገሬ ምንም ሳልይዝ አልሄድም፤ ንጉሡ አያስገቡኝም” የሚሉ ማባበያዎችን ይጠቀሙ እንደነበር የሚናገረው መኮንን፤ ከተማ የቱኒዚያውን ፕሬዚዳንት ያግባቡበትን መንገድ ለይቶ ይጠቅሳል። ፕሬዚዳንቱ የሁለቱ ቡድኖች የጋራ አቋም ሳይኖር እንዴት አንድ ላይ እንሰበሰባለን የሚል የእምቢታ ምላሽ ሲሰጧቸው በምላሹም “አፄ ኃይለሥላሴ ያለርስዎ ይህ ስብሰባ አይካሄድም” እንዳሏቸው ይናገራል።

በወቅቱ አፄ ኃይለሥላሴ የነበራቸው ቦታ ከፍተኛ ስለነበርም የቱኒዚያው ፕሬዚዳንት እሺ ብለው መጡ። ያ ታሪካዊ ስብሰባ ሊደረግም በቃ፤ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትም ተበሰረ። ነገር ግን ሒደቱ ቀላል አልነበረም። ሁለት የተለያዩ እሳቤዎችን ይዘው የመጡ ቡድኖችን አንድ ላይ መምጣት ቀላል አልነበረም፤ የተወሰኑ አለመግባባቶች ቢፈጠሩም የነበረው ድባብ በጣም የተለየ እንደነበር አቶ ከተማ ለልጃቸው ለመኮንን ነግረውታል። “እንዲህ አይነት ስሜት አፍሪካ ውስጥ ተፈጥሮ አያውቅም” ብለው አባቱ አጋጣሚውን ገልፀውለታል።

በመቀጠልም የአፍሪካ ፖሊሲዎችን ማርቀቅ፣ የድርጅቱ ፀሐፊ እንዲሁም ዋና ጽሕፈት ቤት የት ይሁኑ የሚሉ አንገብጋቢ ጥያቄዎች ነበሩ። በከተማ አመራርነት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሁለቱን አንጃዎች ፖሊሲና ሌሎች ሀሳቦችን ጨምረው አቀረቡ፤ ፖሊሲዎቹ ላይ አንዳንድ አለመስማማቶች ቢፈጠሩም ሰነዱ ተፈረመ።

ከተማ ሥራቸው አላለቀም ለኢትዮጵያ የነበረው ጥሩ ስሜት እያለ ኢትዮጵያ የድርጅቱ ጽሕፈት ቤት መቀመጫ ትሁን የሚል ሀሳብ አቀረቡ። በፍጥነት ከአመራሩ “አይቻልም” የሚል ምላሽ ተሰጣቸው። ምክንያቱ ደግሞ “ከተማ የራሱን ዝናና ስም እየገነባ ነው፤ “ብለው ንጉሡን የሚመክሩ ስለነበሩ እንደሆነ መኮንን ይናገራል። የተፈራው አልቀረም ትንሽ ቆይቶም ፈረንሳይኛ ተናጋሪ ሀገራት የድርጅቱ መቀመጫ ዳካር እንድትሆን መስማማታቸው ተሰማ።

ኢትዮጵያ ድርጅቱን ለመመሥረት ይህንን ያህል ለፍታ አመድ አፋሽ መሆኗ ንጉሡን አስደነገጣቸው። ከሴኔጋል ሌላም ናይጄሪያ ያላትን ትልቅነት ተጠቅማ እዚህ መሆን አለበት የሚል ክርክርም ጀምራ ነበር። የሃገራቱ እሰጣገባ ብቻ ሳይሆን “ኢትዮጵያን አትምረጡ” የሚል ቴሌግራም እየተሰራጨ እንደነበር የሶማሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለከተማ አሳዩዋቸው። “ኢትዮጵያና ሶማሊያ መካከል ግጭት እያለ ሚኒስትሩ ያንን ማድረጋቸው ለአባቴ በሕይወቱ ሙሉ የሚያስደንቀው ጉዳይ ነበር። ቢጋጩም የሶማሊያ ድጋፉ ለኢትዮጵያ ነበር” ይላል ልጃቸው መኮንን።

በመቀጠልም ኢትዮጵያ እንድትመረጥ የማግባባቱ ሥራ /ዘመቻ/ ተጀመረ። በተለይም ለጊኒ እናንተ ኢትዮጵያን መቀመጫ ካደረጋችሁ የጸሐፊውን ቦታ እንሰጣችኋለን የሚል ሃሳብን እንዳቀረበ መኮንን ይናገራል። በመጨረሻም ከናይጄሪያ በስተቀር ኢትዮጵያ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጽሕፈት ቤት መቀመጫ እንድትሆን ሀገራቱ ድምፃቸውን ሰጡ። “ብዙዎች እንደሚሉት በአፄ ኃይለሥላሴ ምክንያት አይደለም አዲስ አበባ የተመረጠችው፤ ከብዙ ማግባባት፣ ክርክርና ፍጭቶች በኋላ ነው የድርጅቱ ጽሕፈት ቤት አዲስ አበባ ሊሆን የቻለችው።”

ለዘመናት በተለያዩ መድረኮች ላይ ኢትዮጵያን የወከሉት አቶ ከተማ የተባበሩት መንግሥታትን ጨምሮ፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከመሆናቸው በፊት በተለያዩ ኃላፊነት አገልግለዋል። የትምህርት ጉዟቸው ሀ ብሎ የተጀመረው ኬንያ ነበር። ምክንያቱም ጣሊያን ኢትዮጵያን ሲቆጣጠር በሰባት ዓመታቸው ወደ ጅቡቲ ለመሰደድ ተገደዱ።

ትንሽ ጊዜ ጅቡቲ ቆይተውም ጉዟቸውን ከአጎታቸው ጋር ወደ ኬንያ አደረጉ። በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ስር በነበረችው ኬንያም ስደተኞች ከሀገሬው ተማሪ ጋር አብሮ መማር ስለማይቻል ለኢትዮጵያውያን ስደተኞች ተብሎ በተከፈተውና በቢትወደድ ዘውዴ ገብረ ሕይወት ኃላፊነት በሚመራው ትምህርት ቤት ትምህርት ጀመሩ። ኢትዮጵያ ነፃነቷን ስትቀዳጅ ደግሞ ወደ ጋራ ሙለታ ተመለሱ።

ያኔም ትምህርታቸውን የመቀጠል ፅኑ ፍላጎት እንደነበራቸው መኮንን ይናገራል። ለዚህ ደግሞ የአጋጣሚ በር ተከፈተላቸው። ንጉሡ የተለያዩ አካባቢዎችን በሚጎበኙበት ወቅት ጋራ ሙለታን ሲጎበኙ በአካባቢው ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ልጆች አሉ ምን ይደረግ? ብለው ሲጠየቁ አዲስ አበባ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምጣት እንደሚችሉ ምላሽ ተሰጣቸው። መኮንን እንደሚናገረው አዲስ አበባ ሄደው ወዲያው ትምህርት ቤት የሚገቡ መስሏቸው የነበረ ቢሆንም ሲደርሱ አናስገባም የሚል ምላሽ ተሰጣቸው። የሚያድሩበትም ሆነ የሚበሉት አልነበራቸውም፤ በጊዜው “ሰው ለሰው አዛኝ በመሆኑ” ይላል በአካባቢው የነበሩ ወታደሮች መጠጊያ ሆኗቸው። ሥራም እየሠሩ ትንሽ ከቆዩ በኋላ ነገሩ በወቅቱ የጦር ሠራዊት ኃላፊ ለነበሩት ጄኔራል መርዕድ መንገሻ በመነገሩ በሳቸው ምክንያት ትምህርታቸውን ሊጀምር እንደቻሉ ይናገራል።

የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች የመኳንንትና የሹማምንት ልጆች በመሆናቸው ከፍተኛ ልዩነት ይታይበት የነበረ ሲሆን አባቱ የነገሩትንም መኮንን እንዲህ ያስታውሰዋል። “ንጉሡ በየጊዜው እየመጡ ተማሪዎቹን ይጎበኛሉ። መምህሩም ስም በሚጠራበት ወቅት ከስማቸው ፊት ደጃዝማች፣ ልዑል እንዲሁም ሌሎች ሹመቶች ነበሩ። ጃንሆይም ልጆቹ በእኩልነትና ያለምንም ተፅዕኖ ትምህርታቸውን እንዲማሩ ቅጥያው እንዲሰረዝ አዘዙ” ይላል።

በመቀጠልም ለከፍተኛ ትምህርት ወደ አሜሪካ ሚቺጋን ሆፕ ኮሌጅ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ለማጥናት ያቀኑ ሲሆን፤ የማስተርስ ዲግሪያቸውንም በቦስተን ዩኒቨርስቲ በተመሳሳይ ትምህርት ተመርቀዋል። አሜሪካ ሲደርሱ ከፍተኛ ዘረኝነት ያጋጠማቸው ሲሆን፤ “ውሾችና ጥቁሮች አይፈቀድም” የሚሉ መልዕክቶች እንዲሁም የነበረው የዘረኝነት ሁኔታ አፍሪካዊነታቸውን ብቻ ሳይሆን የፓን አፍሪካዊነት ፅንሰ ሀሳባቸውንም በከፍተኛ ሁኔታ ያሳደገው ነገር እንደሆነ መኮንን ይናገራል። ምንም እንኳን የፒኤችዲ ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ቢጠየቁም ቤተሰቤን እረዳለሁ ብለው ተመለሱ። ከዚያም ሀገራቸውን በውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነትና በተለያዩ ኃላፊነቶች አገለገሉ።

ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ከዙፋናቸው ተወግደው ዓመታት ካለፉ በኋላ አምባሳደር ከተማ « ... የአፍሪካ የመጀመሪያዎቹ መሪዎች ትልቁ ችግር ... በእኛም ላይ ደረሰ፡፡ መሪዎች በሥልጣን ላይ በሚቆዩበት ጊዜ ተተኪውን ሥርዓትና ሰው ሳያዘጋጁ ጊዜው ይደርስና ሀገራቱ ስጋት ላይ ይወድቃሉ፡፡ የዴሞክራሲን መርሆች መከተል ሲቻል፣ ሥልጣን የሰፊው ሕዝብ መሆኑ ሲታወቅና ሕዝብም መብቶቹን እያወቀ ሲሄድ ነው ወደ ሌላ መንግሥት በጤና መዛወር የምንችለው...» ብለው ተናግረዋል፡፡

ይሁን እንጂ ንጉሠ ነገሥቱ የአምባሳደር ከተማን ምክር ከመስማት ይልቅ አምባሳደር ከተማን ከውጭ ጉዳይ ወደ ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ቱሪዝም ሚኒስትርነት አዛወሯቸው። አምባሳደር ከተማ የገመቱት አልቀረም ... ከደብዳቤው ሦስት ዓመታት በኋላ የ1966ቱ አብዮት መጥቶ ንጉሠ ነገሥቱን በላቸው፡፡

ወታደራዊው መንግሥት ሥልጣን ሲይዝ አምባሳደር ከተማ ታሰሩ፡፡ ከስምንት ዓመታት እስራት በኋላ ተፈቱ፡፡ ከዚያም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የዓለም የምግብ ፕሮግራም የምሥራቅ አፍሪካ ዳይሬክተር፣ የአፍሪካ ቀጣና ልዩ አማካሪና ተወካይ ሆነው አገልግለዋል፡፡ አምባሳደር ከተማ በ1952 ዓ.ም ከወይዘሮ ራሔል ስነ ጊዮርጊስ ጋር ጋብቻ መስርተው አራት ልጆችን አፍርተዋል።

ወይዘሮ ራሔል ስለባለቤታቸው ባሕርይ ሲናገሩ « ... ከሁሉም ሰው መግባባት የሚያስችል ተፈጥሮ ያለው ሰው ነበር ...» ይላሉ፡፡ ልጃቸው አቶ መኮንን ከተማ ይፍሩ በበኩሉ « ... አባቴ የነበረበትን ማንነቱን አይረሳም፡፡ በሰው እኩልነት ያምናል ...» ብሏል፡፡አምባሳደር ከተማ እጅግ ደማቅ ለሆኑት አኩሪ ተግባሮቻቸው የኢትዮጵያን ጨምሮ የበርካታ አገራትን (የእንግሊዝ፣ የፈረንሳይ፣ የሶቪየት ኅብረት፣ የኢጣሊያ፣ የዩጎዝላቪያ፣ የሴኔጋል፣ የኬንያ፣ የናይጀሪያ፣ የጋና፣ የዛየር፣ የግብፅ፣ የብራዚል፣ የሜክሲኮ፣ የካናዳ፣ የጃፓን የኢንዶኔዥያ ...) ኒሻኖችን ተሸልመዋል፡፡

አንጋፋ ኢትዮጵያውያንና የውጭ አገራት ዲፕሎማቶችም ስለአምባሳደር ከተማ አስደናቂ ተግባራት በተደጋጋሚ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። «... ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴና አቶ ከተማ ይፍሩ በሁለቱ ጎራ ተሰልፈው የነበሩ መሪዎችን በማግባባት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እውን እንዲሆን አድርገዋል ...» የቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዚዳንት ታቦ ምቤኪ

«... አቶ ከተማ ይፍሩን ከአፍሪካ አንድነት ድርጅት ታሪክ መለየት አይቻልም፡፡ በጣም ብዙ ደክመዋል። የአፍሪካ መሪዎች በጃንሆይ ሰብሳቢነት ሲሰባሰቡ ጀምሮ መሪዎችን በማነጋገርና በማግባባት ከፍተኛ ተሳትፎ ነበራቸው፡፡ የሞኖሮቪያና የካዛብላንካ ቡድኖች ተፈጥረው የሃሳብ ልዩነት በነበረበት ወቅት አምባሳደር ከተማ በየሀገራቱ እየዞሩ ከመከፋፈል ይልቅ አንድነት እንደሚሻልና የቡድኖቹን ሃሳቦች በውይይት መፍታት እንደሚቻል ያስረዱ ነበር፡፡

በጣም ወደ ግራ ያዘነበሉ የአፍሪካ መሪዎችንና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮችን በማግባባት ያበረከቱት አስተዋፅዖ እጅግ ከፍተኛ ነበር ።» አንጋፋው ጋዜጠኛ፣ የታሪክ ጸሐፊና ዲፕሎማት አምባሳደር ዘውዴ ረታ«... አምባሳደር ከተማ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ «ብሔራዊ ጥቅምን ያስከበረና ገለልተኛ የሆነ» እንዲሆን ብዙ ጥረት አድርገዋል ... ከኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች መካከል የአፍሪካ የነፃነት ታጋዮችን በመደገፍና ወደ ነፃነት የሚያደርሱ መንገዶችን በማመቻቸት እንደአምባሳደር ከተማ ይፍሩ ታላላቅ ተግባራትን ያከናወነ ሰው የለም ...» የቀድሞው የመከላከያ ሚኒስትርና በአሜሪካ የኢትዮጵያ አምባሳደር አያሌው ማንደፍሮ፤ አምባሳደር ከተማ ጥር 6 ቀን 1986 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡

በኑዛዜያቸውም የሚከተለውን መልዕክት አስቀምጠው አልፈዋል ...«በራሴ በኩል አገሬን በንጹሕ ልቦና አቅሜና የጊዜው ሁኔታ በሚፈቅደው መጠን ከማገልገል በስተቀር የፈፀምኩት ወይም ያደረስኩት አንዳችም በደል ያለመኖሩን ስለማምንና ስለማውቅ ምንጊዜም ቢሆን ሕሊናዬ ፍጹም ንጹሕ ነው። የፈፀምኩት በደል ቢኖር ከተራ ገበሬ ቤተሰብ ተወልጄ በችሎታዬና በድካሜ ተወዳድሬ በቁጥር አነስተኛ በሆኑ ክፍሎች በሞኖፖል ተይዞ ለነበረው ከፍተኛ የሥራ ቦታ ራሴን ብቁ አድርጌ መገኘቴ ብቻ ነው፡፡

የእኔ ወንጀል ኢትዮጵያ ሀገሬ በሰጠችኝ ዕድል ተጠቅሜ የእኔ ብጤ፣ ከድሃ ቤተሰብ የሚወለድ ዕድሉ ከተሰጠው ከማንም የማያንስ መሆኑን በሥራ ማስመስከሬ ብቻ ነው፡፡ ሥራ ላይ በነበርኩበት ዘመን በተለይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በነበርኩበት ጊዜ የፈጸምኳቸው ሥራዎች በተለይ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መመሥረትና ዋናው መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ላይ እንዲሆን ያደረግሁት ለኔ ምንጊዜም የሚያንጸባርቅና ሐውልት ስለሆነ ለባለቤቴንም ለልጆቼም የሚያኮራቸው ነው፡፡»

ከኢትዮጵያ አልፈው ለአፍሪካ ጭምር ኩራትና ባለውለታ ለሆኑት ለአምባሳደር ከተማ ይፍሩ ስም መታወሻ የሚሆን ተግባር ኢትዮጵያ ውስጥ አለመከናወኑ ብዙዎችን አስገርሟል፤ አሳዝኗልም ይሉናል፤ “ከተማ ይፍሩ – የተዘነጋው ታላቁ የአፍሪካ ኅብረት ኩራትና ባለውለታ!!!” በሚል ርዕስ ከአራት ዓመት በፊት “አዲስ ዘመን”ጋዜጣ ላይ ያስነበቡን አንተነህ ቸሬ የተባሉ ጸሐፊ፡፡

ሻሎም ! አሜን።

ማህበራዊ


# የሕይወት ገጽታ

# አዲስ ዘመን ጋዜጣን በብስክሌት ማደል የጀመሩት የሀገር ባለውለታ

አስመረት ብሥራት

በሀገሪቱ የሕትመት ሚዲያ ታሪክ ግንባር ቀደም የሆነው የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት መቋቋም መሠረት የሆነው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ሕትመት መጀመር ነው። ስሙም የተወሰደው ንጉሡ ከስደት መመለሳቸውን አስመልክቶ በሚያዚያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ባደረጉት ንግግር ነው። "ዛሬ በኢትዮጵያ አዲስ ዘመን ተጀመረ" ሲሉ ከተናገሩት አረፍተ ነገር ላይ መሆኑን የታሪክ መዛግብት ያትታሉ።

አዲስ ዘመን ሲጀመር አርበ ጠባብ ሆኖ ቁመቱ 42 ሴንቲ ሜትር ስፋቱ ደግሞ 31 ሴንቲ ሜትርም ነበር። ዓምዱም በሦስት የተከፈለ ሲሆን ይህን የብራና ጽሑፎች ተፅዕኖ ሊሆን እንደሚችል ታሪክ ሰናጆች ያብራራሉ። የጋዜጣው ስያሜ የግዕዝን የአፃፃፍ ሥርዓት በጠበቀ መልኩ በሥርዓተ ነጥብ ታጅቦ ይፃፍ ነበር። ድርብ ሰረዝ ለእርሱ መጠቀም የተጀመረው ቆይቶ ነበር። በጋዜጣው ላይም ርዕሰ አንቀፅና የዋና አዘጋጅ ስም ቆይቶ እንደመጣም የተገኘው መረጃ ያመላክታል።



አቶ ዕቁባይ አዲስ ዘመንን በዚህ መልኩ ያሰራጩ ነበር

ጋዜጣውን የሚመራው የጋዜጣና ማስታወቂያ ጽሕፈት ቤት እየተባለ የሚታወቀው ተቋም እንዳሁኑ መሐል አራት ኪሎ ላይ ሳይከትም በፊት ሰባራ ባቡር አካባቢ ነበር። ጋዜጣው ሲመሠረት እውነት፤ አገልግሎትና ረዳትነት የሚሉ ዓላማዎችን ይዞ መነሳቱን ያገኘነው የታሪክ ድርሳን ያትታል። በወቅቱ የነበረው የጋዜጣው መሸጫ ዋጋ ሦስት የጣሊያን ሊሬ ሲሆን አሁን የአንድ ጋዜጣ ዋጋ አስር ብር ላይ መድረሱ ይታወቃል።

በወቅቱ አብዛኛው የጋዜጣው የጽሑፍ ይዘት ስለ ንጉሠ ነገሥቱ ክብርና ስለሀገር ፍቅር የሚሰብክ ሲሆን ከጥቂት የኅትመት ቆይታዎች በኋላ የግሪክ ፈላስፋዎችን ሥራዎች በተከታታይ በማተም ሕዝቡ እንዲያውቅና እንዲመራመር ሰፊ ጥረት ሲያደርግ እንደቆየም ታሪክ ያወሳል። በወቅቱ በጋዜጣው ላይ የዜናም ሆነ የርዕሰ አንቀጽና የአስተያየት ገጽ ያልነበረ መሆኑንም ታሪክ ይናገራል።

ዘመን ዘመንን እየወለደ ሲሄድ በርካታ ዋና አዘጋጆችን ይዞ ያለፈ የታሪክ መዝገቡ አንጋፋው አዲስ ዘመን ጋዜጣ የመጀመሪያው ዋና አዘጋጅ የነበሩት ሰው ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ነበሩ። እኚህ ሰው በወቅቱ የታወቁ የቤተ ክህነት ሊቅ ነበሩ። እኚህ ሰው ዋና አዘጋጅ ብቻ ሳይሆኑ ከ1933 እስከ 1953 ዓ.ም ለሃያ ዓመታት በዋና አዘጋጅነት ያገለገሉ ጠንካራ ሰው ነበሩ።

ወልደ ጊዮርጊስ በጋዜጣው ላይ ከአራሚ ጀምሮ፤ በወቅቱ አጠራር የዜና ሠራተኛ፤ አዘጋጅ፤ ዋና አዘጋጅ በመሆን ለዓመታት አገልግለዋል። ከ1936 ዓ.ም ጀምሮ ለኅትመት የበቃው የዘኢትዮጵያን ሄራልድም አማርኛ ለማይችሉ ለውጭ ሀገር ዜጎች እንዲያነቡት የተዘጋጀ ነበር። ጋዜጣው የሀገሪቱን ማኅበራዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ለውጭ ማኅበረሰብ በማስተዋወቅ ረገድ የላቀ አስተዋፅዖ እንደ ነበረው መረጃው ያመለክታል።

በርካታ ጋዜጦችና መጽሔቶች በተለያዩ ጊዜያቶች ቢታተሙም ከአዲስ ዘመንና ከኢትዮጵያን ሄራልድ በስተቀር ሌሎቹ በመንግሥት ለውጦችና ከእነሱ ጋር ተከትሎ የመጣው የርዕዮተ ዓለም ፍልስፍና ምክንያት ብዙም ሳይቀጥሉ ቀርተዋል። አዲስ ዘመን መታተም ከጀመረ ከአስራ ስምንት ዓመታት በኋላ እለታዊ የሆነ ሲሆን ሰኞ ሳይታመም በሳምንት ስድስት ቀን ብቻ እየታተመ ለረዥም ዓመታት ቆይቷል። አዲስ ዘመን ጋዜጣ ሰኞንም ጨምሮ በሳምንት ለሰባት ቀናት መታተም የጀመረው በ1993ዓ.ም ጀምሮ ነበር። የአፍሪካ ኢኮኖሚክስ ኮሚሽን አዲስ አበባ ውስጥ መቋቋሙን ተከትሎ ዘኢትዮጵያን ሄራልድም ከ1951 ዓ.ም ጀምሮ እለታዊ ሆኗል።

ከኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ማኅበር በተገኘው ማስረጃ መሠረት ድርጅቱ የሚያሳትማቸው ጋዜጦች በ1997 ዓ.ም የነበራቸው ስርጭት፤ ዘኢትዮጵያ ሄራልድ 6500 ቅጂ፤ አል-ዓለም ጋዜጣ በየሳምንቱ 2500 ቅጂ፤ በሪሳ ጋዜጣ በየሳምንቱ 2000 ቅጂ ነበረው።

ይህ ተቋም ጋዜጦችንና መጽሔቶችን ከማሳተም ባለፈ በሀገሪቱ አንቱ የተባሉ ስመጥር ደራሲያንን በማፍራት አቻ ያልተገኘለት እንደ ነበር የታሪክ መዛግብት ያብራራሉ። በወቅቱ ጉምቱ ጸሐፍት መካከል አቤ ጉበኛ፤ ብርሃኑ ዘርሁን፤ በዓሉ ግርማ፤ ጳውሎስ ኞኞ፤ ከበደ ሚካኤል፤ ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ፤ ነጋሽ ገብረ ማሪያም፤ የሺጥላ ኮከብ ፤ ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር፤ ደምሴ ፅጌ፤ ታደለ ገድሌ፤ አበረ አዳሙ እና ሌሎችም በርካታ ደራሲያን የፈሩበት በቀጣይም የሚፈሩበት ታላቅ ተቋም ነው።

በዚህ ታላቅ ተቋም ውስጥ ከጋዜጠኞችም በላይ እነዚህን ታዋቂ የሕትመት ወጤቶች አንባቢያን ዘንድ ማልደው በትኩሱ መረጃን ለማድረስ የሚታትሩ ጋዜጣ አከፋፋዮች ይገኙበታል። ከእነዚህ ጋዜጣ አዳይ ሰዎች መካከልም የእድሜያቸውን አጋማሽ በተቋሙ ያገለገሉ እና የሀገር ባለውለታ የሆኑ አንድ ሰውን ለዛሬ የሕይወት እንዲህ ናት ዓምድ ይዘንላችሁ ቀርበናል መልካም ቆይታ።

ገና በልጅነት እድሜያቸው ኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ውስጥ ሲሠሩ የነበሩ ዘመዳቸው ተከትለው ወደ ተቋሙ ብቅ ያሉት እኝህ ሰው "ይችን ጋዜጣ እዛ አድርሰህ ና፤" እየተባሉ ሲላኩ አደጉ። ጉልበታቸው ሲጠና ጠንካራ ጎረምሳ ሲሆኑ ደግሞ ጋዜጣውን በሳይክል ይዘው በመዞር በከተማዋ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ የሚደርስባቸው ቦታዎች በሙሉ ያደርሱ ነበር።

በእጅ ጋዜጣ እየተሰጣቸው እዚህና እዛ ሲላኩ የነበሩት ሰው በሳይክል ጋዜጣ አድርሱ ሲባሉ በፍጥነት ለየተቋማቱ በማድረሳቸው የበላይ ኃላፊዎችን ይሁንታን አግኝተው ገና በአስራ አምስት ዓመታቸው ጋዜጣን ማከፋፈል ሥራቸው ሆኖ ኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትን ተቀላቀሉ። እኚህ ሰው በጡረታ እስከተገለሉባት ቀን ድረስ በድርጅቱ ለአራት አስርተ ዓመታት ያለማቋረጥ አገልግለዋል።

አቶ ዕቁባይ ዮሴፍ ወልደ ኪዳን ይባላሉ። በ1940 ዓ.ም በትግራይ ዓድዋ ከተማ ነበር የተወለዱት። ከአባታቸው ከአቶ ዮሴፍ ወልደኪዳንና ከእናታቸው ዘውዴ ውነህ የተወለዱት እኚህ ሰው እንደማንኛውም የትግራይ አካባቢ ሕፃን በቤተክህነት ደጅ ነበር ከፊደል ጋር የተዋወቁት።

በቄስ ትምህርት ተምረው ፊደል የለዩ ቢሆነም ገና በአፍላ እድሜያቸው ከተወለዱባት ከዓድዋ አንድ የቅርብ ዘመዳቸውን ተከትለው ወደ አዲስ አበባ መጡ። ከትውልድ ቀያቸው ከወጡ በኋላ ያመጧቸውን ሰው እግር እግር እየተከተሉ የሚሠሩትን ማየት፤ ያዩትን ለመሞከር መታተር ጀመሩ። በዚህም የሞከሩት ቶሎ የሚገባቸው ንቁ አዕምሮ ያላቸው አፍላ ወጣት ሆኑ።

በመላላክ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትን የተዋወቁት እኚህ ሰው በ1955 ዓ.ም ብስክሌት በመንዳት ጋዜጣ የማዞር ሥራ ላይ በመሰማራት የመጀመሪያ የቅጥር ፊርማቸውን አስቀምጡ። ወጣቱ ዕቁባይ በወቅቱ የአስራ አምስት ዓመት አፍላ ወጣት ሆነው ነበር ድርጅቱን የተዋወቁት።

በመቀጠል ሞተር ሳይክል የመንዳት የሚያስችል ሥልጠና ወስደው በሞተር መጀመሪያ ሲሠሩት የነበረውን የጋዜጣ ስርጭት በበለጠ ቅልጥፍና ያካሂዱት ጀመር። ከሞተር ብስክሌት ቀጥሎ ሾፌር በመሆን በመሥሪያ ቤቱ አስፈላጊ የሆኑ ሥራዎችን በሙሉ ሲሠሩ ቆይተዋል። በተቋሙ የተመለከትነው የቅጥር ማኅደር እንደሚያመለክተው እስከ 1977 ዓ.ም ድረስ በሹፍርና ሲያገለግሉ ቆይተዋል።

ከጥቅምት 16 ቀን 1977 ዓ.ም እስከ መጋቢት 16 ቀን 1978 ዓ.ም ድረስ በተጠባበቂ የሰርቪስ ተቆጣጣሪነት አገልግለዋል። ሙሉ የሥራ ሕይወታቸውን በድርጅቱ ያደረጉት እኝህ ሰው ከመጋቢት 16 ቀን 1978 ዓ.ም እስከ ሚያዚያ 18 ቀን 1978 ዓ.ም ድረስ በንብረት ክፍል ሠራተኝነት አገልግለዋል። ከሚያዚያ 19 ቀን 1978 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 1986 ዓ.ም ዳግም በሾፌርነት በከፍተኛ ትጋት ሲያገለገሉ ቆይተዋል።

በ2001 ዓ.ም በጡረታ እስከተገለሉበት ጊዜ ድረስ በሰርቪስ ክፍል ተቆጣጣሪነት፤ የትራንስፖርት ክፍል ኃላፊና ሌሎች ትራንስፖርት ነክ በሆኑ ኃላፊነቶች ላይ ሲያገለገሉ መኖራቸውን የግል ማኅደራቸው ያስረዳል። በዚህ ሁሉ የአገልግሎት ዘመናቸው ጋዜጣውን ከማሰራጨትም በላይ ጋዜጠኞችን ለዘገባ ይዞ መውጣት ተቀዳሚ ሥራቸው እንደነበር አብረዋቸው የሠሩ አንጋፋ ጋዜጠኞች ይመሰክራሉ።

**አቶ እቁባይ በሥራ ባልደረቦቻቸው አንደበት**

**አቶ ተሾመ ቀዲዳ የበሪሳ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ባልደረባ**

" ለረዥም ዓመታት በበሪሳ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ውስጥ አገልግያለሁ። ለሠላሳ ዓመታት የዘለቀ ትውውቅ ያለን ሲሆን አቶ ዕቁባይ ከሾፌርነት እስከ የተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ሲያገለግሉ አውቃለሁ። በሥራ ላይ በነበሩበት ወቅት አቶ ዕቁባይ ከሁሉም ሰው ጋር ጤናማ ግንኙነት የነበረው አይነት ሰው ነበር።

አቶ ዕቁባይ እንዳጫወተኝ ከሹፍርና በፊት ለዓመታት በብስክሌት በየቋማቱ ጋዜጣ ያድል እንደ ነበረ ነው። አብረን በሠራንባቸው ዓመታት በጣም መልካም ሰው ነበር። የጋዜጠኝነት የሥራ ባሕሪን በመረዳት በአግባቡ ሲያገለግል የኖረ ሰው ነው። እኔ ስፖርት ጋዜጠኛ ስለሆነኩኝ እስታድየም በማመሽበት ወቅት ያለ ምንም ቅሬታ ሰብሰቦን በየቤታችን በየምሽቱ ካደረሰን በኋላ ነበር እሱ የሚያርፈው።

ለአቶ ዕቁባይ አለቃም ሆነ የበታች ሠራተኛ እኩል ቦታ ነበረው። ቀድሞ አገልግሎቱን የጠየቀው የበታች ሠራተኛ ከሆነና አንድ መኪና ብቻ ካለ ቅድሚያ የሚያገኘው ቀድሞ የሚመጣው መሆኑ ልዩ ያደርጋቸዋል። አቶ ዕቁባይ መልካምነቱ ማሳያ የሚሆነው ጡረታ በወጣበት ወቅት ሙሉ የመሥሪያ ቤቱ ሰው ነበር ታላቅ ፕሮግራም አዘጋጅቶ የሸኘው።

ከዕቁባይ ከሥራ ባልደረባነት አልፎ ማኅበራዊ ትስስራችን የጠበቀ ነበር። ያ ማለት ለበዓላት መጠራራትን፤ ለችግር መደራረስን፤ አብሮ ማምሸትንና ቤተሰብ እስከ ቤተሰብ መተሳሰር ድረስ መልካም ግንኙነትን መፍጠር የሚያውቅበት ታላቅ ሰው ነበር።" ሲል አቶ ተሾመ ቀዲዳ ትውስታውን አካፍሎናል፡፡

**ሰለሞን ጥዑመ ልሳን የቀድሞ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ባልደረባ**

"ከአቶ ዕቁባይ ጋር የተዋወቅነው እኔ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## አዲስ ዘመን ጋዜጣን በብስክሌት...

ከ6ኛ ገጽ የዞረ

የጋዜጠኝነት ሥራን ስቀላቀል ጀምሮ ነው። ሹፌርም ሆኖም ሆነ የሥራ ክፍሉ ኃላፊ በነበረበት ጊዜዎች ጥሩ ግንኙነት ነበረን። በአዲስ አበባ ከተማና በመስክ ሥራዎች ጋር አብረን ተንቀሳቅሰናል፤ አቶ ዕቁባይ ሥራዎችን በሠላማዊ መልኩ መሥራት የሚወድ ለእያንዳንዱ ሥራ ኃላፊነትን የሚወስድ ሰው ነበር። የጋዜጠኝነትን ሥራ በአግባቡ ተረድቶ የሚሠራ ሁሉንም እንደ አመሉ ተቀብሎ ባለው ውስን አቅም ለሁሉም የሚያደስ ሰው ነበር።

እንዳለ መታደል ሆኖ የሚዲያ ተቋማት የሚዋከቡት በትራንስፖርት ክፍል ኃላፊዎች ነበር። እንደ እቃ ቀላል አድርጎ ሰውን የመመልከት ሁኔታ ይታያል። ዕቁባይ ጋር ግን ያ የለም። ሥራ የሚያግዝ በፈገግታ የተሞላ የሥራ ቀናትን በደስታ ለማሳለፍ የሚያስችል ስሜት የሚፈጥር አይነት ጥሩ ሰው ነበር።

ሰው ቢታመም ጠያቂ፤ ለቅሶ ቢኖር ቀድሞ ደራሽ፤ የእሱን እርዳታ ለፈለጉ ሁሉ እጁ የማይታጠፍ፤ ሰጥቶ የማይጠግብ፤ አብልቶ ሰው የጠገበ የማይመስለው ሰው ነው፤ በኃዘን ሁሉንምን ሠራተኛ በየተራ እየወሰደ የማኅበራዊ ትሰስሩ ተቋም ውስጥ እንዲጠብቅ የሚያደርግ ሰው ነበር።

በመስክ ሥራ ላይ በአግባቡ ሥራው እንዲሸፈን የሚያደርግ፤ መስክ ሥራ ላይ የተለያዩ ቦታዎች ጋዜጠኞችን በአግባቡ በማድረስ ሥራው እንዲሳለጥ በማደረግ፤ ሥራ አልቆ እረፍት የሚሆንበት ጊዜ ላይ በጣም ደስ የሚል ግንኙነት ያለው፤ መደሰት መሳቅ የሚወድ፤ የሚጫን ነገር ካለ ጭኖ ተባብሮ መምጣት የሚወድ ሰው ነው።

ዕቁባይ ከልብ የማይጠፋ አይነት ሰው ነው። እቁባይ ግልጽ ሰው ነው። ፊለፊት የሚናገር፤ የመሰለውን ከማድረግ ያለፈ ክፋት የሌለው የብዙኃኑ በወቅቱ የነበሩ ጋዜጠኞች የሕይወት ቅመም እንደሆነ መናገር ይቻላል። የፕሬስ ማከፋፈያ መምሪያ በሚባል ጊዜ ጀምሮ ሰለቸኝ ደከመኝ ሳይል ሥራውን በአግባቡ የሚሠራ ጠንካራ ሰው የነበረ ሕይወቱን በሙሉ በተቋሙ ያገለገለ ሰው ነው" ሲል አቶ ሰለሞን ሃሳቡን አካፍሎናል፡፡

### አቶ ዳኜ አበራ የፎቶግራፍ ባለሙያ

"ከአቶ ዕቁባይ ጋር የተዋወቅነው በ1987 ዓ.ም ነው። እኔ ወደ ኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ስቀላቀል እሱ ሾፌር ነበር። ከዛ የስምሪት ኃላፊ ሆኖም ረዥም ጊዜ ሠርቷል። በጦር ሜዳ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ወቅት አብረን የመዝመት እድልም ገጥሞን ነበር። ከጦርነቱም በተጨማሪ በርካታ የሀገራችንን ክልሎች አብረን ለመርገጥ ችለን ነበር።

ከዕቁባይ ጋር በጣም የተግባባነው በጦርነቱ ጊዜ ነበር። ወደ ዘመቻው ስንሄድ በሁለት ቡድን ተከፍለን ነበር፤ አንደኛው እሱ የያዘው ቡድንና ሌላው ደግሞ ሰይፉ የሚባል የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ሹፌር የያዘው ቡድን ነበር። እኔም ከኢቲቪዎች ጋር ነበርኩኝ፤ ግንባሩ አንድ ነው። የመጨረሻው ውጊያ ሲካሄድ በጣም የተፋፋመ ነበር፤ ብዙዎቹ ሲፈሩ እሱ የያዘው ቡድን ግን ወደኋላ ቀርቶ ሲዘግብ በከባድ መሣሪያ ተመተው ከአፈር ውስጥ ነበር ተጎትተው የወጡት።

በወቅቱ ሁለት ከቴሌቪዥን ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ደግሞ አንድ ፎቶግራፈር ሲሞቱ ብዙዎቹ ሲቆስሉ ከዛ አደጋ የተረፈ ሰው ነው። በተፈለገው ሰዓት የተፈለገው ቦታ ያለምንም ቅሬታ የሚደርስ የሀገር ባለውለታ ነው። ሥራውን ወዶና ፈቅዶ የሚያገለግል አይነት ሰው ነው። ቁጡ ተናዳጅ የፎቶ ግራፍ ባለሙያው አቶ ዳኜ



አበራ ትውስታውን አካፍሎናል፡፡

### አቶ ሰለሞን በቀለ ሾፌር

" ከአቶ ዕቁባይ ጋር ሥራ ከተቀጠርኩበት ጊዜ አንስቶ እንተዋወቃለን። ከሌላው ሠራተኛ ጋር የመኪናው ተገልጋይና ሠራተኞች አይነት ግንኙነት በዛው የተመሠረተ ወዳጅነት ቢኖርም፤ በሰርቪስ ክፍል ውስጥ በመተጋገዝና በመደጋገፍ መሥራቱ፤ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል የብዙዎችን ቦታ ሸፍኖ መሥራቱ፤ ድካምን ኃዘንን ችግርን በሙሉ በመተጋገዝ ማለፉ የበለጠ ይታይ ነበር።

አቶ ዕቁባይም ለችግር ደራሽ ደከመኝ ሰለቸኝ የማያውቅ ሌሎች ያዘኑበት ነገርን በፈገግታ እንዲረሱት የሚያደርግ ጥርስ አያስከድንም የሚባል አይነት ሰው ነበር። ከሁሉ በላይ ከልጅነት እስከ እውቀት የሠራበት ቤት ሥራ እንዳይበደል የነበረው የማስተባበር ችሎታ ከፍ ያለ ነበር።

ለሰው ደራሽ፤ ለጋስ እጅግ በጣም ጠንካራ ሠራተኛ ነገሮችን ደባብቆ ማለፍ የማይችል ነገር ግን ተናግሮ ወዲያው የሚረሳ አይነት ሰው ነበር። የያዘውን ነገር ዳር ሳያደርስ የማያቆም የጥንካሬ ተምሳሌትም ነበር፤ በተለይ ሥራ ላይ አይሆንም የሚባል ነገር አያውቅም፤ ሁልጊዜ እችላለሁ፤ አደርገዋለሁ በሚል መንፈስ የሚተጋ በአመራርነት ጊዜውም ሆነ በሾፌርነት ዘመኑ አንድም ቀን ሳያርፍ ለድርጅቱ የለፋ ሰው ነው።

በሁሉም ሠራተኞች ዘንድ የነበረው ተቀባይነት የላቀ እንደነበረ የሚታየው በጡረታ ተገልሎ ከመሥሪያ ቤቱ ሲሸኝ በታላቅ ክብር ነበር። ሠራተኛው በስጦታ አንበሽብሾት በፍቅር እንባ ነበር የሸኘው። በአጠቃላይ ዕቁባይ

**ለሰው ደራሽ፤ ለጋስ እጅግ በጣም ጠንካራ ሠራተኛ ነገሮችን ደባብቆ ማለፍ የማይችል ነገር ግን ተናግሮ ወዲያው የሚረሳ አይነት ሰው ነበር**

መገለጫው መልካምነት ደግነት ተታሪነት እንደነበር አስታውሳለሁ"

### ከባለቤታቸው አንደበት

"ከአቶ ዕቁባይ ጋር የተዋወቅነው ያደኩበት ሰፈር ሾላ አካባቢ ስለነበረ ከቤት ተልኬ ወደ ሱቅ በወጣሁበት አጋጣሚ ነበር። ያኔ በእድሜ በጣም አፍላ ወጣት የምባል አይነት ልጅ ነበርኩ። በአጋጣሚ የተጀመረው ትውውቅ አድጎ ለትዳር እንበቃለን የሚል ሀሳብ ግን አልነበረኝም።

ዕቁባይ በልጅነቴ ያወኩት እንደ አባት አስተምሮ አሳድጎኝ የኖረ አባቴም ባሌም ነበር። በትዳር አሥራ ስድስት ዓመታትን አብረን አሳልፈን ሁለት ልጆች አፍርተናል። ቤቱን አክባሪ ፤ጎዶሎ የማይወድ በፈገግታ የተሞላ ሰው ነበር። ለልጆቹ የሚሳሳ ድንቅ አባት ነበር።

ከሦስት አስርታት በላይ የእድሜ ልዩነት መኖሩ እንደ ባልና ሚስት ሳይሆን አንደ አባትና ልጅ ተከባብረን እንድንኖር አድርጎን ነበር። በወቅቱ አስቸጋሪ የነበሩ ነገሮች ቢኖሩም ትዳሩን አክባሪ ቤቱን ወዳድ ሳቅ ጫወታን የሚወድ አይነት ሰው እንደነበረ መናገር እችላለሁ። ለልጆቹ የሚሳሳ ልጆቹን ከማየት ከእነሱ ጋር ከመጫወት በላይ ደስታ የሚሰጠው ነገር እንዳልነበር አስታውሳለሁ"ስትል ወደኋላ የኋሊት ተሻግራ የነበረውን የፍቅርና የትዳር ሕይወት አጫውታናለች፡፡

### ከልጆቹ መካከል መና ዕቁባይ ስለ አባቷ

"አባቴ ከልጅነቴ ጀምሮ በፍቅር እያሳደገኝ ትምህርት ቤት እያመላለሰ ያስተማረኝ አባቴ ነው። እስካለሁበት ጊዜ ድረስ ለእኔ ያለው ፍቅር መግለፅ ስለሚያቅተው በስሜ እራሱ አይጠራኝም ‹‹እናቴ›› ብሎ ነው የሚጠራኝ፤ እንደዛ ብሎ ሲጠራኝ በጣም ደስ ይለኛል። ለእኔ ብሎ ሕይወቱን ለሠጠኝ አባት ምንም ሳላደርግለት እኔን የሚፈልግበት ደረጃ ደርሼ ሳያይ ተለየኝ። አባቴን በምንም በማንም የማልተካው የማልቀይረው የማለውጠው ብቸኛው ሰው አባቴ ነው።

አባቴ ለእኔ በጣም ጥሩ እና መልካም አሳቢ ሰው ነው:: ስለእሱ ሳወራ ቃል ያጥረኛል ምን ብዬ እንደምገልፀው ቃላቶች አይገልፁልኝም "

የዋህ ልበቀና እንደሆኑ የተነገረላቸው የእድሜያቸውን እኩሌታ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ብቻ ያገለገሉት አባት ኅዳር 9 ቀን 2016 ዓ.ም ከዚህ ዓለም ድካም አርፈዋል። አቶ ዕቁባይ ዮሴፍ ለሁሉም የሰው ልጆች የተቀመጠውን የሞት ፅዋ መጎንጨት ግዴታቸው ሆኗል።

ለሁሉ ደራሽ፤ አልባሽ አጉራሽ የሆኑት ሰው የሥራ ዓለም ታሪካቸው ኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ብቻ የነበረ እራሳቸውን በተለያዩ ሥልጠናዎች እያሳደጉ ከብስክሌት አሽከርካሪነት እስከ ታዋቂ ሹፌርነት፤ ከጋዜጣ አዳይነት እስከ የተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች አገልግለው 2001 ዓ.ም በጡረታ በክብር ተገልለዋል።

ጡረታ ከመውጣታቸው በፊት ከጋዜጠኞች ጋር በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች የተዘዋወሩ ሲሆን በደርግ ዘመነ መንግሥት በወታደራዊ መንግሥቱና በወያኔ መካከል የነበረውን ጦርነት ለመዘገብ የወጡ ጋዜጠኞችን ይዘው በጦር ሜዳ ውለዋል። ዳግም በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ወቅት ጋዜጠኞችን ይዘው በተጓዙበት ወቅት በከባድ መሣሪያ በመመታታቸው የተነሳ መኪናው ውስጥ የነበሩት አብዛኞቹ ሲቆሰሉና ሲሞቱ እሳቸው ግን እግራቸው ላይ በፍንጥርጣሪ ከመጎዳት ያለፈ ምንም ችግር ያልገጠማቸው መሆኑን ወዳጆቻቸው በትዝታ ይናገራሉ።

ሆኖም ስራ ሁልጊዜ ከመቃብር በላይ ነውና ከብስክሌት በመዞር አንጋፋውን አዲስ ዘመን ጋዜጣ በማደል መረጃዎችን በጧት ሲያደርሱ የነበሩት እኚህ የሀገር ባለውለታ ለዘላለም ሥራቸው ሕያው ሆኖ ይኖራል፡፡ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ በታወሰ ቁጥርም የአቶ ዕቁባይ የስራ ትጋትና ውለታም አብሮ ይወሳል።

ኢኮኖሚ

## ባህልና ቱሪዝም

# የኢትዮጵያ ሳምንት-የሁለተኛው ትውልድ ጥሪ

ዳግም ከበደ

ኢትዮጵያ የበርካታ የቱሪዝም መስህቦች መገኛ ነች። እነዚህን መስህቦች ወደ መዳረሻነት ቀይሮ የቱሪስት ፍሰቱን መጨመር ደግሞ ከዘርፉ ተዋንያን የሚጠበቅ ኃላፊነት ነው። ባለፉት ዘመናት የሀገሪቱን ሀብቶች በሚፈለገው ልክ የማስተዋወቅና ከዚያም ተጠቃሚ የመሆን ሂደቱ አዝጋሚ የሚባል እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ። የቱሪዝም ልማቱ፣ ጥበቃው እንዲሁም የቱሪስቶች ትኩረት በውስን የኢትዮጵያ መዳረሻዎች ላይ ብቻ የተገደበ ነበር።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የቱሪዝሙን ዘርፍ መነቃቃትና እድገት አቅጣጫ የሚቀይሩ እርምጃዎች በመንግሥት እየተወሰደ ይገኛል። ዘርፉን ከዋና ዋና የኢኮኖሚ ምሰሶዎች ተርታ መድቦ ልዩ ትኩረት ከመስጠት ጀምሮ አገሪቱ የቱሪዝም እምቅ አቅሞቿን አውቃ ለእድገቷ መሰላል እንዲሆኑ ለማስቻል ልዩ ልዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ እየሠራች ትገኛለች።

መንግሥት በዘርፉ ፖሊሲዎችን፣ ሕጎችንና አስቻይ ማዕቀፎችን ከመንደፍ እና በሥራ ላይ ከማዋል ባሻገር መዳረሻዎችን በማልማት፣ በማስተዋወቅና የግሉ ዘርፍን ተሳትፎ በማበረታታት ጉዳዮች ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል። በዚህም በጥቂት ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያ በቱሪዝም ፈጣን እድገት እያስመዘገበችና የሀገር ውስጥና የውጪ ቱሪስቱም ቁጥር እየጨመረ ይገኛል።

ዘርፉ በኮቪድ ወረርሽኝ ስርጭትና በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በነበሩ ግጭቶች ፈተና ውስጥ ወድቆ እንደነበር ባይታበይም በተለይ በሦስትና አራት ዓመታት ውስጥ በመሠረተ ልማት ግንባታ ረገድ ጉልህ እድገቶችን አሳይቷል። እነዚህ ፕሮጀክቶች የፈጠሩት መነቃቃት ያጋጠሙ ችግሮችን ተቋቁሞ የቱሪስት ፍሰቱ እንዳይቋረጥና ችግሮቹ የፈጠሩትን መቀዛቀዝ መቋቋም እንዲቻል በር ከፋች ሆኗል።

ከአዳዲስ የመዳረሻ መሠረተ ልማት ግንባታዎች ባሻገር የሀገር ውስጥና የውጪ ቱሪስቱን የጉብኝት ፍላጎት የማነቃቃት፣ የማስተዋወቅ እንዲሁም ሀገር አቀፍ ጥሪዎችን የማድረግ ተግባሮች ባለፉት ዓመታት ተፈጽመዋል። ዲያስፖራ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው መጥተው ከባሕልና ከማንነታቸው ጋር እንዲተዋወቁ፣ የውጪ ቱሪስቶች ከዚህ ቀደም ባልተለመዱ የኢትዮጵያ ክፍሎችና መስሕቦችን እንዲተዋወቁ እና የቱሪስት ፍሰቱ እንዲጨምር የቱሪዝም ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ቱር ኦፐሬተሮችና የዘርፉ ተዋንያን የነበራቸው ድርሻ ቀላል የሚባል አይደለም። ይህ ጥረት አሁንም እንደቀጠለ መረጃዎች ያሳያሉ።

ከሳምንታት በፊት ከዳውሮ ዞን እስከ ኮንታ በሚዘረጋው የጨበራ ጩርጩራ ብሔራዊ ፓርክ ተገኝተው ‹‹የጨበራ ጩርጩራ የዝሆን ዳና ሎጅ›› መርቀው የከፈቱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የሁለተኛው ትውልድ ዲያስፖራ አባላት ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ከባሕላቸው፣ ከማኅበረሰቡ፣ ከታሪክና ከተፈጥሮው ጋር እንዲተዋወቁና ለኢትዮጵያም አምባሳደር ሆነው እንዲያስተዋውቁ ጥሪ አድርገው ነበር።

ጥሪው በኢትዮጵያ በቱሪዝም ላይ እየተወሰዱ ካሉ የማነቃቃት እርምጃዎች ውስጥ የሚካተት ነው። የቱሪዝም ሚኒስቴር በተመሳሳይ ልዩ ልዩ መርሐ ግብሮችን በመቅረፅ እስከ 2017 ዓ.ም የሚዘልቅ የሁለተኛው ትውልድ ዲያስፖራ አባላት ጥሪን ይፋ አድርጎ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን ጀምሯል። ካሳለፍነው የገና በዓል አንስቶ ጥሪውን የተቀበሉ የሁለተኛው ትውልድ ዲያስፖራዎች ወደ ኢትዮጵያ እየገቡ ይገኛሉ። ሚኒስቴሩና የተቋቋመው ብሔራዊ ኮሚቴም በሰጠው መግለጫ እየተደረገ ያለው አቀባበል በቀጣይ ምዕራፍ ወደ አገራቸው ለሚመጡ ተነሳሽነትን እየፈጠረ መሆኑን አስታውቋል።

የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ በተለይ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ጥሪውን አስመልክቶ እንደተናገሩት፤




ለሁለተኛው ትውልድ የተደረገው ጥሪ ዋና የትውልድ ቅብብሎሽ እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን ለብዙ ዓመታት በውጭ ሀገራት ኖረዋል፡፡ ልጆች አፍርተዋል፡፡ ልጆቻቸው የማንነት ጥያቄ አለባቸው። የመጡበትን የእናት የአባቶቻቸውን አያቶቻቸውን ሀገር ማወቅ ይፈልጋሉ፡፡ ይህንን ለማሳካት ጥሪው አስፈልጓል።

ሚኒስትሯ እንደሚሉት፤ ኢትዮጵያ የሚያኮራ ታሪክና ባሕል አላት፡፡ እነርሱም ውብ የሆነ ተፈጥሮ ያላት ሀገር አለቻቸው። ይህ እንደመሆኑ መሰል ትስስር መፍጠር አስፈላጊ ነው፡፡ የሁለተኛው ትውልድ አባላትም መነሻቸውን ያውቃሉ፡፡ ኢትዮጵያ የሁሉም መነሻ ነች፡፡ የሰው ልጅ መገኛ ነች። ‹‹የእናት የአባቶቼ የአያቶቼ ሀገር›› የሚለው ስሜት በውስጣቸው አለ። እንደ ሰው ልጅ ሁሉም መነሻችንን ማወቅ ይፈልጋል፡፡

‹‹ጥሪው ሁለተኛ መጥተው ባሕልና ታሪካቸውን እንዲያውቁ እንዲሁም ለወገኖቻቸው መስጠትና መቀራረብ እንዲችሉ መንገድ ለመፍጠር ነው›› የሚሉት ሚኒስትሯ፤ የያዝነው የጥር ወር ብዙ ፌስቲቫሎች ያሉበት በመሆኑ በተለያየ መልኩ ሀገራቸውን ባሕላቸውን ለማወቅ የተመቸ አጋጣሚ የሚፈጠርበት መሆኑን ይናገራሉ፡፡ ለዚህም የተለያዩ ሁነቶች መዘጋጀታቸውን ያስረዳሉ። ባሕላቸውን እንዲያውቁ፣ እንዲማሩና ወደተለያዩ የሀገራችን ክፍል ሄደውም ራሳቸው በራሳቸው እንዲያገኙ ምቹ አጋጣሚ መፈጠሩን ያስረዳሉ፡፡ ጥሪውን ተከትሎ ወደ ሀገራቸው የገቡ ትውልደ ኢትዮጵያውያንም በርካቶች መሆናቸውን ገልፀዋል።

> የሀገሪቱን የቱሪዝም መስህቦች ለማስተዋወቅ ጥሪው ትልቅ ዕድል የሚፈጥር ነው። የሁለተኛው ትውልድ ዲያስፖራዎች ወደ እናት አገራቸው ሲመጡ ከፍተኛ የቱሪዝም እንቅስቃሴ ይጠበቃል፤ ዘርፉንም በተለየ የማነቃቃት አቅም ይፈጥራል

አቶ ቴዎድሮስ ደርበው በቱሪዝም ሚኒስቴር የስትራቴጂክ ዩኒት አስተባባሪ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት የሀገሪቱን የቱሪዝም መስህቦች ለማስተዋወቅ ጥሪው ትልቅ ዕድል የሚፈጥር ነው። የሁለተኛው ትውልድ ዲያስፖራዎች ወደ እናት አገራቸው ሲመጡ ከፍተኛ የቱሪዝም እንቅስቃሴ ይጠበቃል፤ ዘርፉንም በተለየ የማነቃቃት አቅም ይፈጥራል።

‹‹ጥሪውን አስመልክተን የተለያዩ ዝግጅቶችን በማሰናዳት ላይ እንገኛለን›› ያሉት አቶ ቴዎድሮስ፤ በቱሪዝም ሚኒስቴር ሰብሳቢነት በሚመራ ዐቢይ ኮሚቴ በቅርብ ግዜ ውስጥ የኢትዮጵያ ሳምንት የሚል ደማቅ ሥነ ሥርዓት እየተዘጋጀ መሆኑን ይገልፃሉ። በመሰናዶው ልዩ ልዩ መርሐ ግብሮች እንዳሉ በመግለፅም ከዚህ ወስጥ ባሕልን ማስተዋወቅ የሚረዱ ጭፈራዎች፣ ሙዚቃዎች፣ ባሕላዊ አልባሳት የሚተዋወቁበት ይሆናል። በዝግጅቱ የዕደ ጥበባት ውጤቶች፣ የኢትዮጵያ ድምፆች (ሙዚቃ መሣሪያዎች)፣ ባሕላዊ ምግቦችና የአዘገጃጀት ሥነ ሥርዓቶች ለሁለተኛው ትውልድ ዲያስፖራ እንግዶች የሚተዋወቅበት ዝግጅት የሚያካትት ነው።

‹‹ትውልደ ኢትዮጵያውያኑ በሩቅ ከሚሰሙት በዘለለ በቀጥታ ቀርበው በማየት እና በመሳተፍ ባሕላቸውን እና ማንነታቸውን የሚተዋወቁበት ነው›› ያሉት አቶ ቴዎድሮስ ደርበው፤ በኢትዮጵያ ሳምንት ዝግጅት ላይ ከባሕላዊ ሁነቶቹ በተጨማሪ ጉባኤዎች እንደሚኖሩ ይናገራሉ። በሚኒስቴሩ በኩልም የቱሪዝም መስህብ ማስተዋወቅ ሥራ እንደሚከናወን ይገልፃሉ። በኢትዮጵያ ሳምንት ላይ ከሚከናወኑ ሁነቶች ባሻገር ልዩ ልዩ የጉዞና ጉብኝት ዝግጅቶች ተዘጋጅተዋል።

አስጎብኚ ድርጅቶች፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ (ኢቲ ሆሊደይስ) በቱሪዝም ሚኒስቴር አስተባባሪነት ሁለተኛ ትውልድ የዲያስፖራ ክፍል ፍላጎትና ባሕሪ መሠረት ያደረጉ የጉዞና ጉብኝት ፕሮግራሞች መዘጋጀታቸውን የሚናገሩት አቶ ቴዎድሮስ ደርበው፤ ሆቴሎች፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ አስጎብኚ ድርጅቶች ከፍተኛ ቅናሽ አድርገው በመጠባበቅ ላይ መሆናቸውን አስረድተዋል። በዚህም ኢትዮጵያ አገራቸው ያላትን የቱሪዝም ፀጋዎች እንዲያውቁ፣ ባህላቸውን እንዲረዱና እንደ ሀገር መሠረታቸውን ዳግም እንዲገናኙ በማሰብ የተዘጋጁ ናቸው። ክልሎችም ከዋናው ዝግጅት ጋር በተናበበ መልኩ የተለያዩ ሁነቶችን እንደሚያሰናዱ ይጠበቃል።

ሁለተኛው ትውልድ ዲያስፖራ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው እንዲገቡ ሲደረግ በርካታ ሁነቶችን ታሳቢ በማድረግ ነው። ከዚህ ውስጥ ጥሪው በተደረገ ሰሞን የገና በዓል በመሆኑ በቀጥታ ከኢትዮጵያ ባሕል፣ በዓላትና ፌስቲቫሎች ጋር እንዲገናኙ እድሉን እንደሚፈጥር ሲገለፅ ቆይቷል። የያዝነው የጥር ወርም በተባበሩት መንግሥታት የሳይንስ፣ የትምህርትና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) የተመዘገበው የጥምቀት በዓል የሚከበርበት ወቅት ነው። ይህ አጋጣሚም ወደ ኢትዮጵያ እየመጡ የሚገኙ ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሃይማኖታዊ ፌስቲቫሉ ላይ ተገኝተው ሥነሥርዓቱን ለመታደም እድሉን ይፈጥርላቸዋል።

አቶ ቴዎድሮስ ደርበው እንደሚሉት፣ የጥምቀት በዓል በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች ይከበራል። በተለይ በጎንደር፣ በባቱ (ዝዋይ)፣ በኢራንቡቲ ባማረና በልዩ ሁኔታ እንደሚከበር አንስተው ጥሪ የተደረገላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያንም እንደየፍላጎታቸው እና የግል መርሐ ግብራቸው ተሳትፎ የሚያደርጉበት ሁኔታ እንደሚኖር ይገልፃሉ። በልዩ ሁኔታ በቱሪዝም ሚኒስቴር የተዘጋጀ ሁነት እንደማይኖርና በኢትዮጵያ ሳምንት የሚጠቃለል መሆኑንም ያነሳሉ።

ይሁን እንጂ ጥምቀት ከማይዳሰስ የሰው ልጆች ወካይ ቅርስ መካከል በዩኔስኮ የተመዘገበ ታላቅ የኢትዮጵያውያን ባሕል መሆኑን ያነሱት አቶ ቴዎድሮስ፣ ማንም ሰው በሀገር ውስጥ ተገኝቶ በዚህ ታላቅ ሀይማኖታዊ በዓል ላይ ሳይታደም አይቀርም ይላሉ። ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ይህንን ሀይማኖታዊ በዓል አንደ አንድ የቱሪዝም መስህብ እንደሚያስተዋውቅ ያነሳሉ። ወደ አገራቸው የገቡ የሃይማኖቱ ተከታዮች ትውልደ ኢትዮጵያውያንም በበዓሉ ላይ ይታደማሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ ይገልፃሉ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ወደ ሥልጣን ከመጡ ጊዜ ጀምሮ በውጪ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሀገራቸውን አውቀው ለቀሪው ዓለም እንዲያስተዋውቁ፣ ከባሕልና ማንነታቸው ጋር እንዲገናኙ እና ከታሪካዊ መሠረታቸው ጋር ጥብቅ ትስስር እንዲፈጥሩ ባደረጉት ያላሰለሰ ጥረት በቱሪዝሙ ዘርፍ ላይ ትልቅ ለውጥ ያስገኙ ጥረት በርካታ ውጤቶች ተመዝግበዋል። ለሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያውያን የዲያስፖራ አባላት የተደረገው ጥሪም የዚሁ ጥረት አካል ነው፡፡


ለዲያስፖራ ኢትዮጵያውያን ከተደረጉ ጥሪዎች ውስጥ አንዱና የመጀመሪያው በ2014 የተካሄደው ተጠቃሽ ምሳሌ መሆን የሚችል ነው። በወቅቱ አንድ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ወደ አገራቸው እንዲገቡ በመንግሥት ይፋዊ ጥሪ ተካሂዶ፣ ጥሪው ስኬታማ እንደነበር መረጃዎች ጠቁመዋል። በጊዜው ትውልደ ኢትዮጵያውያን ገናን በላሊበላ፤ ጥምቀትን በጎንደር እንዲሁም የሙስሊሙ ማኅበረሰብም ረመዳንን በኢትዮጵያ እንዲያከብሩና ታሪካዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ባሕላዊ የቱሪዝም መስህቦችን እንዲጎበኙ ተደርጎ ነበር።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## የአርበኞች ማኅበር አመሠራረት

**ዋስልኝ አየለ**



የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር ጥር 1 ቀን 1931 ዓ.ም ተመሠረተ

ይህ ማኅበር የጀግኖችን ሁሉ ታሪክ የሚዘክር ማኅበር ነው ማለት ይቻላል፡፡ አሁን ላይ በሕይወት ያሉ የማኅበሩ አባላት አባት አርበኞች በሕይወት በመኖር የሚያውቁትና በቃል የሚናገሩት ራሱ ብዙ ታሪክ ይናገራል፡፡ ማኅበሩ በተለያዩ የድል በዓላት ላይ በመገኘት የጀግኖችን ታሪክ ያስታውሳል፤ የኢትዮጵያ ጀግኖች ሀገራቸውን በምን አይነት መንገድ ከወራሪ ተከላክለው የጥቁር ሕዝብ የነፃነት ተምሳሌት እንድትሆን እንዳደረጓት ለአሁኑ ትውልድ መልዕክት ያስተላልፋል።

በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን 85 ዓመታትን ወደኋላ መለስ ብለን የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር አመሠራረትና ያሳለፋቸውን ውጣ ውረዶች እናስታውሳለን፡፡ ከዚያ በፊት እንደተለመደው ሌሎች የዚህ ሳምንት የታሪክ ክስተቶችን በአጭር በአጭሩ እናስታውስ፡፡

ከ104 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥር 2 ቀን 1912 ዓ.ም (በአውሮፓውያኑ የዘመን ቀመር 1920) ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በመላው ዓለም ሰላምን የማስፈን ዓላማ ይኖረዋል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበት የነበረው ‹‹የዓለም መንግሥታት ማኅበር›› (በእንግሊዘኛ አጠራሩ League of Nations) ተመሠረተ፡፡

ተቋሙ የተመሠረተው በፓሪስ የሠላም ጉባዔ ሲሆን በሚያዝያ 1938 ዓ.ም ፈርሶ ሥልጣንና ተግባራቱ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (United Nations) እንዲተላለፉ ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩል ጥር 2 ቀን 1912 ዓ.ም የተመሠረተውን የዓለም መንግሥታት ማኅበርን (League of Nations) የተካው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ (United Nations General Assembly)፤ የመጀመሪያ ስብሰባውን ያካሄደው ከ78 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥር 2 ቀን 1938 ዓ.ም (በአውሮፓውያኑ 1946) ነበር፡፡ የጠቅላላ ጉባዔው የመጀመሪያ ስብሰባ የተካሄደው በለንደን ከተማ ሲሆን የ51 ሀገራት ተወካዮች ተሳትፈዋል፡፡

ከ123 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥር 3 ቀን 1893 ዓ.ም የጎጃም ንጉሥ የነበሩት፣ ንጉሥ ተክለኃይማኖት ተሰማ አረፉ፡፡

ከ79 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥር 5 ቀን 1937 ዓ.ም ጀግናው አርበኛ ደጃዝማች በላይ ዘለቀ (አባ ኮስትር) እና ወንድማቸው እጅጉ ዘለቀ በቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ መንግሥት ተሰቀሉ፡፡

በዕለቱ በዝርዝር ወደምናየው ታሪክ ስንሄድ ከ85 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥር 1 ቀን 1931 ዓ.ም የተመሠረተውን የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር አመሠራረት እንቃኛለን፡፡

ያሳለፍነው ሳምንት ከላይ የገለጽናቸውን የታሪክ ክስተቶች በተለያዩ ዘመናት አስተናግዶ ነበር። የአንዳንዶቹ ብዙ የተባለለት ሲሆን የአንዳንዶቹ ደግሞ ምናልባትም ልብ የማይባል ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህን ሁሉ የሚዘክረውና የሚያስታውሰው ግን ይህ ማኅበር ነው፡፡ ስለዚህ የጀግኖችን ታሪክ የሚዘክረውን የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር ምሥረታ እና ታሪካዊ ክስተቶቹን እናስታውስ፡፡

ደጃዝማች ከበደ ተሰማ ‹‹የታሪክ ማስታወሻ›› በተሰኘው መጽሐፋቸው ላይ፣ ይህ ማኅበር በአርበኝነት ዘመን በሸዋ ክፍለ ሀገር በ1931 ዓ.ም «የጥንታዊት ኢትዮጵያ የጀግኖች ማኅበር» በሚል ስም ተሠይሞ የተቋቋመ ማኅበር እንደነበርና ዓላማውም የአርበኞችን ክብር በማበረታታትና በየሀገሩ ካሉ አርበኞች ጋር በመላላክ የሚገኘውን ሥራ ፍሬ እርስ በእርስም ሆነ በስደት ላይ ከነበሩት ንጉሠ ነገሥት ጋርም መካፈል እንደነበር ገልፀዋል።

ጥር 1 ቀን 1931 ዓ.ም ባላምባራስ አበበ አረጋይ (በኋላ ራስ)፣ ሻለቃ መስፍን ስለሺ (በኋላ ራስ)፣ ልጅ ግዛቸው ኃይሌ፣ ወንድማማቾቹ ደጃዝማች ፀሐዩ ዕንቁሥላሴ እና ደጃዝማች ተስፋዬ ዕንቁሥላሴ፣ አቶ እምአእላፍ ኅሩይ፣ ደጃዝማች ሀብተሥላሴ በላይነህ፣ ደጃዝማች ታከለ ወልደሐዋርያት … በአጠቃላይ 29 ስመ ጥር አርበኞች በተገኙበት በሞጃና ወደራ (ተጉለት)፣ በልዩ ስሙ አንቀላፊኝ ሜዳ፣ ‹‹አንዲት ግራር›› በሚባለው ቦታ ለሀገር ፍቅር ሲባል ማኅበሩ ተመሠረተ፡፡

የፋሺስት ጦር ተሸንፎ የኢትዮጵያ ነፃነት ከተመለሰ ከ21 ዓመታት በኋላ፣ በሚያዝያ ወር 1954 ዓ.ም ሌተናል ጀኔራል ነጋ ኃይለሥላሴ ከሥራ ባልደረቦቻቸውና ከሌሎች ሰዎች አገር አፍቃሪዎች ጋር በመሆን ‹‹ጥንታዊት ኢትዮጵያ ሀገራዊ የጀግኖች ማኅበር››ን በታደሰ ሀገራዊ ዓላማና በተሻሻለ ደንብ አቋቋሙት። ይሁን እንጂ ማኅበሩ ከመንግሥት እውቅና ያገኘው ሰኔ 19 ቀን 1956 ዓ.ም ነበር፡፡

ሌተናል ጀኔራል ነጋና ባልደረቦቻቸውም በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ አባላትን መመዝገብ ችለዋል፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ብዙ መሰናክሎችን እያለፈ ዛሬ ላይ የደረሰው ይህ ማኅበር፣ በአሁኑ ወቅት የራስ መስፍን ስለሺ ልጅ በሆኑት በልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን ስለሺ እየተመራ ይገኛል፡፡

በ2006 ዓ.ም የታተመውና ‹‹እኔ ለአገሬ›› የተሰኘው የማኅበሩ መጽሔት ስለአመሠራረቱ በሰፊው ያስረዳል። ከመጽሔቱ በተገኘው መረጃ፤ የማኅበሩ የመጠሪያ ሥያሜ “የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር” ይባላል፡፡ ማኅበሩ በዚያን ጊዜ በነበሩት ኅበዛዝትና የኅበዝ አለቆች የማስተባበሪያና የመምሪያ አካል ነው፡፡

የጀግኖች አርበኞች መሰባሰቢያና መመሪያ ጥላ የሆነው ይህ ማኅበር በሰሜን ሸዋ ተጉለት አውራጃ ለመጀመሪያ ጊዜ ይመሥረት እንጂ ቀስ በቀስ በመስፋፋትና በመጠናከር፤ በእንግሊዝ መንግሥት በመታገዝ በ1933 ዓ.ም የወራሪውን የፋሽስት እብሪተኛ ኃይል በድል አድራጊነት ሚያዚያ 27 ቀን በታላቅ ገድል ድል ተጎናጽፏል፤ መላ አገሪቷ ነፃ ወጥታለች፤ ከዚህ ጣፋጭና አስደናቂ ድል በኋላም ማኅበሩ የተቋቋመበትን ዓላማ እንዲያውቅና እንዲስማማ አድርጎ መተዳደሪያ ደንቡ ተሻሽሎ ተጠናክሮ ተቋቋመ። ይህ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር መጀመሪያ አንቀላፊኝ ላይ ሲመሠረት ዓላማው የአርበኝነቱን ትግል ለማስተባበር ነበር፡፡

ማኅበሩ ከድል በኋላ እንደገና ሲጠናከርና ሲቋቋም ደግሞ ዓላማ ያደረገው የአርበኝነት ትግሉንና የታጋዮቹን ታሪክ ለመዘከርና ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ፣ እንዲሁም በሕይወት ያሉት ጀግኖች አርበኞች የሚደገፉበትን መንገድ ለመፍጠርና ሀገር ተረካቢው ትውልድ መብቱንና ግዴታውን የሚያውቅበትና የሚረዳበትን ማዕከል የሚያገለግልበትን መንገድ በማሰበም ጭምር ነው፡፡

የጥንታዊ ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር ከተቋቋመ በኋላ አሁን ባለበት አራት ኪሎ የራሱን ሕንፃ በማሠራት በየጊዜው ከአርበኞቹ መካከል መሪዎቹን እየመረጠ በዚያው መንገድ ቀጥሏል። ማኅበሩ የተቋቋመበትን ዓላማ ይዞ እንዲቀጥልም ይሁን የመታሰቢያ ሕልውናውን በሕያውነት ለማቆየት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የቅርብ ድጋፍና ክትትል እንዳልተለየው የመጽሔቱ መረጃ ያሳያል፡፡

የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር አንቀላፊኝ ላይ ሲመሠረት በሰብሳቢነትና በአባልነት የነበሩት አባት አርበኞች ቃል ኪዳን ተገባብተው ነበር። ከቃል ኪዳናቸው ውስጥ የሚከተሉት ይገኛሉ፡፡

‹‹እኛ ከዚህ በታች የመተማመኛ ቃል ፊርማችንን ያደረግን በጥንታዊት ኢትዮጵያ የጀግኖች አርበኞች ማኅበር ስንገባ በጥቅምት 23 ቀን 1931 ዓ.ም የወጣውን ደንብ ወደናል፡፡ ግዴታውን ሁሉ እንፈጽማለን። ምንም ቢቸግረን በዚሁ ደንብ በአራተኛው ቁጥር እንደተፃፈው የመንፈስ ቅዱስ ወንድሞቻችንንና ጓደኞቻችንን አንከዳም፡፡ ሁለተኛ በሦስተኛው እንደተባለው የሀገራችንን ነፃነት በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ክብሯ የሚጎድልበትን፣ ጓደኞቻችን የሚጎዱበትን አንሠራም፡፡ እራሳችንም ምንም ቢቸግረን ለጠላት አንገባም፡፡

…. በሃያ አንደኛው ተራ ቁጥር እንደተፃፈው የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት መቃወም የለብንም። ይህንን ሁሉ ባንፈጽም የእግዚአብሔር መቅሠፍት ያጥፋን፡፡ ለዚሁም ፈፃሚ መሆናችንን ለማሳወቅ ዋስ ጠርተናል። ጥር 1 ቀን 1931 ዓ.ም አንቀላፊኝ መንዝ››

ፊርማ መሥራች አባላት (ሹማምንት) የነበሩትም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ክቡር ራስ አበበ አረጋይ፤ የክብር ሊቀመንበር
2. ባሻ ወልደኪሮስ ገብረመስቀል፤ የሥራ ሊቀመንበር
3. አቶ ፈለቀ ዳኜ፤ ዋና ፀሐፊ
4. አቶ ደምሴ ወልደአማኑዔል፤ አባል
5. አቶ ደሣለኝ ተክለወልድ፤ አባል
6. አቶ ልሳኑ ሀብተወልድ፤ አባል
7. ልጅ ፀሐይ እንቆሥላሴ፤ አባል
8. ልጅ ተስፋዬ እንቆሥላሴ፤ አባል
9. ልጅ ወልደዮሐንስ እምሩ፤ አባል
10. ልጅ ጽጌ ወልደማርያም፤ አባል

ማኅበሩ ተመሥርቶ፣ ኢትዮጵያም ድል አድርጋ ወራሪው የጣሊያን ፋሽስት ከኢትዮጵያ ተጠራርጎ ወጣ፡፡ ከድል በኋላ ማኅበሩ መንግሥታዊ ድጋፍ እየተደረገለት፣ የጀግኖችን ታሪክ እየዘከረ እነሆ ዛሬ ድረስ ቀጥሏል፡፡

ከድል በኋላ ሀገሩን ላገለገለው አርበኛ ስደተኛና የውስጥ እርበኛ የመታሰቢያ ሜዳሊያ ተሰጠ። ከዚህ ውጭ መንግሥት ለአርበኛው የሚሰጠው የጡረታ ክፍያ ስለሌለ ለጠየቀው አርበኛ መንግሥት ከሚያዝበት መሬት ለአርበኛው ርስት መሬት እንዲሰጠው ተደረገ፡፡

ለአርበኛው መጦሪያው ይሄው መሬቱ ሆነ። አርበኛው መንግሥት የሰጠውን መሬት አልምቶ፣ ቤት ሠርቶ ለመንግሥት የሚገባውን ግብር እየከፈለ በሰላም መኖር ጀመረ፡፡

በንጉሣዊ ሥርዓቱ በዚህ ሁኔታ የቆየው አርበኛ እና ማኅበሩ በ1967 ዓ.ም የመንግሥት ለውጥ ሲከሰት ግን ችግር ገጠመው፡፡ ንጉሣዊ ሥርዓቱን የገረሰሰው አብዮታዊው ደርግ መሬት የመንግሥትና የሕዝብ ነው የሚል አዋጅ አወጣ፡፡ በዚህ የደርግ አዋጅ ምክንያት በቢሮ የተያዘውን ቤት ብቻ በማስቀረት አርበኛው ሁሉ መሬቱንና ንብረቱን ተነጠቀ፡፡ እንዲያውም አንዳንዶቹ መነጠቅ ብቻ ሳይሆን ለሕይወታቸው የሚያሰጋቸው ሁኔታ ሁሉ ተፈጠረ፡፡ እንዲያም እንዲህም እያሉ ለቢሮ ብቻ በቀረችላቸው ቤት ማኅበሩን አቆዩት፡፡

ዳግም የመንግሥት ለውጥ ተፈጠረ፡፡ ወታደራዊው የደርግ ሥርዓት ተገርስሶ ኢሕአዴግ ሀገሪቱን ማስተዳደር ጀመረ፡፡ የማኅበሩ ሰዎች ከደርግ አንፃር ኢሕአዴግን ያመሰግኑታል፡፡ ምክንያቱም በ2001 ዓ.ም አዲስ ሕንጻ ለማሠራት የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ወስኖ ወደ ሥራ ተገብቷል፤ ሆኖም ግን ሕንጻው በተለያዩ ምክንያቶች ሲጓተት እንደቆየ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በመጨረሻም ተሳክቶ አሁን ያለውን የአርበኞች ሕንጻ በተስፋፋ መልኩ ለመገንባት ተችሏል፡፡ ማኅበሩም እነሆ የጀግኖች አርበኞችን ታሪክ የሚዘክር ሆኗል፡፡

# የዝነኞች ገጽ

# መድረክ የሚፈውሳት ሁለገብ

**ቤዛ እሸቱ**

በ1939 ዓ.ም በመስከረም አንድ የዓውዳ ዓመቱ ግርግር በደመቀበትና ልጃገረዶች አበባዮሽ (አበባ አየሽ ወይ?) በሚጨፍሩበት ዕለት እችን ምድር ተቀላቀለች። በተወለደችበት ቀን የሰማችው የልጃገረዶች ዜማ ይሁን የአጋጣሚ ነገር ከልጅነቷ አንስቶ ለሙዚቃ የተለየ ፍቅር ነበራት፡፡ የእሷን መወለድ ተከትሎ ከአዲስ አበባ ቀጨኔ መድኃኒያለም አካባቢ የፈለቁ አርቲስቶች ቁጥር በአንድ ከፍ ብሏል፡፡ የዚህ ምክንያቱም ከቤት አልፋ የመንደር፤ ከመንደር አልፋ የሀገር ድምቀት የሆነችው አርቲስት ሙናዬ መንበሩ የልደት ቀን መሆን ነው፡፡

ለዘመን መለወጫ አበባየሆሽን ከጓደኞቿ ጋር መጫወት የዓመት ከዓመት ልማዷ ነው፡፡ ከሰፈር ጓደኞቿ መሐል ማራኪ ድምፅ አላትና እሷ ዋና አውራጅ፤ ሌሎቹ ተቀባይ ሆነው ሰፈሩን በአበባየሆሽ ዜማ ያዳርሱታል። ይሄ የዓመት ልምዷ ታዲያ አንድ የበዓል እለት በሻህ ተክለማርያም ከሚባሉ የሀገር ፍቅር መሥራች ደጅ አደረሳት፡፡ የልጃገረዶቹ ወደ ጊቢው አገባብ የደንቡን ለማድረስ እንጂ የቤቱን ጌታ አውቀው አልነበረም፡፡ ሌሎች ልጃገረዶች እያጀቧት አበባየሆሽን በግሩም ድምፅ በምታዜመው ሙናዬ ድምፅ የተገረሙት የቤቱ አባወራ ታዳጊዋን ለማየት ከቤት ወደ ደጃፍ ብቅ አሉ፡፡ ያኔም በ12 ዓመቷ ታዳጊ ብቃት የተደነቁት በሻህ "ለምን ሀገር ፍቅር አትቀጠሪም?" አሉ፡፡ መልሷ አላውቀውም ቢሆንባቸው፤ ሀገር ፍቅርን የሚያሳያት ሰው ሊመድቡላት ተነጋግረው ተለያዩ፡፡

አበባየሆሽ ከሁነኛ ሰው ቤት ያደረሳት ሙናዬ በ12 ዓመቷ ሀገር ፍቅር ላወጣው ማስታወቂያ እንድትመዘገብ መንገድ ከፈተላት፡፡ ፈተናውን በአጥጋቢ ውጤት በማለፏ ትያትር ቤቱን በሁለ-ገብ ባለሙያነት ተቀላቀለች፡፡ ታዲያ ኋላ ላይ የትዳር አጋሯ የሆነው በቀለ ወልደፃዲቅ ቀድሟት የትያትር ቤቱ ሠራተኛ ነበርና ከፈታኞቿ መሐል ነበር፡፡ ታዳጊ እያለች የተቀላቀለችው ሙናዬ በሀገር ፍቅር ያልሆነችው የለም፤ ተወዛዋዥ፣ ድምፃዊ ደግሞም ሀገር ያደነቃት ተዋናይ ነበረች፡፡ ያም ቢሆን ብዙዎች እንዲያውቋትና ስሟን እንዲያነሱ ያስገደዳቸው የትወና አቅሟ ነው። በተለይ "የቀለጠው መንደር" የተሰኘው ትያትር ላይ የነበራት ትወና ታዳሚን በሙሉ የሚያስደምም ነበር፡፡

ትያትሩ ለአምስት ዓመታት በመድረክ ላይ በቆየበት ቀን ሳምንት በሳምንት ያለመታከት አዳዲስ ዲያሎጎችን መፍጠር መለያዋ ነበር፡፡ በተለይ እሷ ወክላት የምትሠራት ነገረኛ የሆነች ሴተኛ አዳሪን ገጸ-ባሕሪ ነበርና ከሳምንት ሳምንት የምታመጣቸው አዳዲስ ስድቦች ደሞ ባሁኑ ምን ብላ ትሳደብ ይሆን? በሚል በጉጉት ይጠበቅ ነበር፡፡ ሙናዬ ስትተውን ሁለመናዋ ይተውናል፤ የሷን ትወና የማይተባበር የአካል ክፍል የላትም፡፡ እጇን የምታንቀሳቅስበት መንገድ፤ ዓይኗ አብሮአት ሀሳቧን ሲደግፍ፤ ሰውነቷ ሲታዘዛት ለጉድ ነው፡፡

ስለሙናዬ ምስክርነት የሚሰጡ አብረዋት የሠሩ የሙያ ባልደረቦቿ የተሰጣትን ገጸ-ባሕሪ በማዳበር (ኢምፕሮቫይዜሽን) ጎበዝ ናት ይላሉ። እሷ ስትተውን ሁለመናዋ አብሯት ይተውናል፡፡ አንገቷ የራሱ መልዕክት አለው፤ ሲያስፈልግ ዓይኗም ይታዘዛል፤ እጇም የግሏ ነው። እሷ ጋ ዝም ብሎ ቃለ ተውኔቱን ማነብነብ አይታሰብም። ታማ እሷን የሚተካ የለምና በደጋፊ ከአልጋ ወርዳ ወደ መድረክ ስትወጣ ከበሽታዋ ጋር ትለያያለች በማለት አብረዋት የሠሩና የቅርብ ቤተሰቦቿ ይመሰክሩላታል። በተደጋጋሚ እያመማት ሥራ ከሚቋረጥ ብላ ለሥራዋ በድጋፍ ትመጣለች፡፡ ከዛ ተደጋግፋ ወደ መድረክ ትሸኛለች፤ ከዛማ ምን ጥርጥር አለው፣ የድሮዋ ሙናዬን ትሆናለች፡፡ ታዳሚንም አብረዋት የሚተውኑትንም አስደምማ ከመድረክ ትወርዳለች፡፡

ሐምሌ 17 ቀን 1958 ዓ.ም ቀኑ አጀማመሩ ከወትሮው የተለየ አይመስልም፡፡ ሙናዬ ከወትሮ በተለየ ሙሉ ቀኗ በሥራ ፕሮግራም ተጣቧል፡፡ በጠዋት ለንጉሥ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መዝሙር የማቅረብና አበባ የመስጠት ፕሮግራም ሥላለ በማለዳው 12፡00 ሰዓት ሀገር ፍቅር ድረሱ ተብለዋል፡፡ ከሰዓት ደግሞ "ምቀኛው እድሌ" የተሰኘው እሷ በትወና የምትሳተፍበት ትያትር በትያትር ቤቱ ለተመልካች የሚቀርብበት ዕለት ነው፡፡ ዓመት


አርቲስት ሙናዬ መንበሩ

ከቀናት የሆናት የመጀመሪያ ልጇ ቶንሲል አሟታል። ከቤት የወጣችው በጠዋት ቢሆንም የእናት አንጀት ነውና በሌሊት ተነስታ ልጇን አጥባና መግባ ነበር፡፡

የልጇ ሕመም ለከፋ ይሰጣል ብሎ የገመተ ባይኖርም፤ ሙናዬን የራሷ መታመምም ሆነ የልጇ መታመም ከሥራዋ ለማስቀረት በቂ አይደሉም፡፡ ከቤቷ ስትወጣ ሀገሩም፣ መንደሩም፣ ቤቷም ሠላም ነበር፡፡ ለነገሩ ለእሷ ሠላም ባይሆንም በሥራዋ ቀልድ አታቅም። እንደታሰበው ማልደው በመሥሪያ ቤታቸው ተሰባስበው ወደ ቤተመንግሥት አመሩ። የጠዋት ፕሮግራማቸው በሠላም ተጠናቀቀ፡፡ ከሰዓቱን ዘወትር መድረክ ሲኖራት እንደምታደርገው ቀድማ በትያትር ቤቱ ቅጥር ተገኝታለች፡፡ ከዚህ በኋላም ነገሮች በሠላም ቀጠሉ፤ እንደወትሮው እራሷን ለትወና አዘጋጀች። ታዳሚው ሠዓቱን አክብሮ የትያትር ቤቱን አዳራሽ ሞልቷል፡፡

ትያትሩ ተጀመረ፤ ሙናዬም የገጸ-ባሕሪ ልብሷን ቀይራ እሷ የምትተውንበት ትዕይንት ሲደርስ ለመግባት በንቃት ትጠብቃለች፡፡ በዚህ መሐል መልዕክት አድርስ ተብሎ ከተላከው የባለቤቷ ታናሽ ወንድም ጋር ተገናኘች። "እናቴነሽ ሞተች" አላት፤ እሷ ግን ጠዋት በሠላም ስማት የተለየቻት ልጅ የምትሞትበት ምክንያት አልታያትምና ልታምነው አልፈለገችም፡፡ ባልደረባዋን ጠርታ "ይሄን ልጅ አንድ በይልኝ" ስትል ወደ መድረክ አመራች፡፡ ባልደረቦቿ ለማጣራት ሞከሩ እውነትም መርዶው እውነት ነው። ትያትሩን ያለሷ መጨረስ የማይታሰብ ነው፡፡ ከመድረክ ስትመለስ በጓደኞቿ ለቅሶ የልጇን ሞት እውነትነት አረጋገጠች፡፡ አብዛኞቹ ትያትሩ ተቋርጦ እንድትሄድ ሀሳብ ቢያቀርቡም እሷ ግን አይሆንም አለች፡፡ "አቋርጬ ብሔድም ልጄ አትመለስም" ስለዚህ ተዋናዩንም ጥበብንም አክብሮ የተገኘውን ሕዝብ አክብራ ለመሥራት ወሰነች፡፡

ሳይደግስ አይጣላም እንዲሉ በትያትሩ ላይም ሙናዬ የምትወክላት ገጸ-ባሕሪ እናቷ ሞታ የምታለቅስበት ቦታ አለና ልጇን አስታውሳ አምርራ አለቀሰች፡፡ እሷን ብሎ፣ ጥበብን አክብሮ ትያትር ቤቱን የሞላውን ሕዝብ እንደፈለገ ከልጄ ሞት አይበልጥብኝም ብሎ ጥሎ የሚሄድ አንጀት አልታደለችም፡፡ እዛው አልቅሳ ወደ ትወናዋ ተመለሰች። ትያትሩ ሲጠናቀቅ ለታዳሚዎች የልጇን ሐዘን ተቋቁማ መሥራቷ ተገለጸ፡፡ ያከበረችው ሕዝብም ከመድረክ መልስ አጅቦ አልቅሶ ልጇን ቀበረ፡፡ ያኔ ታዲያ የሷ ሥራ ወዳድነት ሀገር ምድር ያስገረመ ነበርና ወሬው በወቅቱ የሀገር መሪ የነበሩት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጋ ደረሰ፡፡ በሰሙት የተገረሙት ንጉሡም "ከኃዘኗ ስትጽናና፤ አምጡልኝ አሉ፡፡ እንደተባለውም ስትበረታ ንጉሡ ፊት ቀረበች፡፡ ንጉሡም የ"ምን ላርግልሽ? ጥያቄ አቀረቡ፡፡ እሷም "ደሞዜን ጨምሩልኝ በማለቷ ደሞዟ ከነበረበት 15 ብር ወደ 20 ብር ከፍ ተደረገላት፡፡

ታማ የተሰጣትን ግሉኮስ ነቅላ ወደ ሥራዋ መሄድ ለሷ አዲስ አይደለም፡፡ የታዘዘላትን መርፌ መወጋት ትታ ሥራ ላይ መገኘት ተደጋጋሚ ተግባሯ ነው፡፡ ታዳጊ የሀይስኩል ተማሪ ልጇ በግርግር በተተኮሰበት ጥይት ሞቶ ከባድ ኃዘን ውስጥ ብትሆንም፤ በሠልስቱ ሕዝቡን አክብራ አስቀድሞ የተዋወቀ ትያትር ላይ ተውናለች። በትወናው ዓለም የሙናዬ ልጇ ሞታ መድረክንና ታዳሚን አክብራ መተወን ሲነገር እዚህ ደርሷል። አዘጋጆች አሁን ድረስ በፕሮግራም የሚያረፍድ ተዋናይ ሲገጥማቸው "ሙናዬ የልጇን አስከሬን ቤት አስቀምጣ ትተውናለች። እናንተ እንዲህ በመድረክ ቀልዱ።" እንደሚባል ከሷ ዘመን በኋላ የመጡ ተዋንያን ያነሱታል፡፡ በርካታ ተዋንያን እንደሷ ለመሆን እየሞከሩ የእሷን ትወናዎች ለማምጣት መስታወት ፊት ቆመው ተለማምደዋል፡፡

ሙናዬ በሥራዋ ምክንያት ያልደረሰችበት የሀገራችን አካባቢ የለም፡፡ ከኢትዮጵያ ውጪ ቻይና፣ ሩሲያ፣ ጀርመን፣ ፈረንሳይ፣ ሱዳን፣ ኬንያ፣ ሆላንድ፣ ካናዳ፣ ግብፅ፣ ታንዛኒያ፣ አልጄሪያ፣ ናይጄሪያ ተጉዛ ሥራዋን ካቀረበችባቸው በርካታ ሀገሮች መካከል ይገኙበታል፡፡ በተለይ የፈረንሳይ ጉዞዋ ለየት ያለ ታሪክ አለው፡፡ በወቅቱ ሙናዬ ነብሰጡር ነበረች፤ ይሄ ዜና አለቃዎቿ ጆሮ ይደርሳል፡፡ ያኔ አለቃዋ ቢሮአቸው ጠርተው "እርጉዝ ነሽ አሉ" ሲሉ፣ እሷ "ማ እኔ? ኸረ እርጉዝ አይደለሁም።" ብላ በመካዷ "ሄዳ ትመርመር ተባለ፡፡ የቢሮ መኪና ተዘጋጅቶና አብሯት የሚሄድ ሰው ተመድቦ ወደ ሕክምና ተቋም አመራች፡፡ ወቅቱ "ጉብልዬ" የተሰኘው ዘፈኗ የገነነበት ወቅት ነበርና ሲስተሯ ገና እንዳየቻት "ምነው ምን እንርዳሽ?" አለቻት፡፡ ያኔ የውጭ እድል ገጥሞኝ መሥራት እየቻልኩ "ነፍሰጡር ናት ብለው ሊያስቀሩኝ ነውና ምን ይሻላል ስትል ተነፈሰች፡፡ ሲስተሯም ከዶክተሩ ጋር ተነጋግረው "ነፍሰጡር አይደለችም የሚል ማስረጃ ተሰጣት፡፡

ማስረጃውን ያዩት አለቃዋም አይ የሰው ወሬ ብለው ተገርመው ወደ ፈረንሳይ እንድታቀና ተደረገ። ለፈረንሳይ ተዘጋጅታ የነፍሰጡርነት ልብሷን በሻንጣ ሸክፋ ተጓዘች። ፈረንሳይ ገብተው ማረፊያ ክፍል እንደተሰጣቸው ከአወቁ አላወቁብኝ ልብሶች ተላቃ የነፍሰጡር ዘና የሚያደርግ ልብሷን ለበሰች፡፡ ያኔ ያዩትን ያለመኑት አለቃዋ ምነው ሙናዬ ምነው እንደዚህ ጉድ ታደርጊኝ አለ፡፡ እሷ ማን ናትና አታርግዙ አትውለዱ የሚል ሕግ አለ አላወኩም ነበር ሆነ መልሷ፡፡ በይ አሁን ትያትር ነው የምትሠሪው እንደመጣሻት አርገሽ ሆድሽን አጥፊ ተባለች እሷም ወደ ኩርሲዋ ተመለሰች፡፡

ሙናዬ እንደሷ ሁለገብ ከነበረችው በላይነሽ አመዴ (ኩንስንስ) ጋር የነበራቸው ወዳጅነት የተለየ ነበር። ስለሷ ስታወራ "በላይዬ አመዴ፣ ልቅም እንደስንዴ፣ ይወድሻል ሆዴ።" ከምትላት በላይነሽ ጋር በክፉም ሆነ በደግ፤ እንዲሁም በሥራ የማይለያዩ ወዳጆች ነበሩ፡፡ እሷ ያኔ በሕይወት ሳለች ጊዜ የማይለውጣት ባልንጀራዬ ብቻ ሳትሆን እህቴ ናት ትላት ከነበረው ኩንስንስ ጋር በርካታ ሥራዎችን በጋራ ሠርተዋል፡፡ ተጫዋች ናት። እሷ ካለች ሳቅ መፍጠርን፣ ሰው ማዝናናትን ተክናበታለች። ለዛም ይመስላል የሚያኮርፍ ሰው አልወድም ትላለች። በአንድ ወቅት በሬዲዮ በእንግድነት በቀረበችበት ወቅት ከመጀመሪያ የትዳር አጋሯ ጋር የተለያዩት እራሱ በኩርፊያውና በቀናተኛነቱ መሆኑን ተናግራ ነበር። የምትፈልገው ሕይወት የሳቅና የፈገግታ መሆኑን ትናገራለች፡፡ በሕይወቴ የሚያኮርፍ ሰው አልወድም ትል ነበር፡፡

አሁን አርቲስቶች ብራንድ አምባሳደር ሆነው በሚሊዮኖች ለመከፈል ቢደርሱም እሷ ግን ከ44 ዓመት አገልግሎት በኋላ ደሞዟ 900 ብር ነበር፡፡ በመሐል ኑሮዋን ለማሸነፍና ተጨማሪ ገቢ ለማግኘት ካዛንችሽ መጠጥ ቤት ከፍታ ነበር፡፡ በቤቱ የሙዚቃ መሣሪያ ባይኖርም ባንኮኒውን እየመታች ትዘፍን ነበር። ገበያውም ደህና የነበረ ቢሆንም ከመሥሪያ ቤቷ ሁለት ሥራ መሥራት አይቻልም የሚል ደብዳቤ ሲደርሳት እርግፍ አርጋ ተወችው፡፡

የተሰጣትን ገጸ-ባሕሪ ጥንፍፍ አርጋ እስከጥግ ትተውናለች፤ ስለዚህም እንዲህ ብትጨምር ይሄን ብታስተካክል ይሉ አስተያየት አይሰማም፡፡ ሀገር ፍቅር እየሠራች የጡረታ መውጫ እድሜዋ ቢደርስም መሥሪያ ቤቷ "ስለምትፈለጊ . . . በሚል የጡረታ እድሜዋ እንዲራዘም አድርጓል፡፡ ከሙናዬ በፊት የትዳር አጓሯ ለበርካታ ጊዜ ታሞ ነበር፡፡ እሱን ስታስታምም ስለሱ ስታስብ ያልተጠበቀችው እሷ ቀድማ አረፈች፡፡ የቅርቦቿ በሽታዋ የሦስት ቀን ብቻ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ እሱም ቢሆን እየሳቀች፤ እየተጫወተች ነሐሴ 10 ቀን 1995 ዓ.ም ሳትታሰብ ይችን ምድር ተሰናበተች፡፡ ያኔ በ15 ብር ደሞዝ ሥራ የጀመረችው ሙናዬ ከ44 ዓመት አገልግሎት በኋላ ደሞዟ 900 ብር ደርሶ ነበር፡፡

በትወና ከተሳተፈችባቸው ከመቶ በላይ ሥራዎች መካከል "የቀለጠው መንደር"፣ "የጠለቀች ጀንበር"፣ "ታጋይ ሲፋለም"፣ "አንድ ቃል"፣ "የቆጡን አወርድ ብላ"፣ እና "የቬኑሱ ነጋዴ" ይገኙበታል፡፡ ሙናዬ ሁለት የሙዚቃ ካሴቶችን ያወጣች ሲሆን፣ "ጉብልዬ" እና "ትዝታዬ"ተወዳጅ ሥራዎቿ ናቸው፡፡ ልጇን አጥታ፣ ኃዘኑን ተቋቁሚ በሠራችበት የሀገር ፍቅር መድረክ ልጇን በክብር ድራባታለች፡፡ የሀገር ፍቅር ትያትር ቤት ለሙያዋ ለነበራት ክብርና ፍቅር መታሰቢያዋ ይሆን ዘንድ ሐውልቷን በጊቢው ውስጥ አቁሞላታል፡፡

ሰኔ 3 ቀን 2015 ዓ.ም ብዙ ነገር በሆነችበት የሀገር ፍቅር አዳራሽ "ዝክረ ሙናዬ መንበረ የተሰኘ የ20ኛ ዓመት የሙት ዓመት መታሰቢያ ተደርጎላታል። ዝግጅቱ "ኅብር ግኝት የኪነጥበብ ማኅበር በተሰኘ የባለሙያዎች ስብስብ የተዘጋጀ ነበር፡፡ የመጀመሪያ ልጇን በጊዜ የተነጠቀችው ሙናዬ፤ ከሷ ውጪ አምስት ልጆች አፍርታ ነበር፡፡ ሆኖም አንድ ወንድ ልጇ ከሷ ቀድሞ ሲሞት፤ እሷ እያለች በሕይወት የነበረው ሌላ ወንድ ልጇም አሁን በሕይወት የለም፡፡ ሦስት ሴት ልጆቿ ሥሟን ለማስጠራት የአቅማቸውን እየሞከሩ ነው፡፡ በተለይ አርቲስት ሐረገወይን በቀለ በሷ ሙያ ከመማረኳም ባሻገር ዝክረ ሙናዬን ያዘጋጀው ኅብር ግኝት የኪነጥበብ ማኅበር አባል በመሆን የእናቷን ሥም ለማስታወስ ትጥራለች፡፡

ሙናዬ ከተለየችን ጊዜው 20 ዓመታትን ቢሻገርም፣ በቅርብ ጊዜ በተፈጠረው የቲክቶክ መንደርም የሷን ቀደምት ሥራዎች በርካቶች የሚቀባበሉት ተወዳጅ ተዋናይ ነበረች፡፡ "ሙናዬ መንበሩ የሚለው ሥም ሠው በተሠማራበት የሥራ መስክ በትጋት ካገለገለ ሥሙ ከመቃብር በላይ እንደሚሆን ማሳያ የሆነ ሥም ነው፡፡

# "ከብልህ ደጃፍ ደረሰኝ ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ያለበትን ገቢ የሚያሳጡ በርካታ ከደረሰኝ ጋር የተያያዙ የማጭበርበር ተግባራት ይፈጸማሉ::

ዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2011 ይፋ ያደረገው ጥናት እንደሚያመለክተው፤ ኢትዮጵያ ለሕግ ተገዥ ባለመሆን ምክንያት ለጂዲፒዋ ከታክስ ማግኘት የሚገባትን 4 ነጥብ 5 በመቶ አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችል ገቢ በየዓመቱ ታጣለች::

የአንደኛው ዓለም ዜጎች "ሞትና ግብር የማይቀር ነው" የሚል ብሂል አላቸው:: በሦስተኛው ዓለም ግን ግብር ከመክፈል ይልቅ ሞቱን የሚመርጠው ብዙ ነው:: እኛ ሀገር ደግሞ ነገሩ ይብሳል:: "ከሞኝ ደጃፍ ደረሰኝ ይቆረጣል" ብለው ደረሰኝ ደንበኞች እጅ እንዳይደርስ የሚያደርጉ ነጋዴዎችና አገልግሎት ሰጪዎች ቁጥር ቀላል አይደለም:: እርግጥ ነው "ከብልህ ደጃፍ ደረሰኝ ይቆረጣል" ብለው ህግን አክብረው ደረሰኝ የሚቆርጡ ብዙ ሀገር ወዳዶች መኖራቸውም አይካድም::

ወዲህ ደግሞ ሸማቹ ማህበረሰብ ለፈጸመው ግዢና ላገኘው አገልግሎት የተጠየቀውን ከፍሎ ከመሄድ ባለፈ ደረሰኝ የመጠየቅ ልምዱ እምብዛም ነው::

ወጣት ሳምራዊት ነጋ በአዲስ አበባ ከተማ ኗሪ ናት:: በተለያዩ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ስትገለገል አብዛኞቹ ሳትጠይቅ ደረሰኝ እንደሚሰጧትና ዋጋውን ተመልክታ ክፍያ እንደምትፈጽም ትናገራለች:: በአንጻሩ በሸመታ ወቅት ከሱፐርማርኬቶች በቀር ደረሰኝ የሚሰጡ የንግድ ተቋማት እንደማያጋጥሟትና እርሷም ዋጋው እንዲቀንስላት ትኩረቷን ክርክር ላይ ስለምታደርግ ደረሰኝ መጠየቅን እንደማታስበው ትገልጻለች::

የ52 ዓመቱ ጎልማሳ አቶ ኃይሌ ታደሰ በበኩሉ፤ ግዢ ሲፈጽምም ሆነ አገልግሎት ሲያገኝ ደረሰኝ ሳይቀበል ፈጽሞ ክፍያ እንደማይፈጽምና በዚህም ምክንያት ከአንዳንድ ነጋዴዎች ጋር ግጭት ውስጥ እስከመግባት እንደደረሰ ይናገራል::

በሀገራችን ደረሰኝ ከመስጠትና ከመቀበል ጋር ተያይዞ የሚስተዋለው ችግር ለህግ ተገዢ ካለመሆን ጋር የሚገናኝ ነው:: በዘርፉ በተለያየ ጊዜ የወጡና የተሻሻሉ የህግ ማዕፎች በመኖራቸው የህግ ክፍተት አለ ለማለት ይቸግራል::

የተጨማሪ እሴት ታክስን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር - 609/2001 አንቀፅ 2 (10) መሰረት ማንኛውም ታክስ ከፋይ ላከናወነው ሽያጭ ወይም ለሰጠው አገልግሎት ለደንበኛው ወድያውኑ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ አለበት:: በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 47ሀ (9) (ሐ) ስር ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ያለበት ግብር ከፋይ "ደረሰኝ የማይሰጥ ከሆነ አይክፈሉ" የሚል የፅሁፍ ማስታወቂያ በሚታይ ቦታ በግልፅ ለጥፎ ካልተገኘ አንድ ሺህ ብር እንደሚቀጣ ይደነግጋል።

በተሻሻለው የንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 17 (1) ማንኛውም ነጋዴ ለሸጠው እቃ ወይም አገልግሎት ለሸማቹ ወድያውኑ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ እንዳለበት ተገልጿል::

የፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀፅ 120 (1) እና 131 (1) (ለ) ላይ ማንኛውም ደረሰኝ የመቁረጥ ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ ያለደረሰኝ ግብይት ካከናወነ ወይም አገልግሎት ከሰጠ ከ2 እስከ 5 ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራትና የገንዘብ መቀጮ እንደሚቀጣ በግልፅ ደንግጓል።

በተጨማሪ ግብይት ሳይፈፅም ደረሰኝ የሚቆርጥ ግብር ከፋይም ሆነ የሚቀበል ሰው ከ7 እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራትና በገንዘብ መቀጮ እንደሚቀጣ ተጠቅሷል። ታክስ ከፋዩን ያለደረሰኝ ሽያጭ ወይም አገልግሎት እንዲሰጥ የረዳ፣ ያበረታታ፣ የገዘ እና ያነሳሳ ወይም የተመሳጠረ ማንኛውም ግለሰብም ዋና ወንጀል አድራጊው (ግብር ከፋዩ) በሚቀጣበት ቅጣት ልክ እንደሚቀጣ ይደነግጋል።

በገቢዎች ሚኒስቴር የታክስ መረጃና ሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ራቢያ ይማም ደረሰኝ ከመስጠትና ከመቀበል ጋር ተያይዞ የሚስተዋለው ሰፋ ያለ ችግር ምክንያቶች ሁለት መሆናቸውን ይናገራሉ::

የመጀመሪያው ህብረተሰቡ መብቱን አውቆ አለማስከበሩ ነው የሚሉት ዳይሬክተሯ፣ ሁለተኛው የደረሰኞችን ትርጉም አለማወቅ መሆኑን አመላክተው፤ "ደረሰኞች የዕቃውን ዋጋ ገልጻውልን ብቻ የሚያልፉ ሳይሆኑ የከፈልነው ገንዘብ መንግሥት ጋር መድረሱን የምናረጋግጥባቸው ናቸው" ይላሉ::

አክለውም፣ አንዳንድ ህገወጥ ነጋዴዎች ሸማቹ ደረሰኝ በሚጠይቃቸው ጊዜ አልሸጥም ወይም አገልግሎት አልሰጥም በማለት ለማሸማቀቅ እንደሚሞክሩ ጠቁመው፤ ሸማቾች በአዋጅ የተሰጣቸውን ስልጣን በደንብ ተገንዝበው ወደ ውስጣቸው ስላላሰረጹ 'እቃውን ወይም አገልግሎቱን አግኝቻለሁ ለምን እጨቃጨቃለሁ' ብለው ትተው እንደሚሄዱ ይገልጻሉ::

ሳያውቁ ወንጀል በሆነው ተግባር ላይ ተሰማርተው የሚገኙና ካሳወቅናቸው በኋላ ወደ ሥርዓቱ የሚመጡ ብዙ ነጋዴዎችና አገልግሎት ሰጪዎች አሉ ያሉት ዳይሬክተሯ፤ በአንጻሩ ደግሞ አሻፈረኝ ብለው ከታክስ ራሳቸውን ለመሰወር፤ በገበያ የበላይነትን ለማግኘት እንዲሁም በተለያየ ምክንያት ደረሰኝ መቁረጥ የማይፈልጉ ነጋዴዎችና አገልግሎት ሰጪዎች እንዳሉ ይናገራሉ::

በታክስ አስተዳደር አዋጁ አንቀጽ 120 መሰረት ደረሰኝ ሳይቆርጥ ግብይት ያከናወነ ሰው ግብይቱ ከ100 ሺ. ብር በታች ከሆነ ከ25 ሺ. ብር እስከ 50 ሺ. ብር የሚደርስ አስተዳደራዊ ቅጣትና ከሦስት እስከ አምስት አመት የሚደርስ እስራት እንደሚቀጣ ያመላከቱት ራቢያ፤ "ከ100 ሺ. ብር በላይ የሆነ ግብይት ደረሰኝ ሳይቆርጥ የሚፈጽም ደግሞ ያከናወነውን ሽያጭ ትልቅ ዋጋ እንዲከፍልና ከሰባት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ እስራት እንዲቀጣ ይደረጋል" ይላሉ::

አያይዘውም፤ "ሕገወጦችን የማንቀጣ ከሆነ አስተምረንና ገስጸን ግንዛቤ አስጨብጠን ወደሥቀራ የምናስገባቸው ነጋዴዎችና አገልግሎት ሰጪዎች ይቀጭጫሉ፤ ከገበያም ይወጣሉ" በማለት ለሕጋዊ ነጋዴዎችና አገልግሎት ሰጪዎች ጥበቃ ማድረግ ስለሚያስፈልግና ሀገርም ታክስ ማግኘት ስላለባት በአዋጅ የተቀመጡት እርምጃዎች እንደሚወሰዱ ይገልጻሉ::

ሸማቹ ማህበረሰብ ደረሰኝ መጠየቅን ባህል እንዲያደርግ ገቢዎች ሚኒስቴር በቀጣይ አዲስ አሰራር እንደሚከተል በአመላከቱበት ንግግራቸው፤ "ሸማቾች ለከፈሉት ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሲጠይቁ በደረሰኝ ቁጥሩ የሎተሪ እጣ ውስጥ ገብተው ለሽልማት የሚታጩበትንና የታክስ ተመላሽ የሚያገኙበትን በቴክኖሎጂ የተደገፈ አሰራር ለመተግበር እየሰራን ነው" ሲሉ ሚኒስቴር መስሪያቤታቸው የገቢ አሰባሰብ ሥርዓቱን ለማሳለጥ ወጥኖ እየሰራ ስለመሆኑን ጠቁመዋል::

የገቢዎች ሚኒስቴር ውጥን ከተሳካ ደረሰኝ ከእጁ የማያደርሱት ነጋዴዎች ደጅ ድርሽ የሚል ሸማች አይኖርም:: "ከብልህ ደጃፍ ደረሰኝ ይቆረጣል" ባይ ነጋዴዎችና አገልግሎት ሰጪዎችም ይበዙልናል::

# ዓለም አቀፍ



## ኢርዶጋን አሜሪካ እና ዩኬ ቀይ ባህርን ወደ "ደም ባህር" ለመቀየር እየሞከሩ ነው ሲሉ ከሰሱ

ኢርዶጋን አሜሪካ እና ዩኬ ቀይ ባህርን ወደ "ደም ባህር" ለመቀየር እየሞከሩ ነው ሲሉ ከሰሱ።የቱርኩ ፕሬዚዳንት ጣይብ ኢርዶጋን አሜሪካ እና ዩኬ ቀይ ባህርን ወደ "ደም ባህር" ለመቀየር እየሞከሩ ነው ሲሉ ከሰዋል።ኢርዶጋን፣ አሜሪካ እና ዩኬ በየመን ያደረጉት ድብደባ ተመጣጣኝ አይደለም ነው ብለዋል።

በምዕራባውያን የሚዘወረው ኔቶ አባል የሆነችው ቱርክ፣ የፍልስጤሙን ታጣቂ ቡድን ለማጥፋት በጋዛ ጦርነት እያካሄደች ያለችውን እስራኤልን አጥብቃ አውግዛለች፣ የእስራኤልን ዘመቻ ደግፈዋል ያለቻቸውን ምዕራባውያንንም ተችታለች።

አሜሪካ እና ዩኬ የየመኑ ሀውቲ አማጺ በቀይ ባህር የመርከብ እንቅስቃሴ ላይ ላደረሰው ጥቃት ለመበቀል በየመን ስላደረሱት ድብደባ የተጠየቁት ኢርዶጋን ጥቃቱ ተመጣጣኝ አይደለም ብለዋል።ኢርዶጋን "የደረሰው ጥቃት ተመጣጣኝ ያልሆነ የኃይል እርምጃ ነው" ሲሉ ተናግረዋል።

ኢርዶጋን "በአሁኑ ወቅት ቀይ ባህር የደም ባህር ለማድረግ እየሞከሩ ነው፣ የመን ከሀውቲዎች ጋር በመሆን ሁሉንም ኃይሏን በመጠቀም፣ ለአሜሪካ እና ለዩኬ አስፈላጊውን ምላሽ መስጠት አለባት" ብለዋል።አለም አቀፍ እውቅና ያለውን የየመን መንግሥት የምትደግፈው ቱርክ፣ በእሱ እና አብዛኛውን የየመን ክፍል በተቆጣጠሩት የሀውቲ ታጣቂዎች መካከል እርቅ የመፍጠር አላማ ያለውን በተመድ የሚመራውን ሂደትም ትደግፋለች።

ኢርዶጋን የሀውቲ ታጣቂዎች ከአሜሪካ እና ከዩኬ የተቃጣባቸውን ጥቃት ስኬታማ በሆነ መንገድ መከላከላቸውን ከበርካታ ምንጮች መስማታቸውን እና ኢራንም ሊቃጡባት ከሚችሉ ጥቃቶች ለመከላከል መዘጋጀቷን ተናግረዋል።የሀውቲ ታጣቂዎች በቀይ ባህር የሚንቀሳቀሱ መርከቦችን የሚያጠቁት ለፍልስጤሙ ታጣቂ ቡድን ሀማስ ድጋፍ ለማሳየት መሆኑን ሲገልጹ ቆይተዋል።

የቀይ ባህርን የመርከብ እንቅስቃሴ ሰላማዊ አደርጋለሁ የምትለው አሜሪካ ሌሎች ሀገራትን በማስተባበር በሀውቲዎች ላይ ጥቃት መክፈቷን አል ዐይን ዘግቧል።

## ሰሜን ኮሪያ ከ2020 ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ ጎብኚዎችን ልትቀበል ነው




ሰሜን ኮሪያ ከ2020 ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ ጎብኝዎች ልትቀበል ነው። ሰሜን ኮሪያ በኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት ድንበሯን ከዘጋችበት ከፈረንጆቹ 2020 ወዲህ የሩሲያ ጎብኝዎች ቡድን ወደ ሰሜን ኮሪያ በመግባት የመጀመሪያው ለመሆን ተቃርበዋል።

በወረርሹ ወቅት ከባድ የሚባል የድንበር ቁጥጥር ካደረጉ ሀገራት ውስጥ ቀዳሚ ሰሜን ኮሪያ እስካሁን ድረስ ድንበሯን ለውጭ ጎብኝዎች ሙሉ በሙሉ ሳትከፍት ቆይታለች።

ይህ ጉዞ የተመቻቸው፣ ከሰሜን ኮሪያ ጋር የምትዋሰነው የሩሲያዋ የሩቅ ምስራቅ ፕሪሞርስካይ ክራይ ግዛት መሪ ባለፈው ወር በፒዮንግያንግ ውይይት ለማድረግ ጉብኝት ካደረጉ በኋላ ነው።

ሮይተርስ እንደዘገበው፤ ጎብኚዎቹ ፒዮንግያንግን እና ስካይ ሪዞርትን ጨምሮ በተለያዩ ቦታዎችለአራት ቀናት ይቆያሉ።የሩሲያውያን ጉብኝት በተለየ ሁኔታ የተመቻቸ መሆኑን ዘገባው ጠቅሷል።የሩሲያው ፕሬዝደንት ቭላድሚር ፑቲን እና የሰሜን ኮሪያው መሪ ኪም ጆንግ ኡን ባለፈው መስከረም ወር በምስራቃዊ ሩሲያ በተገናኙበት ወቅት፣ በወታደራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ለመተባበር ቃል ገብተው ነበር።

ከሰሜን ኮሪያ ጋር በሚደረጉ የንግድ እንቅስቃሴዎች የተጣለው ተመድ የጸጥታው ምክርቤት ማዕቀብ፣ በቱሪዝም ላይ ተጽእኖ አላሳደረም። ወረርሽኙ ከመከሰቱ በፊት ሀገሪቱ ከቻይና ጎብኚዎች ብቻ 175 ሚሊዮን ዶላር ታገኝ እንደነበር ጠቅሶ አል አይን ዘግቧል፡፡

# “የማዕድን ዘርፍ አሁንም በሀገሪቱ ጂዲፒው ላይ ያለው ድርሻ ብዙም ለውጥ የለውም”

ኢንጂነር ሀብታሙ ተገኝ
የማዕድን ሚኒስትር

በሀገሪቱ የማዕድን ዘርፍ ተስፋና ተግዳሮቶች ዙሪያ የማዕድን ሚኒስትሩ ኢንጂነር ሀብታሙ ተገኝ ከትናንት በስቲያ ከጋዜጠኞች ጋር ያደረጉትን ቃለ ምልልስ ሙሉ ቃል እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡

**ጥያቄ፡- እንደሚታወቀው መንግሥት በአስር ዓመቱ የልማት መሪ እቅድ ውስጥ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች መካከል የማዕድን ዘርፍ አንደኛው እንደሆነ ይታወቃል። ዘርፉ አሁን ላይ ያለው አፈፃፀም ምን ይመስላል?**

**ኢንጂነር ሀብታሙ፡-** እንግዲህ ይህ ዘርፍ ብዙ ያልተጠቀምንበትና እንደ አዲስ የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ምሰሶ ሆኖ የመጣ ስለሆነ ቀድሞ መሠራት የነበረባቸውን ብዙ ሥራዎች ጭምር አሁን ነው ገና እየሠራን ያለነው። ምናልባት ሰምታችሁ ከሆነ ከሕግ ማስተካከያ ጀምሮ ተቋማትን በዚህ መንገድ መገንባትን ጨምሮ በዚህ ዘርፍ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የትኩረት መስኮችን ባካተተ መልኩ ብዙ ሥራዎች እየተሠሩ ነው።

ዘርፉ ወዲያው ለማምረት ዝግጁ ያልነበረ ዘርፍ ነው። ለማምረት የሚመቹ ነገሮችንም አብረን እየሠራን ነው። ሀገሪቱ ካላት አቅም አኳያ አሁን ላይ ያለው አፈፃፀም እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ያለውን ሀገራዊ አቅም እና በተጨባጭ ሊመረት የሚችለውን ታሳቢ አድርገን እየሠራን ነው።

የዘርፉ ዋና ዋና ትኩረቶች ሦስት ነገሮች ናቸው። አንደኛው የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት ሲሆን፤ ሁለተኛ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ማስቀረት ነው። የማዕድን ዘርፍ ለሌላው የልማት አካል አምራች የሚባለው ዘርፍ ነው። ምናልባትም ብዙ ነገሩን ከሌላ ጋር ጥገኛ ሳያደርግ ሊያመርት የሚችል፤ ለሌሎች የግብር፣ የኢንዱስትሪ እና የኮንስትራክሽን ግብዓት መሆን የሚችል ዘርፍ ነው። በዚህ ዘርፍ ላይ የምንጠቀማቸውን ከውጭ የሚገቡ ምርቶች በሀገር ውስጥ መተካት አንዱና ዋነኛው የትኩረት አቅጣጫ ነው። ሦስተኛው የሥራ ዕድል መፍጠርና አካባቢንም ጠብቆ ማስኬድ ነው። እነዚህ በቀጣይ የሚከናወኑ ዋና ዋናዎቹ የትኩረት መስኮች ናቸው።

የውጭ ምንዛሪን ከማስገኘት አኳያ ለረጅም ዓመታት ዋና ትኩረት ተደርጎ እንደ ባሕል የሚታየው ወርቅ ነው። ነገር ግን ወርቅ ብቻ ሳይሆን እንደሀገር ሌሎች ብዙ ማዕድናት አሉን፡፡ ወርቅን ስናይ ወርቅ በሁለት መንገድ ነው የሚመረተው። አንደኛው በባሕላዊ መንገድ በየክልሉ በሚገኙ ማኅበራት የሚመረተው ነው፤ ሁለተኛው ደግሞ በፋብሪካ ደረጃ የሚመረተው ነው ።

በፋብሪካ ደረጃ በአሁኑ ግዜ ሥራቸውን እየጨረሱ ያሉ፤ እንዲሁም ወደ ሥራ ገብተው እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ያሉ አንድ አምስት ተቋማት አሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ በፋብሪካ ደረጃ ወርቅ ሲያመርት የነበረው ትልቁ ሜድሮክ ነው። ሜድሮክ ሕገ ደንብን ከመንግሥት ከወሰደ ጀምሮ በማምረት ላይ ይገኛል። ሌላው በቅርብ ጊዜ ወደ ዘርፉን የተቀላቀለው ኢዛና ነው እሱም ምርቱ ትንሽ ነው። ከዚህ ውጪ የሆኑ ሌሎች ትልልቅ ፋብሪካዎች ገበያውን ሊቀላቀሉ እየመጡ ነው። አሁን ባለው ሁኔታ ለማምረት ጫፍ ላይ የደረሱ ያሉ ሲሆን የተወሰኑት ደግሞ ገና ከዓመት በኋላ ወደ ሥራ የሚገቡ ናቸው።

የሀገራችን የወርቅ ምርት ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ የምንችለው ከላይ በዘረዘርናቸው ሰፊና ተደራሽነት ባለው የገበያ አማራጮች ላይ ሲመሠረት ነው። ከዚህ በፊት በአብዛኛው ሊባል በሚችል ሁኔታ ምርቱ ይገኝ የነበረው በባሕላዊ መንገድ ስለነበረ ብዙ ችግሮችን ሲያስተናግድ ቆይቷል፡፡ አሁንም ከጥቂት ክልሎች ከሚመጣው ውጪ በአብዛኛው ችግር ያለበት እንደሆነ ደፍሮ መናገር ይቻላል፡፡ ይህም በኮንትሮባንድ እና በተለያዩ ሕገወጥ ንግዶች ሰለባ በመሆን ሀገር ማግኘት የነበረባትን እንዳታገኝ እክል ፈጥሯል፡፡ ከዛ ውጪ ግን በፋብሪካ ደረጃ ያለው ምርትና እንቅስቃሴ ተስፋ ሰጪና ዘርፉን የሚያነቃቃ እንደሆነ ማየት እንችላለን።



እንደ እውነቱ ከሆነ አፈፃፀማችን አሁንም ያሰብነውን ያህል አይደለም። ብዙ ጥያቄዎች የሚነሱበት ነው፡፡ ሆኖም ግን ወደሥራ ለመግባት በመጠባበቅ ላይ ያሉ አዳዲስ ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው ወደ ሥራ ሲገቡ ኢትዮጵያ በዓመት የምታገኘውን ወርቅ በአጭር ጊዜ ውስጥ ማምረት የሚችሉ ናቸው። ከዚህ ጋር በተያያዘ የተቋማት ግንባታን ጨምሮ እንደ ሀገር ለዚህ ዘርፍ ትኩረት የተሰጠው የማዕድን ካውንስልን ጨምሮ ብሔራዊ የማዕድን ካውንስልን ማቋቋም ነው።

ካውንስሉ ብዙ ተቋማትን የያዘ ነው። በዚህ ዘርፍ ላይ ያሉትን የሀገሪቱን ችግሮች ሊፈታ የሚችል በጣም በትልቅ ደረጃ የሚታይ ነው። ብዙ እርሾ ስላልነበረው ቶሎ ብለን ለማምረትና ከፍ ያለ አፈጻጸም ለማስመዝገብ አልቻልንም። ዘርፉ በባሕሪውም ብዙ ዓመት ይወስዳል፤ ማዕድን የማፈላለጉ ሁኔታ ብቻውን አድካሚና አንዳንድ ቦታ ላይ እስከ አስር ዓመት የሚቆይ ጊዜ የሚወስድ ነው። ከዚህ ሂደት ጋር በተያያዘ የኦጋዴን ቤንዚን እንኳን ስንት ዓመት እንደፈጀ የምታውቁት ነው። ዓመታትን የሚፈለግ፣ በጣም ብዙ ካፒታል የሚያሻው የሀገርን ሠላም ጭምር የሚፈለግ ዘርፍ ስለሆነ በቶሎ ተጠቃሚ የምንሆንበት ዘርፍ አይደለም።

**ጥያቄ ፡- ዘርፉን በማዘመንና ሕጋዊ ሥርዓትን ተከትሎ እንዲያመርት፤ በዚህም ሀገሪቱ የምታገኘውን ገቢ በማሳደግ በኩል ባለፉት ዓመታት የተሠራው ሥራ ምን ይመስላል?**

**ኢንጂነር ሀብታሙ፡-** ወርቅ በባሕላዊ መንገድ ነው ሲወጣ የነበረው፡፡ ነገር ግን ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ ደረጃ ግንባር ቀደም የሚያደርጋት የፖታሽ ሀብት አላት፡፡ በሚፈለገው ደረጃ ማምረት ቢቻል ትልቅ የገቢ ምንጭ መሆን የሚችል ነው፡፡ ከፖታሽ ቀጥሎ ሊቲየም፤ ታንታለም የዘመኑ ግሪን ኢነርጂና ይህን ተከትሎ ያሉ ማዕድናት አሉ፡፡ እነዚህን ሁሉ ማዕድናት ማየት ይገባል፡፡

የወርቅ ማውጣት ሥራ በባሕላዊ መንገድ የተመሠረተ ስለነበር አልፎ አልፎ ባሉ አለመረጋጋቶችና የኮንትሮባንድ ንግድን ተከትሎ ችግሮች አሉ፡፡ ችግሮችን ለመቅረፍ ብሔራዊ ካውንስል ተቋቁሞ እየተሠራ ነው፡፡ በጣም የከፉ የሚመስሉ ችግሮች መጥተው ነበር ብዙ የማይታወቁ የውጭ አገር ዜጎች ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ገብተው በባሕላዊ የወርቅ ማውጣት ሥራ ተሠማርተው ብዙ ችግር ፈጥረዋል፡፡

በተሠራው ሥራ እነዚህን ችግሮች ሥርዓት እንዲይዙ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን በሀገር ውስጥ ተደራጅተው የሚያመርቱ ዜጎች አሁንም የሚፈለገውን ያህል የወርቅ ምርት ወደ ብሔራዊ ባንክና የሀገሪቱ ቋት እያመጡ አይደለም። ስለዚህ የወርቅ ምርትን በተገቢው መንገድ ወደ ብሔራዊ ባንክ እንዲገባ የውጭ ሀገራት ተሞክሮ የሚያሳየው የራሱ የሆነ የፀጥታ አካል እንደሚያስፈልገው ነው፡፡

ሥራው የሚጀምረው ትኩረት ከመስጠት ስለሆነ ሥርዓት ባለው መንገድ እንዲመራ የተጀመረው ሥራ አበረታች ነው፡፡ ከገቢ አኳያ የተጀመሩ ተተኪ ምርት የማምረት ሂደት ጥሩ ነው፡፡ ከሰል፣ ሲሚንቶ በብዛት እየተመረተ ነው። ማዳበሪያም ለማምረት ትልቅ ኢንቨስትመንት ስለሚፈልግ ቅድመ ሥራዎች እየተሠሩ ነው፡፡ ግብዓት የሚሆኑ የተፈጥሮ ጋዝ ምርት ከማምረት ጀምሮ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ነው፡፡ ጠቅለል አድርገን ስናየው የእስካሁኑ እርምጃችን ተስፋ ሰጪ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነ አመላካች ነው፡፡

**ጥያቄ፡- በ2022 በአጠቃላይ ከአንድ ፐርሰንት በላይ ያልዘለለ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፤ ይህን ከማሳደግና በተለይም በዘርፉ ለሚከናወኑ ሥራዎች ማሽነሪዎችን ከማስገባት ጋር በተያያዘ ያለው ውጤት እንዴት ይገለጻል?**

**ኢንጂነር ሀብታሙ፡-** ቅድም እንዳልኩት ነው። በአንድ ዓመትና በሁለት ዓመት ጫፍ ላይ መድረስ አይቻልም፡፡ በመንግሥት ትኩረት ተሰጥቶት ለረጅም ዓመት የሚሠራ ነው፡፡ በእርግጥ አንዳንዶቹ በአጭር ጊዜ ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባውን ያህል ያልተሰጣቸው፣ እንደ ወርቅ ያሉ ፋብሪካ የሚያስፈልጋቸው ማሽነሪዎች ለረጅም ዓመታት በፍለጋ የቆዩ ናቸው፡፡

እነዚህ በፍለጋ ላይ ያሉ ተቋማት ሥራ ሲጀምሩ እንደ ሀገር የሚፈለገውን ምርት ያመርታሉ፡፡ የታወቀ ሊገመት የሚችል በዘላቂነት ሊገኝ የሚችል ምርት ማግኘት ትልቁ ችግር ነው፡፡ እነዚህ ተቋማት ወደ ሥራ ሲገቡ፤ የወርቅ ምርት እንደ ሀገር ስናገኝ የነበረውን ብቻቸውን ያመርታሉ፡፡

አሁን ትልቅ ችግር እየሆነ ያለው የታወቀ፣ ሊገመት የሚችል፣ በዘላቂነት የሚገኝ ምርት ማግኘት ነው። መንግሥት በብሔራዊ ባንክ በኩል የሆነ ማሻሻያ ሲያደርግ የሆነ ሰሞን ላይ በጣም ትልቅ ወርቅ ይመጣል። ጥቁር ገበያው ላይ ያለው ነገር ሲሰፋ ደግሞ መልሶ ይጠፋል።

ባሕላዊ ምርቱ እና የመሳሰሉት ላይ እንደዚህ አይነት ነገር አለ፡፡ አሁንም ጂዲፒው ላይ ያለው ድርሻ ብዙ ለውጥ የለውም፡፡ ነገር ግን ምናልባት በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት በጣም ከፍተኛ የሆነ ሼር (ድርሻ) ይኖረዋል። ቅድም ባልኩት መንገድ ሥራዎች እየተሠሩ ስላሉ ማለት ነው፡፡ አሁን ግን ምናልባት ባለፈው ዓመት ላይ የነበረውን ያህል ውጤት የለውም። ተከታታይ ጠንካራ ሥራዎች ግን እየተሠሩ ነው፡፡

አሁን ወርቁም ሌሎችም የከበሩ ማዕድናትም ተደማምረው የዓመት ኤክስፖርቱ ከግማሽ ቢሊዮን ዶላር ብዙም የዘለለ አይደለም። ነገር ግን የከበሩ ማዕድናት ብቻቸውን የኢትዮጵያ ፖቴንሻል በመሆናቸው፣ ከግማሽ ቢሊዮን በላይ ዩኤስ ዶላር ኤክስፖርት ማድረግ የሚችል አቅም ላይ ነን፡፡

የዚህ ሁሉ ዋና መነሻ ቅድም አንስቼዋለሁ፡፡ ለዘርፉ እንደ ሀገር ትኩረት መስጠት፣ የተለያዩ ድጋፎችን፣ ማበረታቻዎችን መስጠት፣ የእሴት ሰንሰለቱን በደንብ አድርጎ ማየት፤ የባለድርሻ አካላትን በተመለከተም ተጠያቂነት እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ይህ ዘርፍ የራሱ የሆነ ተጠያቂነት ባለው፤ ለጋራ ሃብት ለሀገር በሚጠቅም መልኩ ሥራ ላይ ሊውል ይገባል፡፡ ለሁላችንም የሁላችንም ሀብት ነው የሚል እሳቤ ፈጥረን ካልተንቀሳቀስን፤ ሌሎች አፍሪካ ሀገራት ላይ ያጋጠመውን የሚመስል የራሱ የሆነ የፀጥታ ችግር ሊፈጥር ይችላል፡፡

ከዛ የተነሳ ለከበሩ ማዕድናት ላይ የነበረው

**ወደ ገጽ 14 ዞሯል**

# “የማዕድን ዘርፍ አሁንም በሀገሪቱ...

ከ12ኛ ገጽ የዞረ

አፈጻጸም በጣም የከፋ (ዎረስት) ነበር፡፡ ምርቱ በብዛት አለ፡፡ አፈጻጸሙ ግን በጣም ዝቅተኛ ነበር። ይሄንን በአጭር ጊዜ ለማስተካከል ሞክረናል፡፡ የመሸጫ ከፍተኛና ዝቅተኛ ዋጋውን አስተካክለን ለማዘጋጀትና ለማየት እየሞከርን ነው፡፡

የብዙ የአፍሪካ ሀገሮች ችግር በማዕድን ብቻ ሳይሆን፣ በግብርናውም ሆነ በሌሎችም ዘርፎች እሴት ጨምሮ ኤክስፖርት የማድረግ ችግር ነው። ከከበሩ ማዕድናት አኳያ ካየነው ያለው ችግር በጣም የባሰ ነው፡፡ እንዳለ ለሕንድ እና ለፓኪስታን፤ ለአሜሪካ ገበያ በጥሬው ነው የሚላከው፡፡ እና የተወሰነ እሴት ቢጨመርበት ብዙ ነገር ለሀገር ውስጥ መጠቀም እንችላለን፡፡

ባለፈውም ኤግዚቢሽን ላይ እንደታየው በጣም ብዙ ሃብት አለን፡፡ ማዕድናቱ ከወርቅ በላይ በጣም ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ናቸው፡፡ እንደ ሀገር እነዚህን የመጠቀሙ ልምድ የለንም፡፡ ወርቅ እና ብር ነው የተለመደው፡፡ ግን ከዛ በላይ የከበሩ ነገሮች አሉን ፡፡

ገበያውን በደንብ አላስተዋወቅነውም፡፡ እሴትም አልጨመርንበት፡፡ ኢንቨስተሮችም በበቂ ሁኔታ አልመጡም፡፡ በርግጥ አሁን በማኅበርም የተደራጁ እና ማሠልጠን የጀመሩ ተቋማት አሉ፡፡ ከከበሩ ማዕድናት ፋውንዴሽን ጋር በመሆን የሚደረጉ ጥረቶች አሉ፡፡ ግን ብዙ ሥራ ይፈልጋል፡፡

ደላንታ፣ ወሎ አካባቢ ያለው ኦፓል ማዕድን ቢታይ በጣም የሚገርም ነው፡፡ በዓለም ገበያ ላይ ያለውን ዋጋ ሲነግሩን በጣም የሚያስገርም ነው፡፡ ነገር ግን በጣም በወረደ ሁኔታ ነው አመራረቱ፡፡ የእሴት ሰንሰለቱንም ፖሊሽ የሚያደርጉ ተቋማት ብዙም አይደሉም፡፡

በሂደት ቀስ በቀስ ይህንንም ዘርፍ ደግፈን፣ ዋጋ ሰጥተነው ልንጠቀምበት የሚገባ ነው፡፡ ለዚህም ማስተካከያዎችን እያደረግን ነው፡፡ ፍቃድ የሚሰጡ ክልሎች ናቸው፡፡ እኛ ኤክስፖርት እንዲያደርጉ ፈቃድ/የኮምፒውተንስ ላይሰንስ ነው የምንሰጠው። ነገር ግን በእኛ በኩል ያንን እሴት ጨምረው በትክክል ኤክስፖርት እንዲደርጉ ቼክ በማድረግ ላይ ነን። በተለይ ፍቃዶች በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች፤ በመንግሥት መዋቅር፣ በክልልም፣ በፌደራልም ላይ ቢሰጡ ለሀገር በሚጠቅም መንገድ ቁጥጥር/ሬጉሌት እየተደረገ ቢመራ መልካም ነው፡፡

**ጥያቄ፡- ዘርፉ የሥራ እድልን ከመፍጠር አኳያ ትልቅ አቅም እንዳለው ይታወቃል፣ አሁን ላይ የሥራ እድልን በመፍጠር ረገድ ያለው ሚና ምን ይመስላል?**

**ኢንጂነር ሀብታሙ፡-** ዘርፉ በጣም በርካታ ዜጎችን ያቀፈ ነው፡፡ በተለይ ቅድም እንዳልነው ብዙ ሥራው በባሕላዊ መንገድ የሚከናወን ነው፤ በመላው ሀገሪቱ በባሕላዊ ምርት ላይ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ዜጎች ተሰማርተዋል።

ዘርፉ ያለው አቅም ይህ ብቻ አይደለም። የከበሩ ማዕድናት ላይ ሥራዎችን ሠርተን፤ ወርቅ ላይም ሥራዎችን ሠርተን፤ እስካሁን ያልተጠቀምናቸው ማዕድናትም ሲወጡ ከፍተኛ የሆነ የሥራ ዕድል ሊፈጠር ይችላል። ለሀገርም በዛኑ ያህል ገቢ ያስገኛል።

በሁሉም ዘርፍ በሀገሪቱ እየተመረተ ያለው ምርት ከአንድ ሚሊዮን የዘለለ አይደለም፡፡ ይሄ በጣም ትንሽ ነው፡፡ በሀገሪቱ ካለን አቅም አኳያ በእልህ ልንሠራ ይገባል። በእርግጥ ዘርፉ የረዥም ጊዜ ኢንቨስትመንት ስለሆነ ሠላም ይፈልጋል፡፡

ኢንቨስተሮች አንድ ወርቅ ላይ የሚያመርት ኩባንያ መጥቶ አስር ዓመት ፈልጎ፣ ገንዘቡን በብዙ ዶላር ጠፍጥፎ፤ ከዛ እንደገና ለሃያና ለሠላሳ ዓመት ሊያመርት ነው የሚመጣው። በመሆኑም አስተማማኝ የሆነ ሠላም ይፈልጋል፡፡

ይሄ የዘርፉ የተለየ ባሕሪው ነው፡፡ እነዚህን እንደ ሀገር ማሰብ አለብን። ለተጨማሪ ኢኮኖሚ በሀገሪቱ ላይ እስከ አሁን ከምናውቃቸው ከግብርናና ከኢንዱስትሪ፤ ከተለመዱ ዘርፎች በተጨማሪ ተጠቃሚ መሆን ካለብን ይሄንን እንደ ሀገር ተስማምተን አውቀን፤



የሚቀጥለው ትውልድም እንዲጠቀም በሚያስችል መልኩ መጠቀም ያስፈልገናል፡፡

**ጥያቄ፡- ከሠላምና መረጋጋት ጋር በተያያዘ ከዘርፉ ተጠቃሚ መሆን ያልቻሉ አካባቢዎች ካሉ?**

**ኢንጂነር ሀብታሙ፡-**ሁላችንም እንደምናውቀው ከሠላምና መረጋጋት ጋር በተያያዘ ችግር ውስጥ ያሉ አካባቢዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ ፖታሽ ወደ አፋር አካባቢ ነው ያለው። ፖታሺየምን መጠቀም የጀመሩ ኩባንያዎች ነበሩ፡፡ ቤኒሻንጉል ጉምዝ፣ ጋምቤላ፣ ትግራይ፤ እነዚህ አሁን ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ ኦሮሚያ፣ አማራ አካባቢ ያሉ በሙሉ የወርቅ አምራቾች ናቸው፡፡ ሊቲየም ታንታለም ያሉ ማዕድናት ያሉባቸው ናቸው። ሌሎች ገና ብዙ ተመራምረን ያላገኘናቸው ማዕድናት ያሉባቸው አካባቢዎች ናቸው፡፡ ይህ አንድ ከፍተኛ የሆነ ችግር ነው። ቢሆንም እየታገለን እንሠራለን።

ሰው እድል ሲያገኝ፣ ወጣቶች ሲቀጠሩ ስለሆነ ሠላም የሚመጣው ባለው ሁኔታም ሥራዎች እየተሠሩ ነው። የፀጥታ መዋቅር ተመድቦ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። ይህም ሆኖ ብዙ አካላት እንዲመጡ እንፈልጋለን። ብዙ ዓለምአቀፍ ትልልቅ በዚህ ዘርፍ ላይ ያሉ ተቋማት መጥተው ሀብታቸውን እንዲያፈሱ፤ ከሀገር በቀል ተቋማት እና ከግል ባለሀብቶች ጋር ሆነው በሽርክና እነዚህን ሀብቶች እንዲያለሙ እንፈልጋለን፡፡

በዚህ መልኩ አስበን፣ ይህን ሀብት ካላወጣን በስተቀር አሁን ካሉብን የኢኮኖሚ ችግሮች ለመውጣት በጣም እንቸገራለን። ይህንን እውነታ ሁሉም ዜጋ ሊያስብበት ይገባል፡፡ ሀብታችንን በደንብ መጠቀም እንድንችል ሠላም ያስፈልጋል፡፡

ቅድም እንዳልኩት ባለሀብቶች ለሠላሳ ለአርባ ዓመት የሚቆይ ኢንቨስትመንት ውስጥ ለመግባት የሠላምን ጉዳይ ሳያረጋግጡ በቢሊዮን ዶላር ማፍሰስ ይቸገራሉ። ለዘርፉ ሠላም በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ ዜጎች የመንግሥት መዋቅር ውስጥ ያሉ የፀጥታ አካላት ተረባርበው ሰላምን እውን ለማድረግ መሥራት ይጠበቅባቸዋል ፡፡

**ጥያቄ፡- የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችና አምራቾችን በዚህ ዘርፍ ላይ በበቂ ሁኔታ ለማሳተፍ ምን ድጋፍ እያደረጋችሁ ነው?**

**ኢንጂነር ሀብታሙ፡-**በመሠረቱ በአዲሱ ሕጋችን ላይ የሀገር ውስጥ አምራቾች ማምረት በሚችሉት ላይ የውጪዎቹ እንዳይገቡ ሕጉ ይከለክላል፡፡ በሕግ ደረጃ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ማምረት የሚችሉትን የውጭ ባለሀብቶች መጥተው ያምርቱት ቢባል ብዙም የሚጨምሩት ነገር የለም፡፡ እነሱ የራሳቸው ቅድሚያ ሊያሰጣቸው የሚችል ሥራ አላቸው፡፡ እሱ ብቻም ሳይሆን በሽርክና ነው የሚሠሩት፤ ብዙ ነገር ተጋግዘው ነው የሚሠሩት፤ የውጭ ባለሀብቱም በግልፅ እዚህ ሀገር ውስጥ የሚፈልገው ብዙ ነገር አለው፡፡

ያንን እየሠሩ ያሉ ብዙ ተቋማት አሉ፡፡ በተጨባጭም አሁን ላይ ያሉ አሉ፡፡ ነገር ግን ከላይ እንደገለፅኩት ዘርፉ ብዙ ቴክኖሎጂ ይፈልጋል፤ ትልቅ ቴክኖሎጂ፣ ትልቅ ኢንቨስትመንት ይፈልጋል፡፡ ከኛ ሀገር ምናልባት የስቶክ ገበያው ሲመጣ ሁላችንም ዜጎች ሼራችንን ገዝተን ትልቅ አቅም ሲኖረን እንደ ሀገር ለማምረት ብዙ ላንቸገር እንችላለን፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ ግን ይከብደናል። ለምሳሌ ኩርሙኩ የሚባለው ፋብሪካ ብቻውን መጀመሪያ ጊዜ 5 መቶ ሚሊዮን ዶላር ነው ኢንቨስት ያደረገው፡፡

ይሄንን ለብቻው ኢንቨስት ለማድረግ የሀገር ውስጥ ባለሀብቱ ይቸገራል፡፡ በሽርክና/በጆይንት ቬንቸር ግን ይሞከራል፡፡ በሁሉም አማራጮች አሉ፡፡ በራሳቸው ኢንቨስት ለማድረግ አቅም ካላቸው አሁንም ማንም የሚከለክላቸው የለም ነው የምንለው፡፡ ተባብሮ በጋራ እንደ ኮርፖሬት ኢንቨስት ማድረግም ይቻላል፡፡

**ጥያቄ፡- የሀገር ውስጥ አምራቾች ዘርፍን ምን ያህል እየደገፉ ነው፡፡ የቴክኖሎጂ ውስንነት ከመቅረፍ አንጻር ምን ያህል አበርክቶ አላቸው፡፡**

**ኢንጂነር ሀብታሙ፡-** ቴክኖሎጂ የሚመጣው አብሮ ምርቱ ሲመጣ ነው፡፡ ኢንቨስትመንቱ ሲመጣ እኛ እንደሀገር ስንደግፍ ነው፡፡ ቴክኖሎጂው በአብዛኛው ለግል ባለሀብቱ ክፍት ነው፡፡ ቴክኖሎጂ እኛ አምጥተን አይደለም የምናስተዋውቀው፡፡ ይሄ የቆየ ዘርፍ ነው፤ ብዙ እድሜ የሆነው ዘርፍ ነው፡፡ በጣም የበሰለ ቴክኖሎጂ ነው፡፡ ብዙ አዲስ የምንለው አይደለም። ከዚህ ዘርፍ ሌሎች ሀገሮች ብዙ ተጠቅመዋል። አንድ ቦታ ላይ መቶ ዓመት ጭምር የሚያመርቱ አውስትራሊያን፣ ካናዳን፣ ደቡብ አፍሪካን የመሰሉ ብዙ ትልልቅ ቴክኖሎጂው አላቸው፡፡

ቴክኖሎጂን በአብዛኛው የሚያመጡት ኢንቨስተሮች ናቸው፡፡ ነገር ግን በትንንሽ እስኬል የሚያመርቱ ባሕላዊ አምራቾች አንዳንድ ጊዜ ለጤና አስጊ በሆነ መንገድ፤ አካባቢን ሊበክል በሚችል ደረጃ የሚመረትበት ሁኔታ ሲከሰት በነሱ ደረጃ ሊጠቀሟቸው የሚችሏቸውን ቴክኖሎጂዎች ማስተዋወቅ ያስፈልጋል፡፡

ኤክስፖ ስናዘጋጅም ቴክኖሎጂን ለማስተዋወቅ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ መንግሥት ቴክኖሎጂዎችን ገዝቶ ለተደራጁ ማኅበራት በረጅም ጊዜ ብድር መስጠት ይቻል ይሆናል እንጂ ገዝቶ አይሰጥም፡፡

የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴርም ከዚህ አኳያ አንዳንድ ነገሮችን እያመረተ ነው፡፡ አነስተኛ ማኅበራት ሊጠቀሙ የሚችሏቸውን ማለት ነው፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ተቋማቱ መጀመሪያውንም ቢዝነስን መሠረት አድርገው የሚያመርቱና የሚታወቁም ናቸው፡፡

አማራጮች አሉ፡፡ ይህንንም እድል ማምጣት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ እድል ለሚመረጡ ተቋማት ለእነርሱ የገበያ እድል ነው፡፡ ስለዚህ ይህንን ለማድረግ ነው ኤግዚቢሽን የምናዘጋጀው፡፡ ገዝተን ለማቅረብ እየሞከርን ነው፡፡ ለመንግሥት ብዙም አመቺ ላይሆን ይችላል ሜጋ የሆኑ ተቋማት ግን ብቃትና ቴክኖሎጂው ያላቸው ናቸው፡፡

**ጥያቄ፡- በሚኒስቴሩ ከሚሠሩ ሥራዎች አንዱ ለኢንዱስትሪው ግብዓት የሚሆኑ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት መተካት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የኮንስትራክሽን ዘርፉ በምን መልኩ እየተደገፈ ነው?**

**ኢንጂነር ሀብታሙ፡-** ከኮንስትራክሽን አንጻር ሀገራችን ገና የምትገነባ ሀገር ነች፡፡ በሺዎች የሚቆጠር እድሜ ያላት ጥንታዊ የምትባል ሀገር ነች፤ ነገር ግን ገና የምትገነባ ሀገር ነች፡፡ ለግንባታ ወሳኝ ከሆኑ ነገሮች አንዱ ሲሚንቶ ነው፤ ሌላው ብረት ነው፡፡ እነዚህን ነገሮች በሀገር ውስጥ ማምረት መቻል በጣም ጠቀሜታ አለው፡፡

ባለፉት ዓመታት የሲሚንቶ እጥረት አጋጥሞ ነበረ። በነገራችን ላይ ከባለፈው ኤክስፖ ጎን ለጎን ሲቀርቡ የነበሩት ጥናቶች እንዳመላከቱት ኢትዮጵያ ያላት የሲሚንቶ ጥሬ ሃብት አቅም አፍሪካን ሙሉ መገንባት የሚያስችል ነው፡፡

25 በመቶ የሚሆነው የሀገሪቱ የቆዳ ሽፋን ለሲሚንቶ የሚሆን ግብዓት የሚገኝበት ነው፡፡ በሲሚንቶ ሀብት በጣም ሀብታም ነን፡፡ ግን አንዳንድ የፖሊሲ ጉዳዮችም ስለነበሩብን ያለው ይበቃል በሚል ፈቃዶች ቆመው ነበር፡፡

ለሀገር ካመረትን በኋላም ወደ ውጭ መላክ እንችላለን፡፡ የሲሚንቶ እጥረቱ ተፈጥሮ የነበረው፤ አንደኛ ሲያመርቱ የነበሩ ፋብሪካዎች በሙሉ አቅም ባለማምረታቸው ነው፡፡ ለምሳሌ መሶቦ በነበረው ግጭት ከምርት የወጣበት ሁኔታ ነበር፡፡ በምዕራብ አካባቢ የነበሩ ሲሚንቶ ፋብሪካዎች በነበረው ፀጥታ አሁንም ድረስ በብዙ መቆራረጥ ችግር ውስጥ ናቸው። ይህም ሌላው ያጋጠመ ችግር ነው፡፡ አልፎ አልፎ የውጭ ምንዛሪና የመለዋወጫ እጥረት ችግሮችም ነበሩ፡፡

ከዚህ ውጭ የፍላጎት መጨመር አለ፡፡ ጭማሪው በዓመት ከ 30 ሚሊዮን ቶን በላይ ነው፡፡ በአሁን ወቅት ማምረት ያቆሙ ፋብሪካዎች በሙሉ ወደ ሥራቸው ተመልሰዋል፡፡ ስለዚህ የተሻለ የሲሚንቶ ምርት ይኖራል።

ከዚህ በላይ አዳዲሶቹ በጣም እየመጡ ነው። ለሚገን ሔዶ መመልከት ይቻላል፡፡ አሁን ባለው የመጀመሪያው ምዕራፍ ዳንጎቴና ደርባን አንድ ላይ የሚያሕል ነው። ደርባ የማስፋፊያ ሥራ ለመሥራት ተፈራርሞ ሥራ ጀምሯል። በረንታ የሚባሉ ሌሎች ሲሚንቶ ፋብሪካዎችም ሥራ እየጀመሩ ናቸው። ሲሚንቶ ላይ ተገማች በሆነ መንገድ ከችግሩ እንወጣለን፡፡ ለመገንባት ስጋት አይኖርብንም፡፡

ሌላው ትልቁ ችግራችን ብረት ነው፡፡ አሁን ባለው የውጭ ምንዛሪ እጥረትም እየተቸገርን ያለው ብረት ላይ ነው፡፡ ከላይ ከጠቀስኩት አኳያ ብረትንም ልክ እንደ ወርቅና እንደሌሎች ትልቅ ቴክኖሎጂ የሚጠይቅ ነው፡፡ ሃብቱ አለን ፍለጋ ላይ ያሉ በቅርብ ጊዜ ሊያመርቱ የሚችሉ ተስፋ ያላቸው አሉ። እስካሁን ድረስ ግን ኢንቨስተሮችን እየጠራን ነው። ሀገር ውስጥ ያሉ ፋብሪካዎች ብረት አቅልጠው ምርት የሚያቀርቡ

ወደ ገጽ 15 ዞሯል

# “የማዕድን ዘርፍ አሁንም በሀገሪቱ...



ከ14ኛ ገጽ የዞረ

ፋብሪካዎችም፣ ብረትን ከሀብቱ አውጥቶ አቅልጦ መስጠት የሚል ነው። ጥሬ እቃውን በሀገር ውስጥ ማቀነባበር ነው ትልቁ ሥራ።

በከፊል ያለቀውን ምርት ከውጭ ማምጣትና እዚህ ያለውን ቁርጥራጭ ብረት ሰብስቦ አቅልጦ ማቅረብ ነው። ይህ ለሀገር በቂ አይደለም። አሁናዊ የብረት ፍጆታችን ከ1 ነጥብ 5 እስከ 2 ቢሊዮን ቶን ነው። ይህንን ከውጭ እያስገቡ መቀጠል አይቻልም።

ከዚህ የተነሳ ብረት ላይ ትልቅ ትኩረት አድርገን እየሠራን ነው። የተጀመሩ ሥራዎችም አሉ። ፍለጋ ላይ ያሉ ተቋማት አሉ፤ እነሱ እንዲሠሩ ሥራዎችን እየሠራን ነው። ነገር ግን በዚህ ዘርፍ ላይ አሁንም ኢንቨስተሮችን ወደ ዘርፉ እንዲገቡ እያበረታታን ነው።

ከነዚህ ውጭ ለኮንስትራክሽን ዘርፉ የሚሆኑ የዓለም አቀፍ ደረጃ ያላቸው ጋራናይት፣ ማርብል፣ ላይምስቶን፣ በጣም ትልቅ ሀብት ነው ያለን። በትናንሽ ችግሮች እክል ቢገጥማቸውም ሀብቱ አለን፣ ማምረትም እንችላለን።

በዋናነት ግን በኮንስትራክሽን ዘርፉ ላይ ቀጣይነት ያለው ልማት እንድንመጣ ትልቁ ትኩረት የሚፈልገው ብረት ነው። ለዚህም ሥራ እየሠራን ነው። ብዛት ያላቸው በዘርፉ የተሰማሩ ተቋማት እንዲመጡ እየጋበዝን ነው፤ ሀብቱንም እያስተዋወቅን ነው።

**ጥያቄ ፦ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ዘርፉ ያለው ተስፋ ሰጭነት ምን ይመስላል?**

**ኢንጂነር ሀብታሙ፡-** ተስፋ ሰጭነቱ እዚህ ያለውን ሀብት ዝም ብላችሁ ዞራችሁ ስታዩት ሊታወቅ የሚችል ነው፡፡ እውነታው አንዳንዴ ቁጭትም ያሳድራል። ተስፋውም በዛ መጠን አለ ማለት ነው።

ለዘርፉ መንግሥት ይህን ያህል ትኩረት ከሰጠው፣ የሀገራችን የሰላም ሁኔታ ከተስተካከለ እና ሁሉንም አስበንበት ከተጠቀምንበት ተስፋችን ብሩህ ነው። በወርቅ ላይ ብሩህ ነገር አለ። ፖታሺየም ላይ እንደዚሁ ፍላጎት ያላቸው፣ የጀመሩም ተቋማት አሉ። ፖታሽ በጣም ትልቅ ነው። ብዙ ሰው ማዕድን ሲባል በአዕምሮው የሚመጣለት ወርቅ ነው። ሊቲየምና ታንታልየም የመሰሉ በቅርቡ ሥራ የሚጀምሩ አሉ።

ስለዚህ ኤክስፖርትም ለማድረግ ከውጭ የሚገባውን ለማስቀረት በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት የሥራ እድል ለመፍጠር በጣም ተጫባጭ የሆነ ተስፋ ያለው ዘርፍ ነው፡፡ የተፈጥሮ ጋዙን ለመጠቀም ሥራዎች እየተሠሩ ነው፡፡ በዚህ ብዙ ሀገሮች ብዙ ተጠቅመዋል፡፡ እኛ ገና ነን፡፡ ከእነሱ ምን የምንማረው ነገር አለ? ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል። አገራችን እንድትሆን ወደሚፈለገው ለማምጣት ሁላችን ገና ብዙ መሥራት አለብን፡፡ ተስፋችን ግን ተጫባጭ ነው። ሥራዎች በሁሉም ዘርፍ ላይ እየተሠሩ ነው፡፡

**ጥያቄ ፡- ባለፉት ስድስት ወራት በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ኢትዮጵያ ከማዕድን ዘርፍ ምን ያህል ገቢ አግኝታለች?**

**ኢንጂነር ሀብታሙ፡-** በባለፈው ሦስት ወር ስንገመግም የነበሩ ቁጥሮች እንዳለፈው ወቅት በምናውቀው መንገድ ነው እየሄደ ያለው፡፡ መሻሻል እስኪመጣ ድረስ ያን ያህል ለውጥ የለውም፡፡ አሁንም ያለው ከእቅዳችን ወደ 60 በመቶ የሚጠጋ ነው። ሌሎችን አላመጣናቸውም ሲሚንቶ ላይ የተሻለ የሚመስል ነገር አለ፡፡

ጥቁር ገበያውና ኮንትሮባንዱ በአነስተኛ ደረጃ የሚመረቱ ምርቶችን በጣም እየተፈታተናቸው ነው፡፡ እሱ ከፍተኛ ፈተና እየሆነ ነው፡፡ ያንን አሁንም ተባብረን እስካላስቆምን ድረስ ችግር እንደሆነ ይቀጥላል። ምርቱ ግን አለ፣ እየተመረተም ነው፡፡ በጣም ከፍተኛ ምርት አለ።

በዚህ በኩል የውጭ ሕገወጥ አካላትን አስቁመናል ነገር ግን የሀገር ውስጡ ኃላፊነት ተስምቶት ሀገሬን ነው እየጎዳሁ ያለሁት፡ አገሬን ነው መርዳት ያለብኝ ብሎ አስቦበት ካልሠራ ለዘርፉ ፈተና ይሆናል፡፡ ያንን ሙሉ ለሙሉ እስካላስቆምነው ድረስ ችግሩ ይቀጥላል።

ችግሩን በዘላቂነት መቆጣጠር የምንችለው ሥራው በፋብሪካ ደረጃ ሲሠራ ነው፤ ያኔ የቁጥጥር ሥራው ይቀላል። አጠቃላይ የሆነውን መረጃ በዓመቱ መጨረሻ ላይ ማየት ይቻላል፡፡ አሁን እቅዱ ላይ ብዙ ክፍተቶች እንዳሉ ነው የሚታየው፡፡ የዝናብ ወቅትም ነው፡፡ የስድስት ወሩን ገምግመን ስንጨርስ መረጃውን ይፋ እናደርጋለን ፡፡

**ጥያቄ፡ የፖሊሲ ማሻሻያዎችን ማድረጋችሁን ተከትሎ በሀገር ምን ያህል ባለሀብቶችን መሳብ ቻላችሁ?**

**ኢንጂነር ሀብታሙ፡-** ብዙ አሉ፡፡ በሁሉም ዘርፍ ላይ ብዙ አሉ፡፡ ፍላጎቱ ብዙ ነው፡፡ ፍለጋ ላይም ያሉ በመቶዎች የሚቀጠሩ ናቸው፡፡ በፋብሪካ ደረጃም ሊያመርቱ የሚችሉም እንዲሁ አሉ፡፡ አምስት ስድስት የሚሆኑ ፋብሪካዎች አሉ፡፡ በቅርብ ጊዜ ነው የመጡት። ብዙ ዓለም አቀፍ ተቋማት መጥተው መቀላቀል ይፈልጋሉ፡፡ አንዳንዶቹም የፍለጋ ሥራቸውን የቀጠሉ ፍቃድ የምንሰጣቸው አሉ።

ነገር ግን ቅድም ባልነው መንገድ እኛ ለዚህ ዘርፍ እንዲመቻች አድርገን ብዙ ነገሮችን መሥራት አለብን። በፖሊሲ ደረጃ እና በተቋም ደረጃ የሠራናቸው ሥራዎች ለነሱ በጣም ጠቃሚ ናቸው። ለሀገር ውስጥም አምራች፣ ለውጭ አምራችም በጣም ጠቃሚ ናቸው። ፍለጋው ላይም የኛ ትልቁ ችግር ሀብታችንን በደንብ አናውቅም። የሀገሪቱን 30 በመቶ የቆዳ ስፋት ላይ ያለውን ሀብት ነው የምናውቀው። የቀረውን አናውቅም።

በመሆኑም ሀብቱን ማወቁ እራሱ አንዱ ትልቁ ነገር ነው። ምክንያቱም የምንሸጠው እሱን ነው። ይሄን ያህል የሚገመት ሀብት አለን ኢንቨስት አድርጉ ማለት ይፈልጋል። እዛ ላይም ሥራዎች እየሠራን ነው። አንዳንድ ተቋማት ጋርም ከተለመደው ውጪ ጠቋሚ የሆኑ ጠቅላላ የሀብት መረጃዎች ሊሰጡ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን ከያዙ ሀገራት ጋርም እየተነጋገርን ነው።

ሥራዎችንም እየጀማመርን ነው። ትልቁ ሥራ እንዳውም እንደሀገር ቅድሚያ የሚሰጠው እሱ ነው። ሀብትን እስካላወቅን ድረስ የት ቦታ ምን አለ? በምን ያክል የሚገመት የሚል እስከሌለ ድረስ ባለሀብቶች ብዙ ሀብት በፍለጋው ላይ እንዲያወጡ ጊዜ እንዲያጠፉ ያደርጋል።

ስለዚህ እዛ ላይ ሥራዎችን እየሠራን ነው። በአጫጭር ወራት ውስጥ ጠቋሚ መረጃዎችን ሊሰጡ የሚችሉ ናቸው። እነዚህን ሥራዎች በቅርብ ጊዜ እንጀምራለን የሚል እምነት አለ። የመንግሥት ድጋፍም አለ። ዘርፉ በባሕሪው በሁሉም የመንግሥት መዋቅር የሚፈልግ ዘርፍ በመሆኑም የሁሉም የጋራ ትብብር ይፈልጋል።

ሀገራችን የሀብታም ደሃ መሆን የለባትም። ዜጋውና ትውልዱ ይሄንን ሀብት በአግባቡ መጠቀም አለበት የምንል ከሆነ ሀብቱ አለ። በመሆኑም ሀብቱን ማልማት ሁላችንም ይጠበቅብናል። በመንግሥት ያለውም ከዚህ በፊት ያልነበረ ነው። ይሄ ሚኒስትር መሥሪያ ቤት እንኳን የተቋቋመው በቅርብ ነው። ተገቢ ትኩረት አለው፤ ለማምረት አንዳንድ ችግሮችን መፍታት እና ሀብታችንን ይበልጥ ማወቅ ጅምር ላይ ያሉ ተቋማትን በፍጥነት ወደ ሥራ ማስገባት ያስፈልጋል። ይህን ማድረግ ከቻልን በሚቀጥሉት አንድ እና ሁለት ዓመታት በጣም ጥሩ ውጤት ማምጣት እንደሚቻል ተስፋ አለ።

**ጥያቄ፦ የወርቅ ኮንትሮባንድ ንግድን ስመከላከል ግብረ ኃይል ተቋቁሞ እየተሠራ ነው ሥራው ምን ያህል ውጤት አስገኝቷል? ለችግሩ በዘላቂነት የተቀመጠ መፍትሔ አለ ወይ?**

**ኢንጂነር ሀብታሙ፡-** በወርቅ ዘርፍ ላይ ያልተፈቀደላቸው ብዙ አካላት ተሠማርተው ነበር። መረጃው አላቸው፡፡ እነዚህ አካላት በሕግ እንዲጠይቁና ከአካባቢው እንዲወጡ ተደርጓል፡፡ ይሄ ትልቅ ነገር ነው፡፡ ግብረ ኃይሉ ከሁሉም ፀጥታ አካላት ፣ ከክልሎች ጋር በጋራ እየሠራ ነው፡፡ በዚህም የሚታይ ተጨባጭ ለውጥ አለ፡፡ ዘላቂነቱ በተመለከተ ማዕድናት ያሉባቸው አካባቢዎች የፀጥታ መዋቅር በቋሚነት ያስፈልጋል፡፡ ይሄ ድሮም ነበር፡፡

በቀደመው ጊዜም ቢሆን የማዕድን ፖሊስ በማቋቋም ትልልቅ ሜጋ የማዕድን ቦታዎች ላይ ቁጥጥር ማድረግ የተለመደ ነው። በግብረ ኃይሉም በኩል እየተሠራ ያለው ይኸው ነው፡፡ ከዚህም ባለፈ የፀጥታ አካላት ተቀናጅተው የማጽዳት ሥራ ተሠርቷል። በወቅቱ ብዙ ሀብት ተወርሷል፤ ብዙዎችም ተጠያቂ ተደርገዋል። የብዙ አካላት ፈቃድ ተሰርዟል፡፡ ውጭ ሀገር ዜጎችም በዚህ ሕገወጥነት ውስጥ ተገኝተዋል፡፡

ክልሎች ብዙ በሕገወጥ መንገድ የተሰማሩ የሀገር ውስጥ ተቋማትን ሀብት ወርሰዋል ተጠያቂም አድርገዋል። ዘላቂነቱ እንግዲህ እንደ ሀገር ሜጋ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ ቅድም ባልኩት መልኩ ነው። ኮንትሮባንድን እንደሀገር የምናይበት መንገድ ለማዕድን ብቻ ሳይሆን በሁሉም ቦታ ላይ ነው። ኮንትሮባንድ ትልቁ ተግዳሮት እየሆነ ነው፡፡ እሱ እንደሀገር የሚሠራ ሥራ ነው፡፡

**ጥያቄ ፦ በሀገሪቱ ‹‹ሊቲየም›› ስማልማት ወደ ሀገር ውስጥ የገባና ሥራ የጀመረ ኩባንያ አለ። እስካሁን ያለው አፈጻጸም ምን ይመስላል ?**

**ኢንጂነር ሀብታሙ፡-** ሊቲየም፣ ታንታለም እና ሌሎች ማዕድናት በአንድ አካባቢ ላይ ብቻ ሳይሆን ብዙ ቦታዎች ላይ ያሉ መሆኑን ጠቋሚ መረጃዎች አሉ። የነበረው ቦታ ላይ የምናወቀው ሊትየም ምርት ላይ እንዲያመርቱ ፈቃድ የተሰጣቸው አካላት አሉ፡፡

ዘርፉ ጥንቃቄ የሚፈልግ ዘርፍ ነው፡፡ ትክክለኛ አቅም ያላቸው አካላት፤ በዚህ ዘርፍ ላይ ልምድ ያላቸው እና የገንዘብ አቅምም ያላቸው ተቋማት በተለይ ዓለም አቀፍ ተቋማት ወደ ሥራው እንዲገቡ ሥራዎች መሥራት አለብን፡፡ ፈቃድ ለጠየቀ አካል ሁሉ መስጠት የለበትም፡፡ በጣም ጥብቅ የሆነ ሥራ መሥራት ይጠይቃል፡፡

ከዚህ በፊት የተወሰኑ ክፍተቶች ነበሩ፡፡ ከዚህ የተነሳ አልሚዎች ችግር ሆነውብናል ብለው የሚያነሷቸው ጥያቄዎች አሉ፡፡ ችግሮቹን ለመፍታት በክልልም ሆነ በተቋማት ደረጃ እየተነጋገርን ነው፡፡ በቅርብ ጊዜ ይህንን ችግር እንፈታለን ብለን እናሳባለን። ወይ ችግሩ ተስተካክሎ ሥራ ይሠራሉ አለበለዚያ ሙሉ ለሙሉ የሥራ ውሏቸው ተቋርጦ ለሚያለማውና ብቃት ላለው አካል እንዲተላለፍ እናደርጋለን፡፡


**ጥያቄ ፦ የፌዴራል መንግሥቱና የክልል የማዕድን ቢሮዎች መካከል የመናበብ ችግር እንዳለ በዘርፉ የተሠማሩ አካላት የሚያነሱት ጉዳይ ነው፡፡ ምን ያህል ተናባችሁ እየሠራችሁ ነው ?**

**ኢንጂነር ሀብታሙ፡-** የፌዴራል መንግሥቱና የክልል የማዕድን ቢሮዎች በተመለከተ ሁሉም በራሳቸው በአዋጅ የተቀመጠ ተግባርና ኃላፊነት አላቸው፡፡ የፌዴራል መንግሥቱ አዋጅ የማውጣትና ሜጋ ፕሮጀክቶችን እና የሀገር ቁልፍ የሆኑ ነገሮችን ነው በአብዛኛው በቀጥታ የሚያስተዳድረው፡፡ ክልሎች ራሳቸው የቻሉ አካላት ናቸው፡፡ ልክ እንደፌደራሉ ሕግ የሚያወጣ ሕጉንም የሚያስፈጸም የሚጠይቅ አካል አላቸው፡፡ በዚያ ደረጃ ኃላፊነት መውሰድ አለባቸው፡፡

ከዚያ ውጭ ቴክኖሎጂን በማስተዋወቅ፣ ሀብት በማስተዋወቅ እና ሕግን በማውጣት የሚፈልጓቸውን ነገሮች ድጋፍ በመስጠት ረገድ ላይ ሥራዎችን እየሠራን ነው፡፡ ግን በቂ አይደለም፡፡ ገና ብዙ የምንሠራው ሥራ አለ፡፡ በሁሉም አካል የሚሰጡ የማዕድን ፕሮጀክቶች ተጠያቂነታቸው በሁሉም አካላት ነው፡፡ እነሱም እራሳቸው የቻሉ አካላት ናቸው፡፡

የፌዴራል መንግሥት ያለው ተግባርና ኃላፊነት አላቸው፡፡ ይሄ ተጠያቂነት እና ኃላፊነት አብሮ መኖር አለበት፡፡ በዚህ ሁኔታ ባለፉት ወራትም የተወሰዱ ማስተካካያዎች አሉ፡፡ አሁንም ብዙ መሥራት አለባቸው። ካውንስሉም በዚህ ላይ ያለውን ክፍተት ለመሸፈን ነው በዋናነት የተቋቋመው፡፡

# ስፖርት



## ስጋሱ የባምባሊ ልዑል

ቦጋለ አበበ



ሚያዝያ 10 ቀን 1992 በሴኔጋል ሴዲዮ የተባለ ስፍራ ነው የተወለደው። ያደገው ግን በሴኔጋል ደቡባዊ እምብርት ውስጥ በምትገኘው ባምባሊ የተባለች ትንሽ መንደር ውስጥ ከሚኖር ማኅበረሰብ ጋር ነው። ይህ ሕጻን ወላጆቹ ከሚንከባከቡት በላይ ብዙ ልጆች ይዘው ስለተቸገሩ ነበር ከአጎቱ ጋር ለመኖር እትብቱ የተቀበረበትን ስፍራ ትቶ ወደ ባምባሊ መንደር የተጓዘው።

ከሁለት ሺህ የማይበልጥ ሕዝብ በሚኖርባት ትንሽ መንደር የጨርቅ ኳስ በየሜዳው እያንከባለለ የልጅነት ሕይወቱን መግፋት የተያያዘው ታዳጊ እድሜው ለትምህርት ቢደርስም ቤተሰቦቹ እሱን ለማስተማር በቂ ጥሪት አልነበራቸውም። ስለዚህ በየማለዳው ከእንቅልፉ ነቅቶ ምሽት ላይ ፀሐይ እስክትጠልቅ በትንሿ መንደር አቧራማ በሆነው ጎዳና ላይ ኳስ ሲያንከባልል መዋል ዕጣ ፋንታው ነበር። ይህን ሲያደርግ ግን በታዳጊ እድሜው ታላቅ ተጫዋች ሆኖ በእግር ኳስ ያልፍልኛል ብሎ በማሰብ አልነበረም።

ይህ ታዳጊ በተለያዩ የአውሮፓ ሊጎች አስደናቂ ብቃት በማሳየት አፍሪካ ካፈራቻቸው ድንቅ ተጫዋቾች አንዱ መሆን የቻለው ሴኔጋላዊ ሳዲዮ ማኔ ነው። ከፈረንሳይ ሊግ ሜትዝ ክለብ ተነስቶ በኦስትሪያው ሬድቡል ሳልዝበርግ አድርጎ ወደ እንግሊዝ ፕሪምየር ሊግ ሳውዝሃምፕተን የተሻገረው ማኔ በሜርሲሳይዱ ክለብ ሊቨርፑል የማይረሳ ታሪክ ሠርቶ በጀርመኑ ኃያል ክለብ ባየር ሙኒክ አንድ ዓመት በማሳለፍ አሁን ላይ ታላላቅ ከዋክብት በተሰበሰቡበት የሳዑዲ ዓረቢያው ክለብ አል ናስር ከትሟል።

ድህነት ባጎሳቆለው መንደር የልጅነት ሕይወቱን ያሳለፈው ማኔ ፕሮፌሽናል እግር ኳስ ተጫዋች የመሆን ፍላጎት ያደረበት አገሩ ሴኔጋል እአአ በ1998ቱ የዓለም ዋንጫ ሩብ ፍጻሜን ስትቀላቀል ከተመለከተ በኋላ ነበር። ታዳጊው ማኔ ትኩረቱን ወደእግር ኳስ ሲያዞር ግን ቤተሰቦቹ መቃወማቸው አልቀረም። ነገር ግን ብዙም አልተጫኑትም፣ እንደሃሳቡ ይጓዝ ዘንድም ከግብርና የሚያገኟቸውን ምርቶች እየሸጡ በአቅማቸው ይደግፉት ያዙ። የመንደሩ ሰዎችም ለታዳጊው ገንዘብ አሰባስበው ወደ ሴኔጋል መዲና አቅንቶ በተሻለ የእግር ኳስ አካዳሚ ውስጥ ብቃቱ እንዲጎለብት ረዱት።

ማኔ ከወገኖቹ የተደረገለትን ድጋፍ ይዞ ወደ ዳካር ያቀናበት ረጅም መንገድና ውጣ ውረድ ወደ ፈረንሳይ ለመጀመሪያ ጊዜ ተጉዞ ፕሮፌሽናል ተጫዋች እስከሆነበት እለት ያለው ታሪክ በራሱ አንድ ትልቅ መጽሐፍ ይወጣዋልና እሱን በሌላ ጊዜ መመልከት የተሻለ ነው።

አስደናቂ ችሎታውን ያስመሰከረው የክንፍ ተጫዋች በትንሿ መንደር በባዶ እግሩ የጨርቅ ኳስ ከማንከባለል ተነስቶ ከዓለማችን ኮከቦች አንዱ በመሆን የሀብትና የዝና ማማ ላይ ከወጣ በኋላ መነሻውን አልዘነጋም። መጀመሪያ ያደረገው ነገር ያገኘውን ቋጥሮ ቤተሰቦቹን በአንድ ትልቅ መኖሪያ ሕንጻ ውስጥ እንዲኖሩ ማድረግ ነበር። በዚያም የአካባቢው ማኅበረሰብ እሱ በትልቅ ደረጃ ሲጫወት ተሰብስበው እንዲመለከቱት ትልቅ ስክሪን ዘርግቶላቸዋል። የተለያዩ ድጋፎችንም በዓይነትና በገንዘብ እያደረገ ከትንሿ መንደር ነዋሪዎች ጎን ከመቆም ቦዝኖ አያውቅም።

ዓመለ ሸጋው ኮከብ አገሩ ሴኔጋልን በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የአፍሪካ ዋንጫ ሻምፒዮን ያደረገው ባለፈው የካሜሩን አፍሪካ ዋንጫ ነው። ከዚያ በፊትም ይሁን በኋላ እንደበርካቶቹ የዓለም ከዋክብት የእረፍት ጊዜውን በተንደላቀቁ ስፍራዎች ማሳለፍ ፍላጎቱ አይደለም። የዕረፍት ጊዜውን በተነሳባት ኮሳሳ መንደር ከድሃው ማኅበረሰብ ጋር ማሳለፍ ምርጫው ነው።

ትንሹ የባምባሊ ሕዝብ ካደገበት ማኅበረሰብ ተሻግሮ የመላው ሴኔጋላውያን ኩራት የሆነውን ልዑላቸውን ከአፍሪካ ዋንጫው ድል በኋላ በአንዱ ቀን እንዲጎበኛቸው ጋበዙት። የክብር እንግዳ ሆኖ በሄደበት ጊዜም በመንደሩ ከሌሎች ሴኔጋላውያን ጋር አንድ ጨዋታ አድርጓል። የመንደሩ የመጫወቻ ሜዳ ጭቃ ነበር፤ እሱ ግን ተጸይፎ አልተዋቸውም። ይልቁንም ጭቃው ላይ በሚገባ ተጫውቶ ነው የተሸኘው። ሲሸኝ ግን በልቡ አንድ ነገር ይዟል። ያደገበትና የታወቀበትን መንደር ሜዳ በሚመጥን መንገድ መሥራት።

ማኔ ይህንን በአዕምሮው ይዞ ወደ አውሮፓ ተመለሰ። ብዙም ሳይቆይ ሥራውን ጀመረ። ለመንደሩ ባምባሊ የሚመጥን ያለውን ሜዳም በአጭር ጊዜ ውስጥ አሠራ። ይህንን ሜዳ የፊፋን መስፈርት ባሟላ መልኩ አሰርቶ ካጠናቀቀ በኋላም ሥራ እንዲያስጀምር ሰሞኑን ነበር ተጋብዞ ወዳደገባት መንደር የተመለሰው። እሱም የሠራውን ነገር ተመልክቶ ‹‹አሁን የልቤ ሞልቷል›› ሲልም በሐሴት ተናግሯል።

‹‹ዛሬ ከእናንተ ጋር በመሆኔ እጅግ ተደስቻለሁ፣ ሁሉም ነገር ወደጀመረባት መንደሬ ባምባሊ እንኳን ደህና መጣችሁ፣ ለእኔ ትልቅ ትርጉም ባለው በዚህ የፊፋ ደረጃን ያሟላ የእግር ኳስ ሜዳ ፊት ስቆም በኩራት እና በደስታ በተሞላ ልብ ነው። ይህ ለምወደው መንደሬ የተሰጠኝ ስጦታ ብቻ አይደለም። ከሁሉም በላይ የአንድነታችን፣ የጥንካሬያችን እና ለእግር ኳስ ያለን ፍቅር ምልክት ነው›› በማለትም ማኔ ደስታውን አንጸባርቋል።

ማኔ ድክ ድክ ብሎ ላደገባት መንደር ያለውን ከመስጠት ሰስቶ አያውቅም። አሁን ካስመረቀው ደረጃውን የጠበቀ የእግር ኳስ ሜዳ ባሻገር ለመንደሩ ያላደረገው ነገር የለም። ከ750 ሺ ፓውንድ በላይ አውጥቶ ትምህርት ቤቶች፣ ሆስፒታል፣ ፖስታ ቤትና ነዳጅ ማደያ ከፍቷል።

በቅርቡ የእግር ኳስ ሜዳውን ባስመረቀበት ወቅትም ታሪካዊዎቹን የሴኔጋል አንጋፋ ኮከቦች ፓፒስ ሲሴ እና አል ሃጂ ዲዩፍን አስከትሎ እአአ 2021 ላይ በ455 ሺ ፓውንድ ያስገነባውን ሆስፒታል ሲጎበኝ ታይቷል። ይህ ሆስፒታል ከመንደሩ ባምባሊ ባሻገር በአቅራቢያ የሚገኙ ከ34 በላይ መንደር ነዋሪዎችንም የሚያገለግል ነው።

ማኔ በባምባሊ መንደር በ250ሺህ ፓውንድ ዘመናዊ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትም አስገንብቷል። ከሁለት ሺህ በላይ ለሚሆነው የመንደሩ ነዋሪ በወር 57 ፓውንድ ድጋፍ የሚያደርገው ማኔ ባስገነባው ትምህርት ቤት ጥሩ ውጤት ለሚያስመዘግቡ ተማሪዎች 326 ፓውንድ የማበረታቻ ሽልማት ይሰጣል። ትምህርት ቤቱን በዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች በማደራጀትም ለእያንዳንዱ ተማሪ የላፕቶፕ ኮምፒዩተር በማደል በትምህርት ቤትም ይሁን በቤታቸው የ4G ኢንተርኔት ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ አድርጓል።




## “ጤናማ የልጆች አስተዳደግ”

አስናቀ ፀጋዬ

ልጆች እንዴት ናችሁ? ሰላም ነው? ትምህርት ጥሩ ነው? ሳምንቱ እንዴት አለፈ? ያሳለፍነው ሳምንት መጨረሻ የገና በዓል በመላው ክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በድምቀት ተከብሯል፡፡ እናንተም በተለይ ክርስትና እምነት ተከታይ የሆናችሁ ልጆች በዓሉን በድምቀት እንዳከበራችሁ እገምታለሁ፡፡ ልጆች! ዛሬ ለየት ባለ ርዕስ መጥቻለሁ፡፡ ለመሆኑ ወላጆቻችሁ እናንተን በምን አይነት መንገድ ነው እያሳደጓችሁ ያሉት?

መቼም ሁሉም ወላጅ ልጆቹን ጠቃሚና ተስማሚ ነው ብሎ ባሰበው መንገድ እንደሚያሳድግ ጥርጥር የለውም። ሁሉም ወላጅ ግን ተመሳሳይ የልጆች አስተዳደግ ዘዴን ይከተላል ማለት አይቻልም፡፡ አንድ የሚያስማማ ጉዳይ ቢኖር ግን፣ አብዛኛው ወላጅ በየራሱ መንገድ ልጆቹን በተሻለ ሁኔታ አሳድጎ ጥሩ ደረጃ ላይ ለማድረስ ጥረት ማድረጉ ነው፡፡ አያችሁ ልጆች! የእናንተም ወላጆቻችሁ ዋነኛ ፍላጎት እናንተን በጥሩ ሁኔታ ማሳደግና ለቁም ነገር ማብቃት ነው፡፡

ታዲያ ልጆች እናንተ በጥሩ ሥነ ምግባርና በመልካም ማንነት ተኮትኩታችሁ እንድታድጉ ወላጆቻችሁ ተጨማሪ የልጆች አስተዳደግ ዘዴዎችን ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ለዚህም ይረዳ ዘንድ ወይዘሮ ሳራ ዘመኑ የተባለችና በሙያዋ ነርስ የሆነች ወላጆች ልጆቻቸውን በአግባቡ ለማሳደግ የሚያግዝ ‹‹ጤናማ የልጆች አስተዳደግ›› የተሰኘ መጽሐፍ አሳትማለች፡፡

ልጆች! ወይዘሮ ሳራ በሙያዋ ነርስ ናት፡፡ የነርሲንግ ሙያ ትምህርቷን የተከታተለችው በአሜሪካን ሀገር ነው፡፡ በዚህ የሙያ ዘርፍ ከሃያ ዓመት በላይ አገልግላለች፡፡ በአሁኑ ጊዜ በሕክምና ተቋሙ ውስጥ እያገለገለች የምትገኝ ስትሆን ቨርጂኒያ በሚገኝ የኮሚዩኒቲ ኮሌጅ ውስጥም የነርሲንግ ትምህርት ታስተምራለች፡፡ በተጨማሪም ወላጆችን




በማሠልጠን ሙያ ሰርተፍኬት አግኝታ ወላጆችን ስለልጆች አስተዳደግ ታስተምራለች፡፡ ላለፉት ሦስት ዓመታት ደግሞ ‹‹እናት ለእናት›› የተሰኘ የዩቲዩብ ቻናልና ፌስቡክ ገፅ ከፍታና ግሩፕ መሥርታ ማኅበራዊ ሚዲያን በመጠቀም በኢትዮጵያና በውጪ ሀገራት ለሚገኙ ወላጆችና ሴቶች ስለልጆች አስተዳደግና ቤተሰብ በማስተማር ማኅበረሰቡን እያገለገለች ትገኛለች፡፡

አሁን ደግሞ ለንባብ ባበቃችውና ‹‹ጤናማ የልጆች አስተዳደግ›› በተሰኘው መጽሐፏ የልጆች አስተዳደግ ዘዴን በሁለት ምዕራፍ ለወላጆች ለማቅረብ ሞክራለች፡፡ አንደኛው ምዕራፍ እድሜን ያማካለ የልጆች እድገትን በሚመለከት የሚያትት ሲሆን ሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ የልጆችን የማሳደግ ተግባራዊ እንክብካቤን ይዳስሳል፡፡

ወይዘሮ ሳራ ይህን መጽሐፍ ያዘጋጀችው በተለይ በልጆችና በወላጆች መካከል ያለውን ክፍተት በማየትና ልጆችን እንደየ እድሜያቸው ደረጃ ማሳደግ ተገቢ መሆኑን በመረዳት ነው። ይህንኑ መሠረት በማድረግ ልጆችን ተንከባክቦ ማሳደግ የሚቻል ከሆነ ወደ ፊት ልጆች ትክክለኛውን መስመር ተከትለው በመሄድ የሚፈለገው አቅጣጫ ላይ ይደርሳሉ ከሚል እሳቤም ጭምር ነው መጽሐፉን አዘጋጅታ ለወላጆች ማቅረብ የፈለገችው። በተለይ ደግሞ አሜሪካን ሀገር ሳለች በነርስ ሙያ መምህርነት ስታገለግል በቆየችባቸው ጊዚያት ውስጥ በርካታ ኢትዮጵያውያን እናቶች በልጆቻቸው አስተዳደግ ዙሪያ ሲቸገሩና እንዴት ማሳደግ እንችላለን? የሚሉ ጥያቄዎች ይቀርቡላት እንደነበርና ይህም በልጆች አስተዳደግ ዙሪያ መጽሐፍ ለማዘጋጀት ቁጭትና ተነሳሽነት አሳድሮባታል፡፡

ብዙ ጊዜ ልጆች ፈሪዎች ናቸው፣ ራሳቸውን አይችሉም፤ ተነሳሽነት የላቸውም የሚባሉት ከልጅነታቸው ጀምሮ ተገርተው ባለማደጋቸው፣ በራሳቸው እንዲተማመኑ ሆነው ባለማደጋቸው፣ ከውስጥ ወደ ውጪ እንዲያብቡ ባለመደረጋቸው ነው የምትለው ወይዘሮ ሳራ፣ ጊዜው ካለፈ በኋላ ልጆችን ወደ መስመር ለመመለስ አስቸጋሪ በመሆኑ ወላጆች ልጆቻቸውን ከልጅነታቸው ጀምረው የሚያዩበትን መነፅር በማስተካከል ልጆች ለራሳቸው፣ ለማኅበረሰባቸው ብሎም ለሀገራቸው እንዲበቁ የሚያስችል መጽሐፍ ስለመሆኑ ትናገራለች፡፡

ወይዘሮ ሳራ እንደምትለው እናቶች ልጆቻቸውን በአግባቡ ለማሳደግ በጣም ይተጋሉ፤ ይለፋሉ። እንዲያም ሆኖ በልጆች አስተዳደግ ዙሪያ አሁንም የእውቀት ክፍተት ይታያል፡፡ ይህንን ክፍተት በማየት ትንሽ መደገፍ ይቻላል በሚል በዩቲዩብ ቻናሏ አማካኝነት በልጆች አስተዳደግ ዙሪያ ፕሮግራም ጀመረች፡፡ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ከውጪው ሰው ባላነሰ ኢትዮጵያውያን እናቶችም በልጆቻቸው ባሕርይ ላይ ለውጥ እያዩ በመምጣታቸው በዩቲዩብ የምታቀርበውን ፕሮግራም ወደ መጽሐፍ በመቀየር ‹‹ጤናማ የልጆች አስተዳደግ›› በሚል አሳትማዋለች፡፡

ልጆች! የወይዘሮ ሳራ ምኞት መጽሐፉን ብዙ ወላጆች ወስደውት እንዲጠቀሙበትና ልጆቻቸውን ነቅተው እንዲያሳድጉበት ማድረግ ነው፡፡ በተለይ ጊዜው የመረጃና የቴክኖሎጂ እንደመሆኑ ወላጆች ጊዜውን በዋጀ ሁኔታና ዘመኑ የሚፈልገውን ነገር መሠረት ባደረገ መልኩ ልጆቻቸውን እንዲያሳድጉም ፍላጎት አላት፡፡ ለዚህ ታዲያ “መጽሐፌ በቂ መልስ አለው ትላለች፡፡ በወላጆችና በልጆች መካከል ያለውን ክፍተት መሙላት የሚቻለው ከልጆች ጋር ትስስር በመፍጠር መሆኑን ትገልፃለች፡፡ ጥሩ ትስስር ካለ ደግሞ መልካም መግባባት እንደሚኖር ትጠቅሳለች፡፡

መጽሐፉ ኢትዮጵያውያን እናቶችና አባቶች አንብበው ተግባራዊ ቢያደርጉት በልጆቻቸው አስተዳደር ዙሪያ ተጨባጭ ለውጥ የሚያዩበት እንደሆነም ወይዘሮ ሳራ ተናግራ፤ አንደኛው የመጽሐፍ ምዕራፍ በእድሜ የተከፈለ ሲሆን እድሜን ያማከለና ሳይንሳዊ መንገድን የተከተለ የልጆች አስተዳደግ ዘዴ ሲሆን፣ ወላጆች ልጆቻቸው በየእድሜ ደረጃቸው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለመወሰን እንደሚረዳቸው ትገልፃለች፡፡ ሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ ልጆችን የማሳደግ ተግባራዊ እንክብካቤ ምን እንደሚመስል ወላጆች እንዲረዱ የሚያስላቸው መሆኑን ትናገራለች፡፡

ልጆች፣ እናንተም ነገ አድጋችሁ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች የምትሰማሩና ሀገር ተረካቢ ዜጎች ናችሁና በመልካም ሥነ-ምግባርና በእውቀት ታንፃችሁ እንድታድጉ ከመምህራን በተጨማሪ ወላጆቻችሁም ለእናንተ አስተዳደግ ትልቅ አስተዋፅዖ አላቸውና ወይዘሮ ሳራ የፃፈችው ‹‹ጤናማ የልጆች አስተዳደግ›› የተሰኘውን መጽሐፍ እንዲያነቡ ጋብዟቸው፡፡ መልካም የትምህርት ጊዜ ይሁንላችሁ!!